# ባለፉት ፴ ዓመታት ሰማዕታተ ክርስትና

# ዝክረ ሰማዕታት


ዓለም አቀፍ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ሕብረት

International Orthodox Tewahedo Alliance (IOTA)



ግንቦት 2015/May 2023



office@iotaethio.org

# 1 መግቢያ

## 1.1 የጽሑፉ ዳራ

የጽሑፉን ዳራ ለመቃኘት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አጭር ቅኝት እንመለከታለን፡፡ በዚህ ዓለም የምትገኘዋ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜም በተጋድሎ ላይ ናት። በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሱ ያሉ መከራዎች አባቶቻችን ያለፉበት መሆኑ ይታወቃል። በዘመናችን እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከአገራችን ማጥፋትን ታስቦ የሚፈጸሙ ናቸው። ጥንት አባቶቻችን ያደርጉት እንደነበረው ቤተ ክርስቲያንን የሚመጥን በቂ ምላሽ በመሥጠት ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ ጥብዓቱ በዚህ ዘመን እየቀነሰ መሆኑ ይታወቃል። ችግሩን አሳሰቢ እያደረገው ይገኛል።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመስቀል ላይ የተመሠረተች በመሆኗ ከመከራ ያረፈችበት ጊዜ የለም፡፡ ዮዲት ጉዲት፣ አህመድ ግራኝ፣ ካቶሊኮች፣ ፋሺስት ኢጣሊያ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል። በዘመነ ደርግ ደግሞ እግዚአብሔር የለም በሚል መርሕ አምልኮተ እግዚአብሔርን ወደ መከልከል ደረጃ ተደርሶ ነበር፡፡ በ1983 ዓ.ም ከተካሄደው የመንግሥት ለውጥ በኋላም በቤተ ክርስቲያን ላይ በዓይነትም በመጠንም የተለያየ መከራ ደርሶባታል። ብዙዎቹ ጥቃቶች የሚፈጸሙት በአክራሪ እስልምና ሲሆን አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በመንግሥት መዋቅር በተቀመጡ ፕሮቴስታንቶች ድጋፍ ይፈጸማሉ። በጨቋኝ ተጨቋኝ ላይ የተመሠረተው የአገራችን ሕገ መንግሥት ሌላው አካል ቤተ ክርስቲያንን ጨቋኝ አድርጎ በመሳል ቢችል ማጥፋት ካልቻለ ደግሞ ማዳከም ይፈልጋል።

የመንግሥት ባለ ሥላጣናት በአክራሪነት መፈረጅ፣ የአንገት ማተብ መበጠስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ሰሚዎች በሚፈልጉት መንገድ አስተካከለን እንድናስተምር እስከ ማስጠንቀቅ ደርሰዋል። ከዚህም አልፎ ለረጅም ዘመናችን የኖረችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ዕውቅና እንደ ሌላቸው ተቋማት እንደ አዲስ እንድትተመዘገብም ተሞክሮ ነበር። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እየተፈጸመ ያለው ጥቃት መንግሥታዊ ድጋፍ ያለው መሆኑን ደፍሮ ከመናገር መቆጠቧም ለአጥፊዎች ተጨማሪ ጠቃት እንዲያደርሱ ዕድል ፈጠረላቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገር መሆኗ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከተነገረ ጀምሮ እስካሁን ከተፈጸሙባት በከፋ ሁኔታ ጥቃቶች ቀጥለዋል። መንግሥትም አገርነቷን ከመመስከር አልፎ አገር ሲጠፋ ሊደረግ የሚገባውን የመከላከል፣ የመጠበቅና ሥርዓት የማስከበር ኀላፊነቱን ባለመወጣቱ ጥፋቱም ጥቃቱም ቀጥሏል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥቃቶች መቀጠላቸውን ከመናገር ወደ ማስቆም አልተሸጋገሩም። ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ በየደረጃው በአገልግሎት ላይ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ አስተዳደር አካላት የሚያቀርቧቸው የእንወያይ ጥያቄዎች እንኳን በመንግሥት አካላት ተቀባይነት አያገኙም። እንዲህ ያለው ድርጊት በአማኖቹ ዘንድ ተናቅን፣ ተደፈርን የሚል ስሜት ያሳድራል። ሰላምና ደኅንነትን ሊያረጋግጥ የሚችል መንግሥታዊ አካል ከሌለ ጉዳዩን በውል ለማስረዳትና ለዓለም ለማሳወቅ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግና ራሳቸውን በማደራጀት ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ አለብን ወደሚል ውሳኔ እንዲሸጋገሩ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለ2000 ዓመታት ሰውን ለድኅነት ለማብቃት ስትተጋ መኖሯ ከዘለዓለማዊ ሕይወት ባሻገር ጤናማ ለሆነ ምድራዊ ጤናማ ኑሮ የሚበጁ ተግባራትን ስታከናውን ኖራለች፡፡ በዚህም ከምእመናኗ በተጨማሪ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወሳኝና ጠቃሚ፣ በዓለም መለያ የሆኗቸውን ዕሴቶች ማስገኘት ችላለች። አገራችን በነጭ በቅኝ ገዥዎች ላለመወረሯ ቀዳሚውን ሚና የተጫወተችውም እርሷ ናት። የሥነ-ምግባርና የሞራል ምንጭ በመሆን፣

ሀገሩን የሚወድ፣ በሕግና ሥርዓት የሚመራ ሥልጡን ማኅበረሰብ በመገንባት በመገንባት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ነጮች ጭምር የሚመሰክሩት ነው። የራሷ ቋንቋና ፊደል ያላት፣ ለሥልጣኔ፣ ለኪነ ጥበብ፣ ለሥነ-ልሳን፣ ለመልከዓ ምድር፣ ለደንና የተፈጥሮ ሀብት መጠበቅ፣ ለሥነ-ሕንጻ ምርምር የሚጠቅሙ መጻሕፍትን አበርክታለች፡፡ ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሁሉ አስተዋጾ ማበርከቷ ተረስቶ በአሁኑ ሰዓት ረቂቅ እና ታቅዶበት የሚፈጸም፣በመንግሥት ድጋፍ ያለውና የፖለቲካ ፓርቲዎችም ጭምር ሰፊ ሱታፌ የሚያድርጉበት ጥቃት በመፈጸም ላይ ነው። በሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና በአማኞቿ ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ልዩ ልዩ መገለጫዎች ያላቸው ናቸው። ለማሳያ ያህል፡-

**ሀ. ኃይል የታከለባቸው ጥቃቶች፡-** ኦርቶዶክሳውያንን በአሰቃቂ ሁኔታ መግደል፣ አካል ማጉደል፣ አብያተ ክርስቲናትን ማቃጠል፣ የኦርቶዶክሳውያንን ቤት፣ ሰብል፣ ከብት ማቃጠል፣ ንብረት መዝረፍ፣ የቤተ ክርስቲያንን ይዞታ መንጠቅ፣ ኦርቶዶክሳውያን በኢኮኖሚ አቅማቸው ደካማ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ከወሳኝ የንግድ እና ገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲገለሉ ማድረግ፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም እንድትዳከም፣ ይዞታዎቿን እንድታጣ፣ በሙስናና በተለያዩ ብልሹ አሠራሮች እንድትጠመድ ማድረግ፣ ከተለያዩ የትምህርት እና የሥራ ዕድሎች ኦርቶዶክሳውያንን በዘዴ ማግለል።

**ለ. ማኅበረሰባዊ ጥቃት፡-** ነባር ኦርቶዶክሳውያን ትውፊት ከሆኑት ከዕድር፣ ከዕቁብ እና ከመሳሰሉት ማግለል፣ በትምህርት ቤቶች ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትና አስተምህሮ እንዳይነገር ማድረግ፣ ኦርቶዶክሳውያን በሚበዙባቸው አካባቢዎች የቤተሰብ ምጣኔን ምክንያት በማድረግ እንዲቀንሱ ማድረግ።

**ሐ. ፖለቲካዊ ጥቃት፡-** ኦርቶዶክሳውያን ከከፍተኛ ሥልጣን፣ ከሀገራዊም ሆነ በተዋረድ ከሚገኙ ኃላፊነቶች እንዲገለሉ ማድረግ፣ በሥልጣን ላይ በሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ላይ የሐሰት ትርክት በመፍጠር ስም ማጥፋት ዘመቻና ሥነ-ልቦናዊ ጫና በመፍጠር ከሥልጣን እንዲለቁ ማድረግ፣ ኵላዊት የሆነችንውን ቤተ ክርስቲያን ለተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ መስጠት፣ ካለፈ ሥርዓት ጋር በአሉታዊ መንገድ ማዳበል፣መፍትሕ መንፈግ፡- ፍትሕ መንፈግ፣ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ በሕግ ውስጥ አለማካተት፣ ከውጭ አካላት ጋር ተባብሮ ማጥቃት፣ የቤተ ክርስቲያኗ መንፈሳዊ ፍርድ ቤት ዕውቅና እንዳይኖረው መከልከል፣ ለሙብቷ ዕውቅና መንፈግ፣ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የፍትሕ ሥርዓቷ ጣልቃ በመግባት አቅም ማሳጣት፣ ተበዳይ የሆኑ ክርስቲያኖች ወደ ሕግ እንዳይሄዱ ማስፈራራት፣ የፍትሕ አካላት ከበዳዮች ጋር የዓላማ አንድነት መኖሩ፣ ልዩ ኃይል፣ ወንጀል ምርመራ አካባቢ የኦርቶዶክሳውያን ድምጽ አለመስማት፣ ወንጀሎኞች ያለፍርድ መልቀቃቸው፣ በዳይን ለቆ ተበዳይን ማሰር፣ የአብያተ ክርስቲያናትን ይዞታዎች መውረር/የጥምቀት የልማት የደመራ ቦታዎችን በግፍ መንጠቅ፣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ቦታ እንዳታገኝ መከልከል፣ የሚሉት ይገኙበታል።

አስቀድሞ የተጠቀሰውን ጥቃት የሚፈጽሙትም፡- ፖለቲካውን ለሃይማኖታዊ ድብቅ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ የሚጠቀሙ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል በየደረጃው የተሰገሰጉ የመንግሥት አካላት፣ አክራሪ ሙስሊሞች፣ እና በእነሱ የሚዘወሩ የተለያዩ ቡድኖችና አደረጃጀቶች፣ በተለያዩ ፕሮቴስታንት ስም የተደራጁ ቤተ እምነቶችና በውስጣቸው የሚያገለገሉ የሐሰት ነቢያት፣ ፓስተሮችና ከተመዘገቡበት ዓላማ ውጪ በቤተ ክስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ ዘረፋና ሃይማኖት የማስቀየር ተግባር የሚፈጽሙ ዓለም አቀፍ "ግብረ ሠናይ" ድርጅቶች፣ የሚደርሱ ጥቃቶችን ተከታትሎ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማሳወቅ የተቋቋሙ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች የኦርቶዶክሳውያንን ጥቃት ሆን ተብሎ የአለማቀፉ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዳይሰማው በሪፖርታቸውን ሰሚዎች በሚፈልጉት መንገድ ማቅረባቸው ተጠቃሽ ነው።

### 1.2 የመረጃው አስፈላጊነት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በምእመናኖቿ ላይ ሃይማኖት ተኮር ጥቃት በየዘመናቱ መፈጸሙ ይታወቃል። በጥቃቱ ምእመናን ተሰደዋል፤ ሞተዋል፤ ሀብት ንብረታቸውን አጥተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ጠብቃ ያቆየታቸው ቅርሶችና ንዋያተ ቅድሳት ወድመዋል። ጥቃት አድርሾቹ የተለያዩ ቢሆኑም የዓላማ አንድነት ያላቸው መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ። የመጽሐፉ አስፈላጊነትም ለሃይማኖታቸው መከራ የተቀበሉ ክርስቲያኖችን በመዘከር የደረሰባቸው መከራ የሃይማኖታቸው ፍሬ መሆኑን ለመጭው ትውልድ ለማሳወቅ ነው። ለአንባብያንና ለተመራማሪዎች ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት የሚለው ሁለተኛው ነው። በየጊዜው የሚፈጸሙ ጥቃቶች በመንግሥትም ሆነ በግል ብዙኃን መገናኛዎች በቂ ሽፋን ባለማግኘቱና ችግሮቹን ለማስወገድ በሚመለከታቸው አካላት የተሠሩ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎች ባለመኖራቸው ምክንያት በየጊዜ ችግሩ እየከፋ መሔዱን ለማሳየት። በኦርቶዶክሳውያን ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ድንገተኛ ሳይሆኑ ታስቦባቸውና በሚገባ ታቅደው፣ መዋቅራዊ ድጋፍም አግኝተው የሚፈጸሙ መሆናቸውን ለማሳየት መጽሐፉን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል።

### 1.3 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና ምንጮች

ዘገባው የተዘጋጀው የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ሲሆን ዋና ዋናዎቹ መረጃ አቀባዮችም ጥቃቶቹ ሲፈጸሙ ለተመለከቱ እማኞች የተሰበሰቡ የቃል፣ የፎቶና የተንቀሳቃሽ ምስል መረጃዎችና ጥቃቱ በደረሰባቸው አካባቢዎች የተላኩ የመረጃ ሰዎች የተሰበሰቧቸው መረጃዎች፣ ጥቃቶቹ ከተደረሱ በኋላ በተለያዩ የሚዲያዎችና ኅትመት ውጤቶች የተሰራጩ ጽሑፎች፣ እስከ አጥቢያ በተዘረጋው መዋቅር የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የቀረቡ የአህጉረ ስብከት ሪፖረቶች ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪ ጥቃቶች እንደ ተፈጸሙ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ብዙኃን መገናኛ የተለቀቁ መረጃዎችን ለማመሳከሪያ ተጠቅመናል።

## 2 የቤተክርስቲያን ጥቃት ለምን?

### 2.1 መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጥቃት ለምን ይሳተፋል?

ላለፉት 50 ዓምታት ሥልጣን ላይ የሚወጡ አካላት ጸረ-ኦርቶዶስ አቋም ያላቸው ናቸው። አቋማቸውንም በፖለቲካ ማንፌስቷቸው አስቀምጠውታል። ሥልጣን የሚገኘው ነባር እና ጥንታዊ የሆነን ነገር ሁሉ በአዲስ እና በተውሶ አስተሳሰብ በመተካት መሆኑ የሚታወቅ ነው። በተንሸዋረረ አስተሳሰብ የሚመሩ በመሆናቸው እንቀፋት ይሆኑብናል ብለው ከሚያስቧቸው መካከል ዋነኛዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ይህ የተሳሳት አስተሳሰባቸው ለኦርቶዶክሳውን መገፋት ክፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረገ ነው። መንግሥት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቤተ ክርስቲያንና በአማኞቿ ላይ በሚደርሰው ጥቃት እንዲሳተፍ ከሚያደርጉት ምክኛንያች መካከል በዋናው የተጠቀሰው ቢሆንም ሌሎች ምክንያቶችም አሉ፡፡ የመንግሥት የአስተዳደርና የጸጥታ መዋቅሮች በኢአማንያን በመያዛቸው የኢ/ኦ/ተ ቤተ ክርስቲያን ከዘውዳዊው ሥርዓት ጋር በመተባበር ስትጨቁን ኖራለች በሚል የተሳሳተ አመለካከት ብድር መላሽ ሆኖ መቅረብ ይገኝበታል።

### 2.2 አክራሪ እስልምና በቤተ ክርስቲያን ጥቃት ለምን ይሳተፋል?

የአንዳንድ አክራሪ ሙስሊሞች ዓላማ ክርስቲያኖችን በመግደልና በማጥፋት ኢትዮጵያን እስላማዊ አገር ማድረግ ነው፡፡ ይህን ካሳኩ በኋላ ከአይ ኤስ፣ በምዕራብ አፍሪካ ከሚንቀሳቀሰው ቦኮ ሐራም እና በምሥራቅ አፍሪካ ከሚንቀሳቀሰው አል-ሸባብ የተባሉት ድርጅቶች ጋር ተመሳሳይ አመለካከት እና አስተምህሮ ያለው ድርጅት/ፓርቲ በማቋቋም ኢስላማዊ መንግሥትን መመሥረት ነው፡፡ እነዚህ አሸባሪ ድርጅቶች በግዛታቸው

ውስጥ ክርስቲያን የሚባል እንዲኖር አይፈቀድለትም፡፡ ነባር ሙስሊሞች እንኳን የእነርሱን አስተምህሮ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆኑ በስተቀር በሕይወት እንዲኖሩ አይፈቀድላቸውም:: በዚህ አስተሳሰባቸው በመካከለኛው ምስራቅ የራሳቸው አስተዳደር እስከመመስረት የደረሱበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ይህ አስተሳሰብ ሰፍቶ በተወሰኑ የሰሜን አፍሪቃ ክልሎችና በሶማሊያ ሰፊ ግዛቶችን እስከመቆጣጠር ደርሷል፡፡ ይህም በአጋጣሚ የተፈጠረ ሳይሆን አስቀደሞ እስልምና የተሰፋፋባቸውን አካባቢዎች መሰረት ያደረገናና በውቅቱ በነበረ የኢትዮጵያ ጠንካራ ክርስቲያን መንግስት ምክንያት መሰፋፋት ያልቻሉባቸውን ቦታዎች በማካተት ሰፊ እስላማዊ ግዛት ለመመሰረት ታስቦ የተሰራ ስራ ነው::  ከታች በምሰሉ ላይ የምንመለከተውም በቀጣይነት ሊመሠርቱት ያሰቡትን ግዛት የሚያመለክት ነው::




*ሥዕል 1*፡ በ"'Empire of Fear: Inside the Islamic State" በተባለ መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ከአይ ኤስ በቀጣይነት ዓለምን ለመቈጣጠር ያወጣው የግዛት መስፋፋትን የሚያሳይ ካርታ ነው።

በካርታው ላይ እንደምንመለከተው ከስፔን እስከ ቻይና ድረስ የተዘረጋ፣ ከምዕራብ አፍሪካ እስከ አፍሪካ ቀንድ ድረስ ከምድር ወገብ በላይ ያለውን የሚያካትተው ክፍላተ ዓለም የሚያካትት ነው። ከምዕራብ ስፔን፣ ሰሜን አፍሪካ፣ ማግረብ (ሙሉው ምዕራብ አፍሪካ ናይጀሪያን ጨምሮ)፣ አርድ አልኪናን (ሊቢያ እና ግብጽን)፣ አርድ አል ሀበሻ (ከካሜሩን ጀምሮ መካከለኛው አፍሪካ፣ የቪክቶሪያ ሐይቅ አካባቢ አገራት፣ ኢትዮጵያና ሶማልያ)፣ ሂጃዝ (ሳውዲ አረቢያ፣ የኤደን ባሕረ ሰላጤ አገራት)፣ የመን፣ ኩራሳን (አዘርባጃን፣ ፓኪስታን፣ ደቡብ ምዕራብ ቻይና) ኢራን እና ቱርክ ናቸው። የአረብ ምድርን እና ከፊል እስያን የሚያጠቃልለውን ግዛት ያካትታል፡፡ በዚህ ግዛትን እና አክራሪነቱን የማስፋፋቱ ጉዳይ ኢትዮጵያ ላይ ልዩ ትኩረት አለው፡፡ በአገራችን በተለያዩ ጊዜያት የሚፈጠሩ ሃይማኖታዊ ግጭቶች እና የአብያተ ክርስቲያናት ቃጠሎ መንስኤው ከዚሁ ግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ በአክራሪዎች የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የሚዘግበው “the religion of peace” ድረ ገጽ በአማካይ በወር ከ200፣ በዓመት ደግሞ ከ2400 በላይ ጥቃቶች እንደሚፈጸሙ ያመለክታል፡፡ በጥቃቶችም ብዙዎች ሕይወታቸውን ያጣሉ፤ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ክርስቲያኖች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፣ ሴቶች ለወሲብ ባርነት ተዳርገዋል፤ አዛውንት ያለ ተንከባካቢ፣ ሕፃናት ያለ አሳዳጊ ቀርተዋል፡፡ በተለይ ራሱን እስላማዊ መንግሥት እያለ የሚጠራው አሸባሪ ቡድን በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሐንን አርዷል፡፡ በኢራቅ፣ ሊቢያና ሶርያ ውስጥ የሚገኙ ብዙ ጥንታዊ ቅርሶችን በተለይም ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን አውድሟል፡፡ በተለይም የኢራቅ እና የሶሪያ እስላማዊ መንግሥት (Islamic State in Iraq and Syria) አካል የሆነው ዳይሽ የሚባለው ቡድን በሊቢያ ውስጥ እስላማዊ መንግሥት ለመመሥረት እና የሰለፊያን አስተምህሮ ለማስፋፋት ሊቢያን የጦር አውድማ አድርጓታል፡፡ ቦኮ ሐራም እና አል-ሸባብ የተባሉት ድርጅቶችም ከአይ ኤስ ጋር የጋራ ግብ ያላቸው ድርጅቶች ሲሆኑ በተመሳሳይ በናይጀርያ ፣ ሶማሊያና ኬንያ ተመሳሳይ ጥቃቶችን እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡

በእንደዚህ ያለ ተልእኮ የተጠለፉ አክራሪ የሆኑ አንዳንድ የአገራችን ሙስሊሞች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ለማሳያ ያህል፦ ራሱን ጂሐዲ ጆን ብሎ የሚጠራ በተለያዩ የቪዲዮ ምስሎች ላይ ከስምንት በላይ ሰዎችን አንገት ሲቀላ የሚያሳይ ሙሐመድ ኢምዋዚ የሚባል የኩዌት ተወላጅ እንግሊዛዊ ሲሆን የዚህ ሰው የቅርብ ጓደኛ የነበረው አሊ አዶረስ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ እንግሊዛዊ ዜግነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡ አሊ አዶረስ ከሙሐመድ ኢምዋዚ ጋር ቅርብ ግንኙነት የነበረውና በዚህ ቡድን ውስጥም ሱታፌ ያለው አሸባሪ ነው፡፡ አሊ አዶረስ በ2015 ዓ.ም በአሸባሪነት ወንጀል ተጠርጥሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ታስሮ ነበር፡፡ በተጨማሪም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሙሐመድ የሚባል የ17 ዓመት ልጅ ኢራቅ ውስጥ ለአይሲስ ሲዋጋ መሞቱ ይነገራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰሚራ አባስ የተባለች ጽንፈኛ ከሌሎች ሁለት ጓደኞቿ ጋር ከዚህ ቡድን ጋር እንደተቀላቀሉ ብዙ መገናኛ ብዙኀን ዘግበውታል። እነዚህ አክራሪ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከሌላው ሕዝብ ጋር አብሮ ተቻችሎ የመኖር ነባር ባህልን እያበላሹ መሆኑን የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤትም ገልጧል።

እስልምና ከራሱ እምነታዊ አስተምህሮ በመነሳት በሚቻለው መንገድ ሁሉ ተገዳዳሪ እምነቶችን እና ሃይማኖትን በማናቸውም መንገዶች በማጥፋት፣ በሀገሪቱ ላይ የበላይ የመሆንና ሀገሪቱን በሸሪዓ የመምራት ዓላማ አለው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ በአማኞች ብዛት ከፍተኛ ቊጥር ያላትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማጥቃት ማዳከም እና ምእመኖቿን ከተቻለ በውድ፣ ካልተቻለ ደግሞ በግድ ማስለም እንደ ዓላማ ይዘውታል። ይህ ዓላማ እንደ ተቋም በአደባባይ ባይሰበክ በእምነቱ ስም የተደራጁ ቡድኖች እና የእምነቱ ተከታዮች ቤተ ክርስቲያንን ሲያጠቁ እና በተለያዩ ጊዜያት ጥቃቶችን ሲፈጽሙ ፤ በመስጊዶች ጭምር ተቋማዊ ድጋፍ ሲሰጣቸው እንጂ አንድም ጊዜ በመጅሊስም ሆነ ፤ በሌሎች በሚመለከታቸው የእምነቱ አካላት ሲወገዙ አይታይም፡፡ ቁርዓን ከ160 ጊዜ በላይ መግደልን የሚያዝ ሲሆን ፤ እስልምና በአንድ ሀገር ውስጥ ከአናሳነት ተነስቶ ሁሉን ወደ መቆጣጠር የሚያድግባቸው ፤ በኢኮኖሚ ፤ በፖለቲካ ፤ በማኅበራዊ ኑሮ ብሎ ጅሃድ እስከ ማወጅ የተለያዩ የእርምጃ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነዚህ ተተግብረው በተለያዩ ክፍላተ ዓለማት ውጤት እንዳስገኙ ይታወቃል

## 2.3 ከፕሮቴስታንት የሚፈጸም ጥቃት

የፕሮቴስታንት ተልእኮ ምራባዊ ባህልና አስተሳሰብ በአንድ አገር ሕዝብ ላይ በመጫን ማኅበረሰቡ ለምዕራባውያኑ ሸቅጥ ማራገፊያ ገበያነት ማመቻቸት ነው። በአገራችን ዓላማቸው እንዳይሳካ እንቅፋት የሆነችባቸው የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መሆኗን የእምነቱ መሪዎች ጭምር በተለያዩ ጊዜያት ሲገልጹ ተሰምተዋል። በመሆኑም ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው በመግባት በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ላይ የተጠናከረ ዘመቻ ከፍተዋል። ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች አንደኛውና ዋነኛው የሐሰት ትርክቶችን በመፍጠር ቤተ ክርስቲያን ያላለችውን ያለች፤ያለችውን ደግሞ የማታምንበት አስመስሎ ስም ማጥፋት ነው፡፡ በዚህም የተቻላቸውን ያህል የዋሃንን በማሳት ምእመናንን ዘረፋ ላይ ተሰማሩ፣ የመንግሥትን ሥልጣን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያኗን እንደ ተቋም የማጥቃትና የማዳከም ተግባር በማከናወን ላይ ናቸው።

## 2.4 የክርስቲያኖች በጥቃቱ ተሳታፊ መሆን

በቤተ ክርስቲያ መንፈሳዊ፣ ዕውቀታዊና መዋቅራዊ ሥልጣን የያዙት አካላት አንድም ከግንዛቤ ማነስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከግል ጥቅም ጋር በተገናኘ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ጥቃት እየደረሰ መሆኑን እያወቁ አይተው እንዳላየ ያልፉታል። ዝምታቸው መንግሥትም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት "ባለቤት ካልጮኸ" እንዲሉ አድርጓል።

# 3 በኦርቶዶክሳውያን ላይ የደረሰው ጉዳትና ውጤቱ

የአንድ ማኅበረሰብ ወይን ግለሰብ ወይንም ተቋም ጉዳት የሚመዘነው በሥነ ልቡና፣ በምጣኔ ሀብት፣ በገጽታ፣ በዕውቀት ሀብታት፣ በታሪካዊ ክብር፣ በመታመንና መተማመን፣ በፖለቲካ ተሳትፎና ተሰሚነት፣ በማኅበራዊና ሕጋዊ ዋስትና ሊሆን ይችላል፡፡ ለሃይማኖት ተቋም የተከታይ ቊጥርና በአስተምህሮው ጸንቶ የሚኖር፣ በሕይወት የሚገለጥ የጥራት መስፈርት ተጨማሪ ሆኖ ይታያል፡፡ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ በባህል ሽፋን፣ በፖለቲካ ቡድኖች ርዕዮተ ዓለም፣ በሌሎች እምነቶችና በመንግሥት መዋቅር ይደርስባት በነበረው ጥቃት ምክንያት ከተከሠቱ ችግሮች መካከል ለአብነት ያህል፡-

## 3.1 የምእመናን ፍልሰት

ሕዝብና ቤት ቈጠራ ተካሄዶ የተገለጠው በሁሉም የአገሪቱ ክፍል በተለይም በኦሮሚያ፣ በሶማሌ፣ በደቡብ ክልሎች ኦርቶዶክሳውያን ልዩ ልዩ ጫናዎች ተደርገውባቸዋል፡፡ ክርስቲያኖች የሚደርስባቸው ጫና በፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም እምነትን፣ ቋንቋንና ባህልን በማደበላለቅ፣ ኦርቶዶክስን ለተወሰነ ቋንቋ ተናጋሪ በመስጠት፣ በፖለቲካዊ ግፊት፣ ከዕድርና ከማኅበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚነትና መሪነት በማራቅ፣ የድህነትና ኋላቀርነት መንስዔ አድርጎ በመክሰስና ትውልዱ ለሃይማኖቱ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖረው በማድረግ፣ ኦርቶዶክሳውያን አናሳ በሆኑበት ወረዳዎችና ዞኖች ከመንግሥት መዋቅር በማስወገድና ፍትሕ በመንፈግና ባይተዋር በመደረጋቸው ከነባሩ ሃይማኖታቸው ፈልው ወደ ሌሎች ሔደዋል።

## 3.2 ከምጣኔ ሀብት መገፋት

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት፣ የአምልኮ ስፍራዎች፣ የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች አዳዲስ በሚፈጠሩ የከተሞች ማስተር ፕላኖች እንዳይካተት በማድረግ ይዞታዎቿ ካርታና ፕላን የላቸውም በሚል ምክንያት መንጠቅ፣ በሚናገሩት ቋንቋ ምክንያት ሀብት ንብረታቸውን

መዝረፍ፣ ሃይማኖታቸውን ምክንያት አድርጎ ያላቸውን እተነጠቁና ማስፈራሪያ እየደረሰባቸው ተፈናቅለዋል። በደቡብና ደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በምሥራቅና በሶማሌ የተደረገውን መፈናቀል ስንመለከት በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ ያነጣጠረ መሆኑን እንረዳለን። ድርጊቱም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የትምህርት፣ የዕውቀት፣ የጥበብ፣ ሥነ መንግሥት፣ የአስተዳደርና የፍትሕ ምንጭ መሆኗን ዕውቅና መንሣት ነው። በዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት የኢትዮጵያን የካበተ ዕሴት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ ኦርቶዶክሳዊው አስተሳሰብ እንዲገፋ ምክንያት ሆኗል።

## 3.3 ማጠልሸት

በሐሰተኛ ትርክትና ፖለቲካዊ ርዕተ ዓለም፣ በውጭ ገብ የማኅበረሰብ ሐቲቶችና ፍልስፍናዎች፣ በሥነ-ብዕልና በስነ-መንግሥት አስተምህሮዎች፣ በሥልጣኔና የመዘመን ትንታኔዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን በአሉታዊነት በማንሳት የተለመደ ነው። የድህነትና የኋላቀርነት ምክንያት አድርጎ በማቅረብ አዲሱ ትውልድ ከኦርቶዶክሳዊ ማንነቱ እንዲሸሽና እንዲሸማቀቅ ለማድረግ ተሞክሯል። በመገናኛ ብዙኃን፣ በፖለቲካ ክርክር፣ በሕዝባዊ መድረኮች መለፈፍ የተለመደ ሆኗል፡፡ በማኅበረሰብ እድገት ውስጥ በመላው ዓለም የነበረውን የፊውዳሊዝምና የባላባት ሥርዓት በመሥጠትና በማርክሳዊ ሌኒናዊ የመደብ ጭቆና ትርክት በመተንተን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሐሰት የጭቆና መሣሪያ እንደ ነበረች በማስተጋባት ከፍተኛ ጥቃት መፈጸም፤ የይህን ጥቃት ወደ በብሔረሰብእ የፖለቲካ ትንታኔ በማሳደግ ቤተ ክርስቲያንን በግድ ስቦ የማስገባት ከፍተኛ ጥቃት መቀጠሉና በቀጥታ ክርስቲያኖችን ግድያ፣ የስደት፣ የመገፋት ዒላማ ማድረግ ተጠናክሯል፡፡ የአምልኮ ቦታዎች ከክርስትና አስቀድሞ ነበሩ ተብሎ ለሚተረክላቸው ባህላዊ እምነቶች ተላልፈው እንዲሰጡ ወጣቱን መገፋፋት፣ አደጋ ሲደርስ ለማስቆም ባለመፈለግ ከፍተኛ ጥፋት ተፈጽሟል። ፍትሕ በመንፈግ ቤተ ክርስቲያን በሥነ ልቡናም፣ በአካልም እንዲሸማቀቅ ማድርግ ቀጥሏል፡፡

## 3.4 አገራዊ ተሰሚነትና ሁለንተናዊ ተሳትፎ መቀነስ

ኦርቶዶክከሳውያን ክርስቲያኖች እንደ ዜጋ፣ ማኅበረ ክርስቲያኑ እንደ ማኅበሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም በሀገራዊ ሁለገብ ውሳኔዎች ውስጥ እንዳይሳተፉ፣ የአንድ የፖለቲካ ብሔረሰብ መዋቅርና የፖለቲካ ተሳትፎ ልክ እንኳን ተነፍጋ እንድትጠፋ ተፈርዶባታል፡፡ የሕግ ድንጋጌ፣ የፖሊሲ ቀረፃ፣ የሀብት ክፍፍል፣ የዓለም አቀፍ ሕግጋት ውስጥ አገራዊ ስምምነቶች ሲፈጸሙ የክርስቲያናዊ ማኅበረሰብ ፍላጎት ሳይጠየቅና ዕውቅና ሳየይሰጠው ቀኖናን፣ ፍትሐ መንፈሳዊን፣ ትውፊትና ታሪክን የሚቃረኑ ሕጎችንና ደንቦች ይተገደበራሉ፡፡ ይህንን ሂደት ለማቃናት ቤተ ክርስቲያን ድምፅዋን የምታሰማበት አገራዊ የፖለቲካና የሕግ ሥርዓት ጠፍቷል፡፡ ገዳማቶቿ በልማት ስም እንዲፈርሱ፣ መኖኮሳት እንዲሰደዱ ሲደረግ ቆይቷል።

## 3.5 የኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ስደት

ክርስቲያኑ ሀብት ንብረቱን እየተነጠቀ ከገጠር ወደ ከተማ በመመሰደድ ድህነት ውስጥ እንዲገባ፣ መሬት አልባ እንዲሆን በተቀናጀ መንገድ ይደረጋል፡ ፡ ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው በሊሙ ገነት፣ ሊሙ ኮሳ፣ ሊሙ ሰቃ፣ ጋሌ፣ ጌራ፤ ጎሬና መቱ ዙሪያ በኖኖ ሰሌ ወረዳዎች፣ በምሥራቅ ሐረርጌ ጎሮ ሙጢ፣ ጂጂጋ ወዘተ ይገኙበታል፤ ከአገር ወደ ውጭ በተለይ በእምነት ወደማይመስሉን ማኅበረሰቦች የሚደረገው ፍልሰት ምንም አይነት ሃይማኖትዊ መብትን የሚመለከት መንግሥታዊ ጥበቃ ስለሌለው ተሰዳጁ በተለያዩ የባህልና የእምነት ጫና ሥር ገብቶ ተገዶ እምነት እንዲቀይር ይደረጋል፡፡

## 3.6 በሞት፣ በግድያ ፍትሕ ማጣት

ክርስቲያኖችን መግድል፣ማሳደድ፣ ንብረት መቀማት፣ አስገድዶ መድፈር፣ በግልፅና በስውር ጫና እምነት ማስቀየር ይካሄዳል፡፡ ለዚህ ሁሉ ፍትህ ለማግኘት የፍትሐ ሥርዓቱ የተደራጀው በጎሣና በእምነት መስመር በመሆኑ አየይቻልም፡፡ መብት መጠየቅ አደጋ ላይ ይጥላል። የየአህጉረ ስብከቱ አባቶችና የቤተክርስቲያን መዋቅር የክርስቲየንን መብቶች ለማስጠበቅ የሚያደርጉት ጠንካራና የተቀናጀ እንቅስቃሴ የለም፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የባህል አባቶችና የሌላ እምነት ተከታጩ ጉዳዩን የሚያወግዙት በመገናኛ ብዙሀን ከተገለጠ በኃላ ለፖለቲካዊ ጥቅም ብቻ ነው፡፡ በቀጥታ የክርስቲያኖችን ጥቃት የሚቃወሙ ሙስሊሞችና ሽመግሌዎች ከተገኙ አደጋ የይደርስባቸዋል፡፡ ለዚህ በሜታ ወረዳ በጨለንቆ ከተማ ክርስቲያኖችን መግደልና ማሳደድ አግባብነት እንደሌለው የሚናገሩ ሙስሊሞች ላይ ከደረሰው አደጋ በአቶ መሐመድ ሰያቃ ላይ የደረሰው ግድያ ምስክር ነው፡፡

# 4 ችግሩ መፍትሔ ካልተሰጠው በቀጣይ የሚጠበቁ አደጋዎች

የአገራችን ሕገ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ ቢደነግግም ኦርቶዶክስን በጥላቻ ወይንም ምዕራባውያንን ለማስደሰት በክልል፣ በዞንና በወረዳ ሥልጣን ላይ የተቀመጡ አካላት የፈቀዱትን እንዲያደርጉ ለቋቸዋል። እንዲህ መደረጉም በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ አሰቃቂ ግፍ እንዲፈጸም ምክንያት ሆኗል። አገሪቱን ከሚመራው መንግሥት፣ ከቅዱስ ሲኖዶስ፣ ከሌሎች የእምነት ድርጅቶች ችግሩ እንዲቆም ተባብረው ካልሠሩ በስተቀር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እና በምእመናን ላይ የተጋለጠው ከፍተኛ አደጋ በዚያው መቀጠሉ ነው።

እስካሁን ለደረሱት ጥቃቶች መንግሥትም ሆነ የሃይማኖት ተቋማቱ መፍተሔ ለመፈለግ የሚያሳዩት ዳተኛነት ምክንያት ወደ ፊት በኢትዮጰያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎች የሚከተሉት ናቸው። ይህ ግምታዊ ትንበያን መሠረት አድርጎ የተሠራ ቢሆንም ዕለት ዕለት እየተመለከትነው ካለው ክሥተት በመነሣት የቀረበ ነው። በሶሪያ፣ በግብጽ፣ በሕንድ እና በምሥራቅ አቢያተ ክርስቲያናት ላይ በሌሎች እምነቶችና ሴኩላር ነን በሚሉ መንግሥታት ከሚደርሰው ተጨባጭ መረጃ በመነሣት የተሠራ ነው። እየተካሄደ ያለውን ድብቅ ኦርቶዶክሳውያንን የማጥፋት ዘመቻ በማቆም ሕጋዊ፣ ተቋማዊ፣ ማኅበራዊና ፍትሐዊ ዋስትና በፍጥነት ማረጋገጥ ካልተቻለ፡-

- ክርስቲያኖች ከልዩ ልዩ የሀገራችን ክፍል ፈጽመው እንዲጠፉ ስለሚደረጉ አቢያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና ጉባኤ ቤቶች ይዘጋሉ፡፡
- በሂደት ላይ የሚገኘው ታሪክን በማጣመም ክርስቲያኑን የማሳቀቅ፣ የቤተክርስቲያንን አገራዊ ተሳትፎ የማኮሰስ ሁኔታ ተጠናክሮ ይቀጠጥላል፡፡ ሰላምን፣ የአገር ዳር ድንበርንና መሰል ታላላቅ አገራዊ ጉዳዮች በሚወሰኑበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ምንም ሚና የሌላት መሆኑ ማሳያ ነው።
- በተለይ ነቃ ያሉ ክርስቲያኖችን ከቀበሌ ጀምሮ እስከ አገራዊ የፖለቲከ ሥልጣን ተሳትፎ እንዳኖራቸው በማድረግ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያንን በአገሩ ባይተዋርና እንግዳ፣ ስደተኛና ለማኝ፣ ተቅበዝባዥና የበታች ማድረግ ሂደት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ሀብት፣ ሥልጣን፣ ዕውቀት፣ ኢትዮጵያዊ ዕሴት ከምድር ለማጥፋት ሲደክሙ፣ ገዳማትን ሲያቃጥሉ፣ አገርን ሲወሩ፣ ለዘመናት የዘለቀውን ነባር ትምህርት ከመደበኛ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ማስወጣታቸው።
- ክርስቲያን ወጣቶች በሃይማኖታቸው ምክንያት ከትምህርትና ከሥራ ዕድል፣ ከማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ተሳትፎ የመገለሉን ጫና ባለመቋቋም መፍለሳቸው።
- እንደ ጅማ፣ በሻሻ፣ ሊሙ ኮሳ፣ ሊሙ ሰቃ፣ ቄለም ወለጋ፣ አሰላ፣ ምስራቅ ሐረርጌ (በጎሮ ሙጢ) እንደ ተደረገው አስገድዶ እምነት ማስቀየር፣ መደብደብ፣ የእምነት ቦታ መጋፋት፣ ግድያ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

- ክርስቲያንን መግደል እንደ ግለሰቦች ግጭት በፖለቲካና በመገናኛ ብዙሀን እየተሰወረ ከየአካባቢው የማጥፋቱ ሂደት ይቀጠጥላል፤ ፖለቲከኞች ክርስትናን ሳይሆን ብሔርን በመቁጠር ድጋፍ ያሰባስቡበታል፡፡
- ውጭ-ገብ ዘመናዊያን እምነቶች፣ አረባዊ እስላም፣ የባህልን እምነቶች ወዘተን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ኦርቶዶክስን ማጠጥቃት በብሔረሰብ የፖለቲካ ድርጅቶች ተጠናክሮ ይቀጥላል (በሰላሌ የተደረገው የዋቂነፈታ ወጣቶች ጥቃትና የኦነግ መቀናጀት ይህንን ያሳያል)፡፡
- አገር ውስጥ ከተፈጠረው ሃይማኖታዊ አድልዎ ምክንያት ከአረብ አገራትና ከምዕራብ የሚመጡ አልሚዎች ኦርቶዶክሳዊያን በአገራቸው በእኩል ተወዳድረው በሁሉም የምጣኔ ሀብት፣ የትምህርትና የፖለቲካ ሕይወት እንዳየይሳተፉ ከፍተኛ አድልዎ የሚፈጽሙበት እድል እያደገ ይመጣል።
- ቀደም ሲል በብሔረሰብ ፖለቲካ ተቃኝተው በምዕራባዊያን ትምህርት ልቀው፣ በጥላቻና ሀሰተንነት ተገንዘው የሀሰት ትርከትን በመተረክ መጽሐፍት ሲያሳትሙ፣ ቤተክርስቲያንን ስም ሲያጠፉ የኖሩ ምሁራን ከምንጊዜውም የበለጠ ተሰባስበው በአውቀት፣ በታሪክ፣ በጥናትና ምርምር ስም የኦርቶዶስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያንን ስም ማጥፋቱን ይቀጠጥላሉ፤ በአሁኑ ጊዜ በድንዛዜ ውስጥ ቆሞ የሚገኘው በስም ኦርቶዶክስ ክርስቲያን የሆነው ምሁር በሴኩላሪዝም ጭምብል ሕሊናውን እየሸነገለ በሠለጠነ ፖለቲካ ስም እናት ቤተክርስቲያኑን ከሚያጠቁት ጋር ቆሞ መሳለቁን ይቀጥላል፡፡
- ዐረባዊ ፖለቲካዊ እስልምናው ምእመናን ከምጣኔ ሀብታ ማግለል እና ከአካላዊ ጥቃቱ በተጨማሪ ክርስትናን የሚያጎድፉ ሀሰተኛ ማጽሐፍትን በመተርጎም፣ በመጻፍ፣ የቤተክርስቲያንና የኢትጵያን ታሪክ በማስለም፣ የሕዝቡን የኖረ የትብብር ባህል በጥርጣሬና በጥላቻ እንዲተካ በማድረግ በኦርቶዶክስ ላይ ያነጣጠረ ጦርነቶችን መቀስቀስ፤ የአካባቢና የቦታ ስሞች በመቀየር፣ ክርስቲያናዊ አሻራዎችን ማደብዘዝ፣ ሥልጣን ላይ ከሚገኙ የነሳና ስውር የእምነት አጀንዳ ይዘው ከሚሠሩ የመንግሥትና የፖለቲካ ተቋማት ባለሥልጣናት ጋር በመሥራት በኦርቶዶክስ ክርስስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ግፍ ከመቼውም የበለጠ ለፍትሕ እንዳቀርብ፣ መገናኛ ብዙሀን እንዳየይደርስበት በማድረግ እልቂቱ ይጠናከራል።
- በኦሮሚያ ክልል በቁሮ ስም ስልጣን ላይ ባሉ ሰዎች ተደራጅቶና ሽፋን እየተሰጠው በክርስቲያኖች ንብረትና የአምልኮ ቦታ ላይ አደጋ የሚያደርሰው፣ ከአክራሪ እስልምና ጋር የሚቀናጀው ጥቃት ተጠናክሮ ይቀጥላል።
- እንደተለመደው የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ፖሊሶች፣ መከላከያ በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል እንዳላዩ በማለፍ፤ ወይንም የሁለት ሰዎች ግጭትና ድንገተኛ ችግር በማስመሰል ክርስቲያኖች ራሳቸውን በተደራጀ መልክ እንዳየይከላከሉ የማመቻቸቱ ሴራ ይቀጠጥላል።

# 5 በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና በምእመናን ላይ የደረሱ ጥቃቶች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያንና በምእምናንፕቿና አገልጋይ ካህናቶቿ ላይ የደረሰው ጥቃት አያሌ ቢሆንም ለማሳያነት ብቻ ይረዳ ዘንድ ከ1983 የመንግስት ለውጥ ጅምሮ ያሉትን ጥቂት መረጃዎች ለማሳየት የሚሞከር ሲሆን የተወሰኑት መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት ጊዜ ረዘም ያለ

ከመሆኑ አንጻር ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የመገናኛ ቴክኖሎጂው ማደግ በተነጻጻሪ የተሻለ መረጃ ለመሰብሰብ አስችሏል፡፡ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠንና እድገት ለማየት ይረዳ ዘንድ በተለያዩ ጊዜያት ከፋፍሎ ጉዳቱ በደረሰባቸው አካባቢዎች ለይቶ ማስቀመጡ ችግሩን ከመሰረቱ ለመቅረፍ ለሚሰሩ አካላት እንደግብዓት ስለሚያገለግል ሪፖርቱን በአራት ዓሥርት ዓመታት ተከፋፍሎ ተቀምጧል፡፡

## 5.1 ከ1983 – 1989 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች

### 5.1.1 በጅጁ ወረዳ

በ1984 ዓም አቦምሳ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ፣ አቡሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ አብሽራ መድኀኔ ዓለም በጉና ወረዳ አንድሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ተራም ቅዱስ ገብርኤልና መሶ ቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ በእሳት ሲወድሙ ሁለት አብያተ ክርስቲያን ደግሞ ፈርሰዋል፤ ጽላቱን ጨምሮ ተዘርፈዋል።

### 5.1.2 አርሲ ነገሌ ወረዳ

በምዕራብ አርሲ ዞን አርሲ ነገሌ ወረዳ ታኅሣሥ 9 ቀን 1984ዓ.ም 60 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 60 ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ ቆስለዋል፡፡ በወቅቱ የአካባቢው ነዋሪዎች የሆኑ ክርስቲያኖች ቤት ንብረታቸው ተዘርፏል፤ ወድሟል፡፡ 6987 ነዋሪዎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያን ተቃጥለዋል ፡፡

### 5.1.3 አርሲ

በ1984 ዓ.ም በ አ ር ሲ በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በጥይት ተደብድበው ሕይወታቸው ሳያልፍ ወደ ገደል ተጥለውና በእሳት ተቃጥለው ሲገደሉ፣ በሺዎች የሚቈጠሩ ደግሞ መኖሪያ ቤቶቻቸው ተቃጥለውባቸው ተፈናቅለዋል። ከብቶቻቸውና ንብረታቸው ተዘርፈውባቸዋል፤ ወድሞባቸዋል፡፡ በጅጁ ወረዳ አቦምሳ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ፣ አቡሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ አብሽራ መድኃኔ ዓለም፣ በጉና ወረዳ አንድሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ተራም ቅዱስ ገብርኤልና መሶ ቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ በእሳት ሲወድሙ፣ ሁለት አብያተ ክርስቲያን ደግሞ ፈርሰዋል። የብዙዎቹ ንብረት ተዘርፏል።

አርሲ ውስጥ ኮፈሌ ወረዳ በምትገኘው ቆሬ ከተማ ጥቅምት 24 ቀን 1988 ዓ.ም ከኢድ አልፈጥር በዓል መልስ ክርስቲያኖች የመንግሥት ተቀዋሚ በመሆናቸው እጃቸውን እንቆርጣለን በሚል ቄጥራቸው በውል ያልታወቁ ክርስቲያኖች ተደብድበዋል፣ በጩቤ ተወግተዋል፣ ቤቶቻቸውም ፈራርሰዋል። መንግሥት ችግሩ በሽማግሌ እንዲፈታ አሳብ ቢያቀርብም ጉዳዩ ከሙስሊም ሽማግሌዎችም አቅም በላይ በመሆኑ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።

### 5.1.4 ጎንደር

በሰኔ 4 ቀን 1988 ዓ.ም በጎንደር የአበራ ጊዮርጊስና በዓታ ለማርያምን ይዞታ ለመንጠቅ ሙከራ ተደርጓል። በቦታው ላይ የዛሬ 100 ዓመት አካባቢ አንድ ሙስሊም ተቀብሮበታል በሚል ሙስሊሞች የሐሰት መረጃ አቅርበው ነበር። እንድሁም በሰኔ 20 ቀን 1988 ዓ.ም በጎንደር ከተማ ኑር አሊ በሚባል ሾፌር ሰሌዳ ቁጥሩ 03984 በሆነ ከባድ መኪና ውስጥ የተመረዘ ጩቤ የተገኘ ሲሆን ፖሊስ ቀድሞ ባለመድረሱ ሾፌሩ ሳይያዝ ቀርቷል። ሳይሰራጩ የተያዙት 63 ጩቤዎች በአንድ መስጊድ ዉስጥ ተገኝተዋል፡፡ ከሰኔ 24 -26 ቀን በተደረገ አሰሳም 111 ተጨማሪ ጩቤዎች

ከአክራሪ ሞስሊሞች ቤት ለመሰብሰብ ተችሏል። ሰኔ 27 ቀን 1988 ዓ.ም ሙኪታር ሳህል ጅብሪል የተባለ የወሀብያ አራማጅ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠቃበትን ካርታ፤ አነስተኛ ካሜራ፤ የእጅ ቦምብ በመያዝ ከምሽቱ 2:00 ሰዓት ላይ ወደ መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም በማምራት ለማጥቃት ሙከራ ያደረገ ሲሆን ሁኔታው ያሰጋቸው አረጋውያን ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር ተባበረዉ አክራሪዎቹ የሚያዘወትሩበትን ቦታ በጠቆሙት መሠረት አካባቢው ሲፈተሽ የሦስት መኖሪያ ቤቶችን በማገናኘት የተሠራ የአጥፍቶ ጠፊዎች ማሠልጠኛ ተገኝቷል፡፡ በፍተሻውም የፋክስ ማሽን፣ ኢንተርኔት፣ ከአጥፍቶ ጠፊዎች ጋር የተደረጉ የፋክስና የኢሜይል ልውውጦች፣ የሚገደሉ የአብነት መምህራንና ተማሪዎች ስም ዝርዝር፣ የአጥፍቶ ጠፊዎች ዝርዝር፣ ለጂሐድ እንቅስቃሴ የሚሆን 70 ሚሊዮን ብር ባንክ ውስጥ መቀመጡ ተደርሶበታል። በተመሳሳይ ወቅትም በዳባትና ደንቢያም በሕጻናት መርጃ ማዕከላት ስም በተከፈቱ ድርጅቶች ውስጥ አጥፍቶ ጠፊዎች ሲሠለጥኑ ለመያዝ ተችሏል፡፡

## 5.2 ከ1990 – 1999 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች

### 5.2.1 ምዕራብ አርሲ

ኮፈሌና ቆሬ በ1992 ዓ.ም በተነሣ ግጭት ጉች መድኅኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል። በአርሲ ኮፈሌ ወረዳ ቆሬ ከተማ ጥቅምት 6 ቀን 1997 ዓ.ም 10 ክርስቲያኖችን ገድለው ሦስቱን በከፍተኛ ሁኔታ አቁስለው 2,237 ምእመናን ከአካባቢው አፈናቅለዋል። አንድ ቤተ ክርስቲያን እና 194 የክርስቲያኖች ቤቶችን ሙሉ በሙሉ አቃጥለዋል። 24 ተጨማሪ ቤቶች በከፊል ተቃጥለዋል። 304 የክርስቲያኖች ከብቶች ደግሞ ተዘርፈዋል። ጥቅምት 27 ቀን ቆሬ ቅዱስ አማኑኤል በዓል ለማክበር በተሰበሰቡ ክርስቲያኖች ላይ አክራሪዎች ጥቃት ለማድረስ ሞከረው ሳይሳካላቸው ሲቀር ወደ መኖሪያ ሰፈር በመሔድ የክርስቲያኖችን ቤት ሲደበድቡና ሲዘርፉ አድረዋል።

ኅዳር 6 ቀን 1998 ዓ.ም በአርሲ ሀገረ ስብከት በኮፈሌ ወረዳ ውስጥ የምትገኘው የአይሻ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፀረ ክርስትና አቋም ባለው ቡድን ስትቃጠል አገልጋዮቿ ካህናት በቤተ መቅደስ ውስጥ ታርደዋል፡፡ አሥር ሰዎች በገጀራ ሲገደሉ ብዙዎች ተጎድተዋል። በወቅቱ የአንሻ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ብዙ አብያተ ክርስቲያንና የ72 ክርስቲያን አባ ወራዎች መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል፤ ብዙ ንብረት ወድሟል፤ ነዋሪዎች ከቀያቸው ተፈናቀለዋል፡፡

### 5.2.2 ግራር ጃርሶ ወረዳ፡-

ሐምሌ 22 ቀን 1993 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገር ስብከት ግራር ጃርሶ ወረዳ የሚገኘው ደብረ ፍስሐ ሽንኩርት ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጥበቃ በቅርስ ዘራፊዎች ተገድለው ቤተ ክርስቲያኑ ተዘርፏል።

### 5.2.3 ኤፍራታና ግድም ወረዳ፡-

የምእመናንና የካህናት ሞት ሚያዚያ 6 ቀን 1993 ከሰሜን ሸዋ ሀገረ ስበከት ኤፍራታና ግድም ወረዳ በደብረ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሌሊት በማኅሌተ ላይ የነበሩ ምእመናን ላይ በአክራሪዎች የጥይት ሩምታ ወርዶባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የአንድ አባት ሕይወት ሊያልፍ ችሏል፡፡

### 5.2.4 ከሚሴ

ጥር 11 ቀን 1994 ዓ.ም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አክራሪዎች ገብተው ስድስት የሣር ክምር፣ 11 የአገዳ ክምር፣ አቃጥለው የቤተ ክርስቲያኑን አጸድ አፈረሱ። በጥር 11 ቀን 1998 ዓ.ም በተከበረው የጥምቀት በዓል ላይ በአክራሪዎች የከሚሴና የባቲ ክርስቲያኖች ተደብድበዋል።

### 5.2.5 ምሥራቅ፣ ቄለምና ምዕራብ ወለጋ

በጥቅምት 23 ቀን 1997 ዓ.ም በምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ዋንኬ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ምዕራብ በር በመስበር ታቦቱና ንዋየተ ቅድሳቱን ዘርፈዋል። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ቦታ ይዛ ሌላው በጠባብ ቦታ መቸገር የለበትም» በማለት የቤተ ክርስቲያኑን አጥር አስፈርሰው መስጊድ እንዲሠሩ ፈቅደውላቸዋል፡፡ በዚሁ ዕለት በአካባቢው በርካታ ክርስቲያኖች ተገድለዋል፤ ካህናት ተደብድበዋል።

### 5.2.6 መቱ (ኢልባቡር)

1999 ዓ.ም ገቺ ጎሌ ጋትራ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ በአክራሪ እስላሞች ወድሞ እንደ ገና በ260 ሺህ ብር ተሥርቷል፡፡ በተመሳሳይ ዓመት በዴዴሳ ወረዳ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የጨሎ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና የቀመቼ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቃጠሎ ደርሶባቸው በማኅበረ ቅዱሳን እገዛና በምእመናን አስተዋጽኦ ተገንብተዋል፡፡ ሆኖም ታላላቅ የእስልምና መድረሳ ትምህርት ቤት ያለባትና አክራሪነት የሚስፋፋባት የዬምቤሮ ከተማ በዙሪያዋ ያሉት ምእመናን ተረጋግተው እንዳይኖሩ በማስፈራራትና በመዝረፍ ብዙዎች ቦታውን ለቀው እንድሄዱ ተደርጓል፡፡

### 5.2.7 በጅማ እና አከባቢዋ

ጅማ በሻሻ አካባቢ ጎልቶ ጥቅምት 4 ቀን ለ5 አጥቢያ 1999 ዓ.ም በአጋሮ በሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በዓል ለማክበር በተሰበሰቡ ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ግድያና ቤተ ክርስቲያኑን የማቃጠል አደጋ ነው። የጉዳዩ መነሻ ኢሉ አባቦራ ዞን ደዴሳ ወረዳ ጨሎ የሚባል ቦታ ሲሆን ዕለቱም መስከረም 16 ቀን 1999 ዓ.ም የደመራ ዕለት ነበር፡፡ ግጭቱ የተነሣው የደመራው ጭስ ወደ መስጊዳችን ገባ በሚል አንዳንድ ሙስሊሞች በፈጠሩት ሁከት ነበር። ጉዳዩን ለማብረድ አቶ ክንዴ የሚባሉ ሽማግሌ ሲላኩ በድንጋይ በመፈንከታቸው ግጭቱ ተከሰተ፡፡ በዚህ ግጭት ምክንያት ከሁለቱም ወገን ሰዎች ሲሞቱ በዚህ ድርጊት የተበሳጩት ሙስሊሞች መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም ጨጉ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን አቃጠሉ።መስከረም 28 ቀን 1999 ዓ. ም የበሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ለማቃጠል ሞከሩ። የቤተ ክርስቲያኑ በር ስለተቃጠለ የአጋሮ ወረዳ ቤተ ክህነት ታቦቱን ወደ አጋሮ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ ለአንድ ሣምንት ቆይተዋል፡፡ በኋላም በሩን በማሰራት፣ ጥቅምት 5 ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ዓመታዊ ክብረ በዓል ለማክበር በዋዜማው ታቦቱ ወደ መንበሩ እንዲመለስ ተደረገ፡፡ በተፈጠረው ግጭት ምክንያት የፌደራል ፖሊስ እንዲገባ የተደረገ ቢሆንም በወቅቱ የነበረው የአጋሮ ከተማ ከንቲባ ወታደሮቹን "ከዚህ በኋላ ሠላም ነው" በማለት ጥቅምት 4 ቀን 1999 ዓ.ም ለጥቅምት 5 ዋዜማ የአጋሮን ወረዳ ለቀው እንዲወጡ አድርጓል።

በዚያ እለት የአጋሮ ምዕመናን፣ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች፣ እንዲሁም ካህናት አባቶች በዓሉን ለማክበር ወደ በሻሻ ሲሄዱ በመንገድ ላይ የሚገኙ ሙስሊሞች ክርስቲያንን እንደሚያርዱ በምልክት ይናገሩ እንደነበር በወቅቱ የነበሩ ምስክሮች ተናግረዋል። ምእመናን ሀገር ሠላም ነው በማለት ወደ ቦታው በመሄድ ዋዜማውን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፉ በኋላ ከሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ላይ የማኅሌት አገልግሎት እየተፈጸመ ሙስሊሞቹ ጦር፣ ገጀራ፣ እሳት፣ ማቀጣጠያ ቤንዚን እና ሌላም የጥፋት መሣሪያ ይዘው ቤተ ክርስቲያኗን ከብበው ምእመናንን መጨፍጨፍ ጀመሩ። በዚህ ድርጊት 6 ሰዎች ታርደዋል፤ ከሞቱት ውስጥ ካህናት፣ ሽማግሌዎች፣ እናቶች ነበሩበት። ከ16 ሰዎች በላይ በገጀራ ተቆርጠው የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፤ ከ30 ሰዎች

በላይ ተደብድበዋል። ቤተ ክርስቲያኑ ከምእመናኑ አስከሬን ጋር ተቃጥሏል፤ አንድ አይሱዙ መኪና ተቃጥሏል፤ እህቶች ተደፍረዋል፣ ውሃ ጠማን ላሉ እህቶች የሰው ደም ቀድተው አጠጥተዋል፤ ከ2000 በላይ ሰዎች ከቀያቸው ተፈናቀለዋል( ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ የጥቅምት ወር የ1999 ዓ.ም)።

በአጠቃላይ ከመስከረም 16 እስከ ጥቅምት 4 ለ5 አጥቢያ 1999 ዓ.ም በተፈጠመው ጥቃት ኦርቶዶክሳውያን ታርደዋል፤ በሺህ የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች ተፈናቅለዋል፤ አብያተ ክርስቲያን ተቃጥለዋል፤ የብዙ ክርስቲያኖች ንብረት ወድሟል፤ ተዘርፏል፤ የክርስቲያኖች አስከሬን ለሰው ክብር በማይመጥን ሁኔታ መሬት ላይ ተጥሏል፡፡ ቁምቢ በተባለ ቦታ ምእመናን ማተባችሁን ካልበጠሳችሁ ተብለው ሲጠየቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጣቶቻቸው በገጀራ ተቆራርጧል፡፡ ከመስከረም 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ ቀናት፣ በጎማ፣ በማና፣ በቶባ እና በኢሉባቦር ሀገረ ስብከትም በዴዴሳ ወረዳ፤ የጦር መሣርያና ገጀራ የያዙ አክራሪዎች 12 ክርስቲያኖችን ገድለዋል፣ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን (የጩጎ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቦሬ ቅዱስ ገብርኤል እና በሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ) ማቃጥለዋል፤ ንዋያተ ቅድሳቱንም ዘርፈዋል፤ ከ800 በላይ የአባ ወራ ቤቶችን አቃጥለው ከቀዬያቸው አፈናቅለዋቸዋል። አንዳንዶችን በግድ አስልመዋል፡፡

## 5.3 ከ2000 – 2009 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች

### 5.3.1 ጎንደር

በ2000 ዓ.ም በበየዳ ወረዳ የሚገኘው ጥንታዊው የበየዳ ደብረ ኃይል ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከነገሥታት የተበረከቱ ከ23 ሺህ ግራም በላይ የሚመዝኑ ሁለት የእጅ መስቀሎች፣ በጥፍጥፍ ወርቅ የተለበጡ ሁለት ጋሻዎች ተዘረፈዋል። በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት በ2005 ዓ.ም. ስድስት አድባራት የተቃጠሉ ሲሆን ለቃጠሏቸዉ ምክንያት አልተወቀም፡፡ ሦስቱ በአንድ አካባቢ፣ ሦስቱ በተራራቀ ሁኔታ በቆላ፣ በደጋ፣ በከተማ አቅራቢያ የሚገኘ ናቸው። የዞኑ አስተዳደርም ሆነ የክልሉ መንግሥት በወቅቱ ለተፈጠሩት ችግሮች መፍትሔ አልሰጡም፡፡

### 5.3.2 ድሬዳዋ

የደብረ በረከት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጥቅምት 26 ለ27 አጥቢያ ሌሊት ማንነታቸው ያልታወቁ አካላት ባፈነዱት ቦንብ በሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ላይ ጉዳት ደረሷል፡፡

### 5.3.3 መቱ (ኢልባቡር)

በ2002 ዓ.ም የቦረቻ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ታቦት በአክራሪ እስላሞች በመዘረፉ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ተዘግቷል። የፖለቲካውን ከለላ በማድረግ ሥልጣን ላይ የተቀመጡ ክርስቲያኖችን በተለያየ ምክንያት ከሥልጣን እንዲ ወርዱ ሲደረግ፣ በንግድ ሥራ በተሰማሩ ክርስቲያኖች ላይ ማስፈራሪያት፣ ዛቻና ዘረፋ ተፈጽሞባቸዋል።

### 5.3.4 ደሴና ኩታበር

በ2003 ዓ.ም ደሴ ቅድስት አርሴማ ቤተ ክርስቲያን በአክራሪ ሙስሊሞች የፈረሰች ሲሆን የኩታበር አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል።

### 5.3.5 ምሥራቅ፣ ቄለምና ምዕራብ ወለጋ

የምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ጥቅምት 4 ቀን 2006 ዓ.ም ለ32ኛው ዓመታዊ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ባቀረበው ሪፖርት በሀገረ ስብከቱ የተፈጸሙትን በደሎች መናፍቃን በገንዘብ እንዲሁም ሥልጣን ላይ በሚገኙ መናፍቃን እንደሚደገፉ፣ የቤተ ክርስቲያንን ይዞታ ለመናፍቃን በመስጠታቸው ሀገረ ስብከቱ ክስ ላይ ስለመሆኑ፣ ትውልድን ይቀርፃሉ ተብሎ ኃላፊነት የተጣለባቸው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የዘመናዊ ትምህርት ቤት መምህራን ከክርስቲያን ሕፃናት ማዕተብ ማሰር አትችሉም በማለት ከአንገታቸው መበጠሳቸው ተገልጧል። በባቦ ገምቤል ወረዳ ሓላፊነት በማይሰማቸው የፖሊስ ሠራዊት ምእመናን ተደብድበው ከአንገታቸው ማዕተብ መበጠስ፣ ወጣቱ በቅድስቲቷ እምነት እንዲያፍር ማድረግ፣ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር፤

- ካህናት በጸሎተ ቅዳሴ አገልግሎት ላይ ሳሉ በወረዳው ባለሥልጣናት ተይዘው እስር ቤት መወሰድ፣ ቤተ ክርስቲያኑ ያለቍልፍ ውሎና አድሮ በሕዝብ መጠበቅ
- የካህናት በባለሥልጣናት ትእዛዝ መንበርከክ፣ መቀጥቀጥ፣ ለከፍተኛ ኢ-ሰብአዊ አደጋና ሥቃይ መዳረግ፤
- በዕለተ ሰንበት ካህናት አገልግሎት ላይ እያሉ ምእመናንን «ውጡና ወደ ስብሰባ ሂዱ፤ ለቅዳሴ ቄሶች ይበቃሉ» ከማለት አልፎ ጥዋት ከኪዳን መልስ መኪና መንገድ ላይ አቁመው የ10 ዓመት ዕድሜ ካላቸው የሰንበት ት/ቤት አዳጊዎች ጀምሮ በመኪና ጭነው ወደ ቀበሌው እስር ቤት መውሰድ
- በቅዱስ ሚካኤል የወርኃዊ መታሰቢያ በዓል ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጎን የእርሻ ቀን አድርገው በማመቻቸት «በአማራ አገር ቄሶች ጥላ ይዘው ገበሬ ማኅበር እርሻ ላይ ተገኝተው ያሳርሳሉ» በማለት ቅዳሴ እየተቀደሰ አንድን ቄስ በማስገደድ ጥላ ይዘው እንዲወጡ አስገድደዋል፡፡ በዚህም የቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት እንዲስተጓጎል፣ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ የመናፍቃንና የሙስሊም አባላት በልማት አስመስለው በሆታና በጫጫታ በመረበሽ ካህናቱ ተደማምጠው ቃለ እግዚአብሔሩን እንዳያደርሱ ማወክ፤
- «የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ቦታ ይዛ ሌላው በጠባብ መቸገር የለበትም» በማለት የቤተ ክርስቲያኑን አጥር አስፈርሰው መስጊድ እንዲሠራ መፍቀድ
- አንድ ሙስሊም ሚልሻ የካህኑን ሚስት ከማሳ ላይ ይዞ «ባልሽ ያለበትን ቦታ አሳይኝ» ብሎ በማስገደድ ካህኑ በዐቢይ ጾም በቤተ መቅደስ በውሎ ቅዳሴ በማገልገል ላይ እያሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ ካህኑን በመስኮት በኩል ባለቤታቸውን እያሳየ ማሣቀቅ፤
- በወረዳ አስተዳደሩ መመሪያ የቀበሌ ሥራ አመራር አባላት፣ በዐቢይ ጾም ወቅት ካህኑን አስገድደው ለስብሰባ ወስደው በቅዳሴ ሰዓት አትሄድም ብለው ከቅዳሴ ማስቀረትና አገልግሎቱን ማስታጎል፤
- ምእመናን አባቶች በእርሻ ላይ እያሉ ፖሊሶች፣ «እዚህ አካባቢ የኦርቶዶክስ ቤተ እምነት የት ነው፤ አሳየን?» ሲሉ «እኔ አላውቅም» ሲሏቸው እርሻቸው ከመኖርያ ቤታቸው አጠገብ ነበርና አንበርክከው በዱላ ደብድበዋቸዋል፡፡ ለኻያ ደቂቃ ወደ ፀሐይ አንጋጥጠው እንዲያዩ አድርገዋቸዋል፡፡ ይህን አይተው የተደናገጡት ባለቤታቸው ምርር ብለው እያለቀሱ ወዲያውኑ ታመው ሰውዬው በተደበደቡ በሦስተኛው ቀን ሕይወታቸው አልፏል፡፡
- የቀበሌ ገበሬ ማኅበር ሚልሻዎች ፣ በመጋቢት 27 ቀን 1996 ዓ/ም ክብረ በዓል ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በመግባት፣ «ታቦት ለማክበርና ለማንገሥ ቄሶች ይበቃሉ፤ ሕዝቡ ግን ወደ ስብሰባ ይሂድ» በማለት ሕዝቡን አስገድደው ወስደው ክብረ በዓሉ በካህናት ብቻ ውሏል፡፡

በጊምቢ ከተማ ውስጥ በአራት ዓመት ውስጥ ሦስት መስጊዶች ያለፈቃድ ሲሠሩ፣ የሕዝብና የመንግሥት ጎተራ ላይ የፕሮቴስታንት አዳራሽ ሲሠራ በዝምታ ያለፉ የመንግሥት አካላት በከተማው ውስጥ የግለሰብ ቦታ አግኝተን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ስንጠይቅ «ቤተ ክርስቲያናችሁ በመንግሥት ለመታወቋ በዘንድሮው ዓመት ያሳደሰችውን የዕውቅና ወረቀት/ደብዳቤ አምጡ» በማለት የ3000 ዓመት ባለታሪኳን ቤተ ክርስቲያን መድፈር

ጊምቢ ደብረ ፀሐይ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ለልማት ሠርቶ ከሚያከራያቸው ሕንጻዎች የመንግሥት ግብር ክፈሉ ማለት፤ ይህ ሁሉ በተለያዩ የእምነት ድርጅቶች ተከታይ የመንግሥት አመራር አባላት መመሪያ ሰጭነት በቤተ ክርስቲያኗ ላይ የሚፈጸምየግፍ ግፍ ነው፤ በዚህም ሀገረ ስብከቱ በሐሳብ፣ በጉልበት፣ በኢኮኖሚ ከፍተኛ እንግልት እየደረሰበት መኾኑ በሪፖርቱ ተጠቅሷል።



ያጋጠሙን ችግሮች

ስዕል 2፡ በ32ኛው የጠቅላላሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ የምዕራብ ወለጋ ሀ/ስብከት የቀረበ ሪፖርት

### 5.3.6 አዳማ

በቀን የካቲት 24 ቀን 2007 በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊበን ዝቋላ ወረዳ አዱላላ ከተማ በሚገኘው የዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ዙሪያ የእሳት ቃጠሎ መቀስቀሱን የገዳሙ መነኰሳት አሳወቀው ነበር ፡፡ ከጠዋቱ 2፡00 ገደማ የተቀሰቀሰው የእሳት ቃጠሎ የጀመረው ወንበር ማርያም እየተባለ በሚጠራው በገዳሙ ሰሜናዊ አቅጣጫ ነበር፡፡ የቃጠሎው መንስኤ በውል ባይታወቅም እሳቱ በአካባቢው ተቀስቅሶ በነበረው ኃይለኛ ነፋስ ወደ ገዳሙ መውጫና በገዳሙ ዙሪያ ተስፋፍቶ ነበር። በጥንታዊውና ታሪካዊው ገዳም ዙሪያ የእሳት ቃጠሎ ሲደርስ የአኹኑ የመጀመሪያ አይደለም፡፡ መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም. በደረሰው የእሳት ቃጠሎ እንደ አርዘ ሊባኖስና የሐበሻ ጥድ ያሉት አገር በቀል ዛፎች በስፋት ወድመዋል፡፡ መጋቢት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. የተቀሰቀሰው ቃጠሎ ደግሞ ተኣምራዊና ግራ አጋቢ ጠባይዕ የታየበት ነበር፡፡ በምሥራቃዊ አቅጣጫ በሚገኘው የመንግሥት ደን ውስጥ ተከሥቶ በአንድ በኩል ኃይሉ ሲቀንስ በሌላ አቅጣጫ እየተዛመተ ገዳሙን ጨርሶ ለማጥፋት በተቃረበበት ሁኔታ ከአዲስ አበባ፣ ከቢሾፍቱና ከአዳማ በፍጥነት ከቦታው በደረሱ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ በጎ አድራጊ ምእመናን እንዲሁም በመከላከያ ሠራዊትና በፖሊስ እገዛ መገታቱ የሚታወስ ነው፡፡



ስዕል 3፡ 24/06/2007 በዝቋላ ደብረ ከዋከብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ዙሪያ ተከስቶ የነበረውን እሳት ቃጠሎ የሚያሳይ

በተጨማሪም በገዳሙ ጠበል የኢሬቻን በዓል ለማክበርና በደብረ ከዋክብት ዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የአባ ገዳ ሐውልት ለመትከል በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ መታቀዱንና በመንግሥት ብዙኃን መገናኛ መገለጹን ተከትሎ ቤተ ክርስቲያናችን በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በኩል ለክልሉ ርእሰ መስተዳድር በጻፈችው ደብዳቤ ተቃውሞዋን አሰምታልች፡፡


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ [illegible]ኖዶስ ጽ/ቤት
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
HOLY SYNOD SECRETARIATE

ቁጥር 15/1[illegible]
ቀን 5 [illegible] 2007

ለክቡር አ[illegible] [illegible]ክታር ከድር
የኦሮሚያ [illegible]ልላዊ መንግሥት ርእሰ መስተዳድር
አዲስ [illegible]

ጉዳዩ፡- ጥንታዊውንና ታሪካዊውን የዝቋላ ገዳምና ገዳማውያን መነኮሳትን አቤቱታ የሚመለከት ይሆናል።

[illegible] በተጠቀሰው በኢትዮጵያ ካሉት ጥንታውያንና ታሪካውያን ገዳማት [illegible] በሆነው [illegible] ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ላይ የእሬቻ በዓ[illegible] እንደሚ[illegible] በመንግሥት ሚድያ በኦሮምኛና በአማርኛ ቋንቋ መተላለፉን በመግለ[illegible] ሁኔታው [illegible] አቅጣጫ እንዳያመራ በመንግሥት በኩል ተገቢው ሕጋዊ መመሪ[illegible] ለ[illegible] እንዲሰጥ ይደረግ ዘንድ ማሳሰቢያ እንድንጽፍልዎ በገዳማውያ[illegible] መነኮሳ[illegible] ሕዝበ ክርስቲያን እየታዩ ያለውን አስጊ የሆነ ችግር በመግለ[illegible] የም[illegible] ሀገረ ስብከት ሰፊ ዘገባ አቅርቦልናል።

የተከበሩ ርእሰ መስተዳድር

[illegible] እኩልነት በታወጀበት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪ[illegible] ሕገ [illegible] አንዱ ቤተ እምነት የሌላውን ቤተ እምነት መንቀፍም ሆነ [illegible] እንደሌ[illegible] ተደንግጓል።

[illegible] ሕገ መንግሥቱን በመተላለፍ በመንፈሳዊ አገልግሎታቸውና በ[illegible]ህርታቸ[illegible] ለሀገር [illegible] ሰላማዊ መረጋጋትን እያስገኙ ያሉ መናንያን መነኮሳትና በአካ[illegible]ው የሚ[illegible] ሕዝበ [illegible] ለማስቆጣት የእሬቻ በዓል በዝቋላ ገዳም እንደሚካሄ[illegible] በመንግ[illegible] ሚዲያ [illegible] ማስተላለፉ ተገቢ ስለአልሆነ ችግሩ ከመፈጠሩ በ[illegible] በተገለጸበ[illegible] የመንግ[illegible] ማረሚያ እንዲተላለፍ ያደርጉልን ዘንድ በአክብሮት እና[illegible]ለን።

እግዚአብሔር ኢ[illegible]ያን ይባ[illegible]

አባ ማ[illegible]
ርእሰ ሊ[illegible]
ፓትርያርክ ዘ[illegible]
Patriarch of Ethio[illegible]
of Axum & Ech[illegible]
St. Tekle Haim[illegible]

ግልባጭ
ለኢትዮጵያ [illegible]ራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል [illegible] ሚኒስቴር
አዲስ አበባ
ለምሥራ[illegible] ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት
ናዝሬት
ለዝቋላ [illegible] አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም
ዝቋላ

ስዕል 4፡ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አባ ማትያስ ለኦሮሚያ ክልል ፕሬዳንት ለነበሩት ለአቶ ሙክታር ከድር የገዳማውያኑን አቤቱታ በተመለከተ የተጻፈ ደብዳቤ

### 5.3.7 ሥልጤ ዞን

በስልጤ ዞን የምሥራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ክርስቲያኖች በአክራሪ ሙስሊሞች በሚደርስባቸው ጫና ግንቦት 02 ቀን 2007 ዓ.ም የድረሱልን ጥሪ አሰምተው ነበር፡፡ ጽንፈኛ ባለሥልጣናት የሚፈጥሙት በደል በመክፋቱ "ወረዳው ሊቢያ ሆኖብናል" በማለት እየደረሰባቸው ያለውን በደል አሳውቀዋል። የወረዳ ፖሊስ የቂልጦ ጎምሮ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያለአግባብ ባሰራቸው ጊዜ "የድረሱልኝ ጥሪ" አሰምተው ነበር። "ሃይማኖትን ከሃይማኖት የሚያጋጭ ጽሑፍ ጽፈው በፌስቡክ አሰራጭተዋል" ሲል ፖሊስ ለፍርድ ቤቱ አስረድቷል፡፡ የሰበካ ጉባኤው ሊቃነ መናብርት "የድረሱልኝ ጥሪ" በሚል ደብዳቤ መጻፋቸውን ቢያምኑም በፌስቡክ አለመልቀቃቸውን ለፍርድ ቤቱ ገልጸዋል፡፡ ፖሊስ በቍጥጥር ሥር በዋሉት ምእመናን ላይ የማጣራው ነገር አለ በሚል የኻያ አንድ ቀን የምርመራ ጊዜ የጠየቀባቸው ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የዐሥር ቀን ጊዜ ቀጠሮ ፈቅዶለታል፡፡ ስድስት የቂልጦ ቅድስት ማርያም ሰበካ ጉባኤ እና የሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ አሠሪ ኮሚቴ ምእመናኑ መካከል በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የሚገኙት ስድስት አባላት፣ ሊቀ መንበሩ መ/ር የማርያም ወርቅ ተሻገር፣ መምህር ሀብታሙ ተካ፣ አቶ ሙሉጌታ አራጋው፣ ወይዘሪት ንጋት ለማ፣ አቶ ማስረሻ ሰይፈ እና አቶ ማሩ ለማ የሚባሉ ሲሆኑ በወረዳው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ የፖሊስ፣ የጤና እና የግብርና ጽሕፈት ቤቶች እንዲሁም የባንክ ቅርንጫፍ ሠራተኞች ናቸው፡፡

"የድረሱልኝ ጥሪ" በሚል ርእስ የተሰራጨው እና የደብሩን የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ማኅተም የያዘው ጽሑፍ፥ በስልጤ ዞን በምሥራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፣ በሃይማኖታዊ ማንነታቸው ላይ በአክራሪነት አስተሳሰብ የተወጠሩ ባለሥልጣናት ይፈጽሙብናል ባሏቸው ግፎች መማረራቸውን፣ የአምልኮ ነጻነታቸው እና ሠርተው የመኖር ዋስትናቸውም አደጋ ላይ መውደቁን ያስረዳል፡፡ኢትዮጵያ የሃይማኖት እኩልነት የተረጋገጠባት መኾኗን የገለጹት ምእመናኑ፣ ስለሚፈጸምባቸው ግፍ እና ሥቃይ ለወረዳው የፖሊስ እና የሕግ አካላት በየደረጃው ቢያመለክቱም የአስተዳደሩ መዋቅሩ እና አሠራሩ ያልተገባ "ሕጋዊ ሽፋን" በመስጠቱ የጥቃቱ ስልት ዐይነት እየጠነከረ መጣ እንጂ መፍትሔ አለማግኘታቸውን ተናግረዋል፡፡ በየቤታችን እና በሥራ ቦታዎች እየደረሰብን ነው ያሉት እስር፣ እንግልት፣ ዛቻ፣ በሥራ ቦታ ከሓላፊነት መነሣት፣ ከደረጃ ዝቅ መደረግ፣ መታገድ እና መባረር እየተጠናከረ መምጣቱን የገለጹት ምእምኑ፣ ድርጊቱ የተባባሰው፤ የቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ቦታ ተረክበው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የመሠረት ድንጋይ ካስቀመጡበት ከጥቅምት 24 ቀን 2007 ዓ/ም ወዲኽ መኾኑን ገልጸዋል፡፡ለመንግሥት እና ለቤተ ክህነት አካላት አቤቱታቸውን ያሰሙበት "የድረሱልኝ ጥሪ" የሚለው ይኸው ጽሑፍ፣ የሀገረ ስብከቱን ፈቃድ በመጠየቅ የተዘጋጀ እንደኾነ የገለጹት ምእመናኑ አክራሪነት በተጠናወታቸው አንዳንድ ባለሥልጣናት የሚደርስባቸውን ሥቃይ በመዘርዘር መፍትሔ የጠየቁበት እንደኾነ ጠቁመው፤ "ታምኑበታላችኹ ወይስ አታምኑበትም" እየተባለ ሃይማኖታዊ ግጭት እንደቀሰቀስን እና የወረዳውን ስም እንዳጠፋን ተደርገን መታየታችን አሳዝኖናል ሲሉ ርምጃውን ተቃውመዋል፡፡ ታሳሪዎቹ በየሞያቸው የተመሰገኑና በምግባራቸው የተወደዱ የመከባበር እና የፍቅር ተምሳሌት መኾናቸውንም ጠቅሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሀድያና ስልጤ ሀ/ስብከት በምሥራቅ አዘርነት
በርበሬ ወረዳ የቂልጦ ጎጥር ቅ/ማርያም
ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት

ለ ..........................................................................

ቁጥር ፡ ቁ/ገ/ቅ/ማ/42/07

ቀን ፡ 02/09/07

## የድረሱልኝ ጥሪ !

በስልጤ ዞን ምስራቅ አዘርነት ወረዳ የምንኖር የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች አደጋ ላይ ነን እና ድረሱልን እንላለን ። ነገሩ እንዲህ ነው ! በስልጤ ዞን ስምንት ወረዳዎች ይገኛሉ በሰባቱም ወረዳዎች በእያንዳንዱ ወረዳ በአማካይ አንድ ቤተክርስቲያን ይገኛል እኛ በምንገኝበት ቂልጡ ወረዳ ግን ጥንት የነበረው ቤተክርስቲያን በመቃጠሉ ምክንያት ለብዙ አመታት ምዕመናን የሚያስቀድሱበትና የሚቀበሩበት ባለመኖሩ ከፍተኛ ችግር ሲደርስብን መኖሩ የሚታወቅ ነው ።ከ2004 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ባደረግነው ውጣውረድ ከብዙ መከራና እንግልት እንዲሁም ከሥራ መባረርና የግድያ ዛቻ ልዩ ልዩ ፈተናዎች በእግዚአብሔር ቸርነትና እርዳታ በተለይም በአባቶቻችን ትዕግስትና ጥረት በምዕመናን ያላሰለሰ ጸሎትና ጥረት ጥቅምት 24 ቀን 2007 ዓ.ም ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ የሚሆን ቦታ ተረክበን ለዚህ ቀዱስ አላማ የረዳንን አምላካችንን እግዚአብሔርን እያመሰገን መንግስትም ላደረገልን በጎ ምላሽ ሁሉ ምስጋናችንን እየገለጽንበት ባለበትጊዜና ለዚሁ ደስታ መግለጫ በብፁዕ አቡነ ቀለሜንጦስ የሀገረስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ስም የሀገረስብከቱ ሥራ አሥኪያጅ የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠዋል ።በበዓሉ ላይም ከተለያ ዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ2500 በላይ የሆኑ ምዕመናን በ20 አውቶብሶችና የግል መኪኖች በመምጣት በዓሉን አክብረዋል ። እኛም ሆንን በበዓሉ የተገኙ ማዕመናን ደስታችንን አጣጥመን ሳንጨርስ «ጆሮ ጭው ' የሚያደርግ አስደንጋጭ አደጋ በላያችን ተከሰተ ።

በቀን 27/02/2007 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያኑ ኮሚቴዎች የሚኖሩበትን ግቢና ቤት በግምት ከምሽቱ 3፡00 አካባቢ ማንነታቸው ለጊዜው ባልታወቁ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በሁለት ሃይላንድ በንዚን በማርከፍከፍ ቤቱን ባላያችን በማቃጠል ሥጋችን በእሳት ነፍሳችንን ለጥፋት በመመኘት ሀገር ሰላም ብለን በተኛንበት ምሽት አነደዱን ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ለጊዜው ከአደጋው ልንተርፍ ችለናል ። ለፖሊስ እና ለህግ አካላት በየደረጃው ብናመለክትም የጥቃቱ ሥልትና ዓይነት እየጠነከረ መጣ እንጂ ምንም መፍትሔ እስካሁን አልተገኘለትም ።

ይህንን ጥፋት በህጋዊ አፈታት መፍትሔ ማግኘት ባለመቻሉ የተበረታታው የጥፋት ኃይል በድርጊቱ እየገፋበት ይገኛል ።ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በተመሳሳይ የጥፋት ድርጊት ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ የተዘጋጀውን እንጨት በማዘናጋት በግምት ከምሽቱ 5፡00 አካባቢ በድጋሚ ሁለት ሃይላንድ ቤንዚን በማርከፍከፍ አካባቢውን ለማውደም የተደረገው ጥረት አሁንም ሦስቱን ወጣቶች ከእቶን እሳት ያደነ እግዚአብሔር ሲታደገን ቻለ እንጂ መከራው እንደቀጠለ ነው። የወረዳው አስተዳደርና ልዩ ለዩ አደረጃጀቶች ይህ ሁሉ ግፍና ሠቃይ እየተፈጸመብን እየተመለከቱ በስብሰባና በውይይት ስም ነገሮችን በማድበስበስ የተጠናከረ ምርመራ እርምት ባለመውሰዳቸው ከዞን በመጡ ከፍተኛ የሕግ አካላት ለጠቀሳ ቢደርጋቸውም ምንም መፍትሔ አላገኘንም ። የወረዳው አስተዳደርና የህግ አካላት ችግሩን ከመፍታት ይልቅ በቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉና በኮሚቴነት የሚገኙ አባላትን በተናጠል በማይመለከታቸው ጉዳይ ሁሉ ተጠያቂ በማድረግ በመንገስት መዋቀር አሠራር በመግባት ያልተገባ ህጋዊነት ሽፋን በመስጠት በማባረርና በመቅጣት በማሳደድ ላይ ይገኛል ።

3. መጋቢ ስርዓት አንዳርጌ ደጀኔ እና ቀሲስ ሙሉ ጌታ በተገኙበት ወቅት አስተዳዳሪዉ በመራዉ ስብሰባ ወ/ሪት ንጋት ለማ ሶስት ጊዜ በእሳት ስንቃጠል አንተ የት ነበርክ የመጀመሪያዉ ተጠያቂ አንተ ነህ ብላ በስብሰባዉ በመናገሯ ጭንቅላቷ እንዲዶለዱም 24 ሰዓት ስራ የሌለበት የት/ት ደረጃዋን፣ የስራ ልምዷን ያላገናዘበ ቦታ በበቀል ማስቀመጥ፡፡
4. ወ/ሪት ምህረት ኃ/ስላሴ በፖሊስ ጽ/ቤት የምትሰራ የኮሚቴያችን አባል ሰትሆን ቤ/ኗ በተቃጠለች ማግስት እዚያዉ መስሪያ ቤት በምትሰራ ሴት ቤ/ኗ አሁኑ መቃጠሉ አይድነቅሽ ገና ይነዳል ስትል ሰምታ በመቃወሟ እና ፖሊስ ጽ/ቤት ላይ ቁራን ሲቀራ ተገቢ አይደለም ብላ በመናገሯ በፋሲካ ማግስት ከስራ ተባራለች።
5. በቂልጦ 2ኛ ደረጃ መሰናዶ ት/ቤት የICT መምህር የሆነዉና የኮሚቴያችን አባል መምህር ጠብቀዉ ከበደ በሚያደርጉት ግፍና አድሎኝነት ተማሮ ከስራ ለቆ ሂዷል።
6. ወ/ሪት ማዕዛ እንዳለ በግብረና ሙያ የተሰማራች ሲሆን የፋሲካን በዓል ሁለት ቀን አሳልፈሽ መጣሽ በሚል ሰበብ ከስራ እንድትለቅና ስሜታዊ እንድትሆንና መገፋፋትና ማሰቃየት።
7. ቂልጦ 2ኛ ደረጃ መሰናዶ ት/ቤት አብዛኛዉ የቤ/ኗ መሪና አመራሮች የሚገኙበት ስፍራ ሲሆን በዚህም ወረዳዉ በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ አስተዳዳሪ ሽፋን በመስጠት ት/ቤት ዉስጥ ለአይን የሚቀፉ፣ ለጆሮ የሚዘገንኑ፣ አስቀያሚ ድርጊቶች ሲከሰቱ በግዴለሽነት በመመልከት ለጥፋት ኃይሎች አቅጣጫ በመስጠት በተቋሙ ዉስጥ የሚገኙትን ምዕመናንና አመራሮች ከሌሎች የት/ቤት ሰራተኞች ጋር እንዲጋጩ ክፍተት በመስጠት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።የዚህም መገለጫዎ የሚከተሉት ናቸዉ
8. ከት/ቤት ዉጭ የተደረገን ጥል በእንግዳ ወርቅና በመ/ር አዲሱ በኩል ያለን ጉዳይ ት/ቤት ዉስጥ በማስገባት ዲሲፕሊን ብለዉ ማሰቃየት፣ ት/ቤት ስብሰባ ላይ የተሰነዘረን አሰተያየት በመ/ር ከሊል አማካኝነት ፖሊስ ጣቢያ እንዲከሰሱ ማድረግ የለየለት ዉዥብር እና ስቃይ በክርስቲያኖች ላይ ማድረስ።
9. የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ሁለት መምህራንን መምህር ደስታዉ በላይና መምህር ታደለ የኔነህ ት/ቤቱ ሌሎች ቡድኖችን በማደራጀት ለድብደበ መጋበዝ በገላጋይ መትረፋቸዉ።ይህንንም የት/ቤቱ አመራር በቦታዉ እያዩ ወደ ዉጭ

እናዳይወጣ የዉስጥ ጉዳይ ነዉ በሚል ማስፈራሪያ ችግሩ እንዲፈታ ሳይሆን እንዲባባስ ምክንያት መሆናቸዉ።

10. 12ኛ ክፍል ላይ ማንነታቸዉ ባልታወቁ የት/ቤቱ ማህበረሰብ አካላት በተፃፈ መምህር የማርያም ወርቅ ተሻገርና መምህር ታደለ የኔነህ ፈታችሁን ማየት አስጠላን .... የመጡት ለልዩ አላማ ነዉ በሚል የሽብርና የነፍስ ማጥፋት አዝማሚያ የታየበት የጭፍጨፋና የእልቂት ዘመቻ የተካሄደባቸዉ መሆኑ ይህንንም የት/ቤቱ አመራርም ሆነ የወረዳዉ አስተዳደር ጉዳዩን እያወቀ ፀጥ ማለቱ መምህራን ነገ ላለመታረዳቸዉ፣ ላለመገደላቸዉ ዋስትና ያሳሰባቸዉ መሆኑ እና በእያንዳንዱን ቀን በሰቀቀን እንዲገፉ ማድረጋቸዉ። በግልጽ የታየ መሆኑ።

11. ይባስ ብሎ ግዙፍ የዲሲፕሊን ችግር ያለበት ብሄርን ከብሄር ሀይማኖትን ከሀይማኖት በማጋጨት ት/ቤቱን በማበጣበጥ የሚታወቀዉ ... ዛሬ ደግሞ ለእኩይ ድርጊታቸዉ ማስፈጸሚያ የመምህራንን ማህበር ሰብሳቢ፣ በጉልበት የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሰብሳቢ በአመራሩ የግል ፈቃድ አድርገዉ በመረጡት በመ/ር ላቀዉ ወ/ሚካኤል ህገ ወጥ ስብሰባ ላይ መምህር እራጌ የተባለ ሙስሊም መ/ር ህዝቡ ዝናብ እንዲመጣለት ሳይሆን የሚጸልዩ የቤ/ኗ መሪ የማርያም ወርቅ ተሻገር ላይ ነዉ የሚጸለየዉ ብሎ ሲናገር በገሀድ (ጅሃድ የታወጀብን መሆኑ) ከማሳየቱም በላይ፣

12. መ/ር ከበደ የተባለ ሰዉ የካቲት 8/07 ዓም ምሽት 3፡00 ሰዓት አቶ ማስረሻ ሰይፌ፣ መ/ር ደስታዉ ባላይ፣ መ/ር የማርያም ወርቅ ለተባሉ የቤ/ኗን አመራር ለመ/ር የማርያም ወርቅ ቦርኮ እንደተመደበ ለዚህም ተጠንቅቆ እንዲጓዝ ከታማኝ ምንጮች አገኘሁት ያለዉን መረጃ የወረዳዉ አስተዳዳሪ እያወቀ ጉዳዩን አጣርቶ የሽብሩንና የአክራሪነቱን መረብ መበጣጠስ ሲገባዉ ችግሩ ሌላ ችግር እንዲወልድ ጊዜ በመስጠት ትዉልድ ሊያልቅ ሲቀርብ አንድ ሌሊት እስኪፈጅ ዝም ብሎ መመልከቱ፣

13. አሁንም እታሳደዉ እንዲሰደድ አድርገዉ የሚለዉን መርህ በመጠቀም አራት ዓመት ሙሉ ከቤ/ን አባቶች ከምዕመናን ከመንግስት አካላት ጋር ፊት በመቆም ቤ/ኗን በሰብሳቢነት የሚመራዉን መ/ር የማርያም ወርቅን እንድ መምህር ለተማሪዉ እንደሚያደርገዉ የአባትና የልጅ ግንኙነት ልጅቱ ትዳር ይዛ ወደ አ/አ የሚሄዱን አጋጣሚ ተጠቅመዉ ከልጅቱ ጋር ያልተገባ ግንኙነት ነበረህ የሚል ዉሃ የ[illegible]ና ተልካሻ ምክንያት በመጥቀስ ልጅቱ ተበደልኩ ብላ ሳትከስ የጽ/ቤቱ

ማኔጅመንትና ወረዳዉ በጋራ በመቀናጀት የቂም በቀል ጦራቸዉን የሶስት ወር ደመወዝ በመቅጣት ያላቸዉ ኃላፊነት የማይሰማቸዉ ድሃን ለመበደል፣ ህዝብ ለማሰቃየት የተቀመጡ እንባገነን መሆናቸዉን በአደባባይ አስመስክረዋል።

ይህሉ የሚሆነዉ ግን ሰላሳ ወንድሞቻችን በግፍ በታረዱበት ሊቢያ አይደለም፣ ይህ የሚሆነዉ ግን ወገኖቻችን ያርህራሄ በሚሰቃዩባት ደቡብ አፍሪካ፣ የመን አይደለም። በለምለሚቱ ምድር የመከባበርና የመቻቻል ሙዳይ የፍቅር ተምሳሌት ኢትዮጵያ ነዉ። ይህ ጽሁፍ የደረሳችሁ ወገኖቻችን የመንግስት መ/ቤቶ፣ አመራሮች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ጋዜጠኞች፣ ለሊቢያ ወንድሞቻችን ብቻ አይደለም ለኛም አልቅሱ።እነሱ ከሀገር ወጥተዉ ተሰደዉ ነዉ እኛ ግን በሀገራችን ከአ/አ 220 ኪ/ሜ ርቀት ኢትዮጵያ።ፍጹም መሮናል፣ ተሰቃይተናል፣ በጭንቀትና በስጋት ላይ ነን።መቼ ምን እንደምንሆን አናዉቅም ድረሱልን እንላለን።

//ከሰላምታ ጋር//

<u>ግልባጭ</u>

- ለምሰ/አዘ/በ/ወ/አስተዳደር
- ለምሰ/አዘ/በ/ወ/ፀጥታ ጽ/ቤት
- ለምሰ/አዘ/በ/ወ/ሲ/ሰርቪስ
- ለምሰ/አዘ/በ/ወ/ፖሊስ
- ለምሰ/አዘ/በ/ወ/ደህዴን

<u>ቂልጦ</u>

- ለስልጤ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት
- ለስልጤ ዞን ፀጥታ መምሪያ
- ለስልጤ ዞን ሲ/ሰርቪስ መምሪያ
- ለስልጤ ዞን ፖሊስ መምሪያ
- ለስልጤ ዞን ደህዴን ጽ/ቤት

<u>ወራቤ</u>

- ✓ ለደ/ቡ/ብ/ህ/ክ/መ/ አስተዳደር ቢሮ
- ✓ ለደ/ቡ/ብ/ህ/ክ/መ/ ሰባዊ መብት ኮሚሽን ቢሮ
- ✓ ለደ/ቡ/ብ/ህ/ክ/መ/ ሰባዊ መብት ጉባኤ ቢሮ



- ✓ ለደ/ቡ/ብ/ህ/ክ/መ/ለመገናኛ ብዙሃን

<u>ሀዋሳ</u>

- ➢ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ➢ ለመ/ኮ/ጉ/ሚ/ጽ/ቤት
- ➢ ለኢ.ትዩጵያ ፕሮድ ካስትግ ኮርኮሬት
- ➢ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
- ➢ ለሲ/ሰርቪስ ሚኒስቴር
- ➢ ለኢ.ሀዴግ ጽ/ቤት
- ➢ ለደህንነት ሚኒስቴር
- ➢ ለኢ./ሰባዊ መብት ኮሚሽን
- ➢ ለኢ./ሰባዊ መብት ጉባኤ
- ➢ ለሀገር ዉስጥና ለዉጭ መገናኛ ብዙሃን
- ➢ ለእንባ ጠባቂ ተቋም
- ➢ ለመንበረ ፓትሪያሪክ ጽ/ቤት

<u>አ/አ</u>

- ➢ ለስልጤ ወረዳ ቤ/ክህነት

<u>ዳሎቻ</u>

- ➢ ለሀድያና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

<u>ሆሳዕና</u>

- ➢ በጽ/ ቤታችን

<u>ቂልጦ</u>



ስዕል 5፡ በስልጤ ዞን የምሥራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ክርስቲያኖች በአክራሪ ሙስሊሞች በሚደርስባቸው ጫና በመማረር የጻፉት የድረሱልን ጥሪ ደብዳቤ

የ«ድረሱልኝ ጥሪ»ው፤ ከደብሩ ምእመናን፣ ከሰበካ ጉባኤው እና ከሕንፃ አሠሪ ኮሚቴው ዓላማ እና ፍላጎት ውጭ ሐራ ዘተዋሕዶ በተባለው ድረ ገጽ በመለቀቁ ድርጊቱን አውግዘነዋል በማለት የማስተካከያ ደብዳቤ እንዲጽፉ የተደረገ ሲሆን የዘቱን ከታች ባለው ምስል ላይ ያገኙታል፡፡

ቁ/ን/ቅ/ማ/104/07
ቀን 04/11/07

በሀድሮና ከሰ... ስብከት በምሥራቅ አዘርነት
በርበሬ ወረዳ የቂልጦ ጎምሮ ቅ/ማርያም
ቤተ ክርስቲያን ሰበ፡ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት

## ማስተካከያ

ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን ለምስራቅ አዘርናት በርበሬ ወረዳ ቂልጦ ጉመሮ ቅድስት ማርያም ቤ/ያን ስር ያሉ ምዕመናንና የቤ/ክያኗ አመራሮች እምነታችንን መሠረት ያደረገ ደረሰብን ያሉትን በደል በቁጥር ቂ/ጎ/ቅ/ማ/42/07 በቀን 02/09/2007 ዓ/ም ለቤተክህነትና ለመንግስት አካላት የድሩልን ጥሪ በሚል በግልባጭ ማድረሳችን ይታወቃል።

ይሁን እንጅ ችግሩን ለመፍታት የሚመለከተው አካል መጥተው እንዲያዩ በሚል አላማ ምላሽ እንዲሰጥበት ለሚመለከታቸው ባለድርሻአካላት የተዘጋጀው ጽሁፍ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

ነገር ግን ይህ ጽሁፍ ባልታወቀ መንገድ በሀራ ተዋሁዶ በሚል ድህረ-ገጽ ተለቆ ተገኝቷል። ይህም ድርጊት ከደብሩ ኮሚቴ እና ምዕመናን አላማ እና ፍላጎት ውጪ ነው በመሆኑም ጉዳዩ በዚህ መንገድ መበተኑ የቂ/ጎ/ቅ/ማ/ቤ/ያን የሰበካ ጉባኤ አባላት የህንጻ አሰሪ ኮሚቴ እና ማህበረ ምዕመናን በአንድነት አውግዘዋል።

ሆኖም በጽሁፍ ውስጥ የጥንት ቤ/ያን ተቃጥሏል የተባለው ያልተረጋገጠ መሆኑንና የሥልጤ ዞን ምስራቅ አዘርነት ወረዳ ንጹሀን የሀገሪቱ ዜጎች በመቻቻልና በመግባባት በፍቅር የሚኖሩበት ወረዳ ናት በወቅቱ በጽሁፉ ላይ ሊቢያ እንደ ንጽጽር መጠቀማችን ተገቢ አልነበረም ። በመጨረሻም ይህንን ችግር ከስሩ ለማድረቅ የወረዳው አመራሮች የዞን የሀይማኖ ፎረም የዞኑ ከፍተኛ አመራሮች የክልል ከፍተኛ አመራሮች የሀዲያና ስልጤ ሀ/ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የየክፍሉ ሀላፊዎች የሀይማኖት አባቱቶች የሀገር፣ ሽማ ግሌሎች፣ እያደረጉ ባለው ከፍተኛ ጥረት ችግሮችን በመፍታት ይገኛሉ። በዚህም የአጥቢያ ቤ/ያን ምእመናንና የቤ/ክያኗ ሰበካ ጉባኤ እና ህንጻ አሰሪ ኮሚቴ ሁሉም አካላት እያደረገ ላለው ጥረት እያመሰገንን አሁንም በድጋሚ ከደብሩ ምእመናንና ሰበካ ጉባኤ እና ህንጻ አሰሪ ኮሚቴ አላማና ፍላጎት ውጪ ሀራ ዘተዋህዶ በተባለው ድህረ-ገጽ በመለቀቁ ድርጊቱን አውግዘነዋል። በዚህ ይቅርታ እንጠይቃለን ወደፊትም ችግሮች ቢፈጠሩ በጠረጴዛ ዙርያ በጋራ በነጋገር መፍታት እንዲሰብን ከዚህ ድርጊት ተምረናል።

ግልባጭ

- ለምስ/አዘ/በ/ወረዳ አስተዳደር
- ለምስ/አዘ/በ/ወ/ፀጥታ ጽ/ቤት
- ለምስ/አዘ/በ/ወ/ፖሊስ ጽ/ቤት
- ለምስ/አዘ/በ/ወ/ ደህዴን ጽ/ቤት

ቁልጦ

- ለስልጤ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤቶች
- ለስልጤ ዞን ፀጥታ መምሪያ
- ለስልጤ ዞን ሲ/ሰርቪስ መምሪያ
- ለስልጤ ዞን ፖሊስ መምሪያ
- ለስልጤ ዞን ደህዴን ጽ/ቤት

ወራቤ

- ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ አስተዳደር ቢሮ
- ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ቢሮ
- ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ሰብአዊ መብት ጉባኤ ቢሮ
- ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ለመገናኛ ብዙሃን

ሀዋሳ

- ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለመ/ጉ/ሚ/ጽ/ቤት
- ለኢትዮጵያ [illegible]


ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር

ለኢህዴግ ጽ/ቤት

ለደህንነት ሚኒስቴር

ለኢ/ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

ለሀገር ውስጥና ውጭ መገናኛ ብዙሃን

ለሀይማኖት ጉዳዮች

ለጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት

ሃላፊ

ለዞን ጽ/ቤት

ስዕል 6፡ ስዕል 5፡ በስልጤ ዞን ምስራቅ አዘርነት ወረዳ የሚገኙ ምእመናን የላኩት የደረሱልን ላይ የተደረገ ማስተካከያ ደብዳቤ ቅጂ

### 5.3.8 ቡሌ ሆራ ወረዳ ገርባ ከተማ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ወረዳ ገርባ ከተማ፣ ከፋሲካ እርድ ጋር በተያያዘ በቡድን ተደራጅታችሁ ሁከት ፈጥራችኋል በሚል የታሰሩ ከኻያ ያላነሱ ሰዎች ፍርድ ቤት ቀርበው በነፃ እና በዋስ ተለቀዋል፡፡ በጾም ወቅት የከተማዋ ሥጋ ቤቶች እንዳይዘጉ ሲከላከሉ ነበር በተባሉ ግለሰቦች ስጋት ተፈጥሮ መቆየቱን የተናገሩት የከተማዋ ነዋሪዎች በጾሙ ተዘግቶ ለፋሲካው በተከፈተ ሥጋ ቤት ደግሞ ሕገ ወጥ እርድ ተካሒዷል በሚል ሁከቱ መቀስቀሱ ተገልጧል። በተፈጠረው ሁከቱ በሉካንዳ ቤቱ ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ባለቤቱን ጨምሮ የታረደውን ከብት ቆዳእና ሥጋ ገዝተዋል የተባሉ ሰዎች በማዘጋጃ ቤቱ ታስረው መዋላቸው ተገልጧል፡፡ በበዓሉ ማግሥት የሥጋ ቤቱ ባለቤት ይቅርታ ጠይቆ የከብቱ ሥጋ ከተወገደ በኋላ ሉካንዳው ሥራውን ቀጥሎ የዋለ ሲኾን፤ ከቀትር በኋላም የከተማው አስተዳደር ሓላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች በተገኙበት በጉዳዩ የምክክር ስብሰባ መካሔዱ ተጠቅሷል፡፡

ስብሰባው በምሽት እንደተጠናቀቀ ማንነታቸው ያልታወቁ ግለሰቦች የወረዳውን ሊቀ ካህናት፣ በከተማው የሚገኘውን የገርባ ደብረ ሰላም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እና የሰበካ ጉባኤ አባላትን መኖርያ ቤቶች በድንጋይ እየለዩ በመደብደብ ጉዳት አድርሰዋል። የከተማዋ ፖሊስ ሁኔታውን በተኩስ ለመቆጣጠር ጥረት እያደረገ በነበረበትም ወቅት፣ ግለሰቦቹ የቤተ ክርስቲያኑን ክልል በመክበባቸው እና ደወልም በመሰማቱ ሁከቱ መባባሱ ተገልጧል። ፖሊስ፥ በቡድን ተደራጅተው ሁከት ፈጥረዋል በሚል፣ በሰሙት ደወል ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመከላከል በምሽት ከየቤታቸው የወጡ በርካታ ምእመናንን አስሯል፡፡ የታሰሩት ምእመናን ማክሰኞ እና ኃሙስ በቡሌ ሆራ ፍ/ቤት የቀረቡ ሲሆን፤ በቂ መረጃ አላገኘኹባቸውም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በነፃ እና በዋስ እንዲለቀቁ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ የደረሱ ጥቃቶች

- በአንዳንድ ባለሥልጣናት ግፊትና በተደራጀ ኃይል የጥላቻ ቅስቀሳ ተካሔዷል።
- ጭምብል አጥልቆ፣ ገጀራ እና ጦር ይዞ ካህናትንና ምእመናንን እየመረጡ አጥቅተዋል።
- መኖርያ እና የንግድ ቤቶቻቸውን እየለየ በድንጋይ ደብድበዋል፤ ዝርፊያም ፈጽመዋል።
- በጾም ወቅት ክርስቲያኖች ሥጋ ቤቶችን እንዲከፍቱ፣ የሚዘጉ ካሉ ጾም ሲፈታ እንዳይሠሩ ይከለክላሉ።
- ጥንታዊውን የገርባ ደብረ ሰላም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጉዳት ደርሶበታል።
- ደወል በማሰማት በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ጉዳጥ እንዳይደርስ የተከላከሉ ምእመናን ሁከት ፈጠራችሁ ተብለው ታስረዋል።
- ምእመናን ተጎጅም ተከሣሽም በመደረጋቸው የሀገር ሽማግሌዎች በስብሰባ ላይ ተቃውመዋል
- ወረዳው ለምእመናኑ የደኅንነት ስጋት የሆኑ ተግባራትን አይፈጽምም፣ ዞኑ ለሚጠይቀው ጥያቄ የሚሰጠው ምላሽ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው።
- በአንድ በኩል ያለው "ጸጥታ ኃይል" አነስተኛ መሆኑን ይገለልጣል፤ ዞኑ ሲጠይቀው ግን ወረዳው "ሰላም" መሆኑን ይናገራል።



*ሥዕል 7፡ ሁከቱ ተፈጥሮ በነበረበት ወቅት ተሰብስበው የነበሩ ወጣቶች*



*ሥዕል 8 ሁከቱ ተፈጥሮ በነበረበት ወቅት የተገኙ የጸጥታ ሃይል*

### 5.3.9 በጅማና አካባቢው

ሰኔ 8 ቀን 2008 ዓ.ም. በጅማ የም ልዩ ወረዳ ቁንቢ ቀበሌ ከሚገኘው በቁንቢ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ማለዳ በአክራሪ ሙስሊሞች ጥቃት ተፈጽሞበታል። የቁንቢ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኝባት የም ልዩ ወረዳ፣ በሰኩሩ እና ናትሪን መካከል ያለችና አነስተኛ

ቁጥር ያላቸው ምእመናን ሲሆኑ የሚበዙት የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። በዕለቱ የኪዳን ጸሎት አድርሰው በሚመለሱ ክርስቲያኖች ላይ ጥቃቱ ደርሶባቸዋል። ፊታቸውን የሸፈኑ አራት አክራሪዎች በመኪና እንደ ደረሱ ወ ደአንድ መስጊድ በመግባት ጥቃታቸውን የጀመሩ ሲሆን ያገኙትን ሰው በስለት አቁሰለዋቸዋል፡፡

ከመስጊዱ እንደወጡ ወደ ቁንቢ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በማምራት የኪዳን ጸሎት አድርሰው በመመለስ ላይ በነበሩ ምእመናን ላይ በቀጠሉት ጥቃት ሁለት ምእመናንን ክፉኛ አቁስለዋል። ከቆሰሉት ምእመናን መካከል የአንዷ እጅ ተቆርጧል። ከጥቃት አድራሾች ሦስቱ በመጡበት መኪና ከአካባቢው በመሰወር ያመለጡ ሲሆን፣ አንዱ በቁጥጥር ሥር መዋሉ ታውቋል። ሦስት ጉዳተኞች በወሊሶ ሆስፒታል በሕክምና ላይ የተረዱ ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ፣ በአክራሪ ሙስሊሞች ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው አንዷ የሆኑትንና በጥቁር አንበሳ ሕክምናቸውን በመከታተል ላይ የነበሩትን ክርስቲያን በወቅቱ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፣ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ፣ ከምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የበላይ ሓላፊ ከነበሩት ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ጋር በመሆን አጽናንተዋቸዋል።

ዕድሜያቸው በ40ወ0ቹ ውስጥ የሚገመተው ሴት ከአንድ እጃቸው አውራ ጣት በቀር ሌሎች መቆረጣቸውን፣ ከከንፈሮቻቸው መገጣጠሚያና ከአፍንጫቸውም አካባቢ ወደ ጆሯቸው አቅጣጫ በስለት መመታታቸውን የሆስፒታሉ ምንጮች ተናግረዋል።



ሥዕል ፱፡ ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ፣ በአክራሪ ሙስሊሞች ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው አንዷ የኾኑትን በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፣ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ፣ ከምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የበላይ ሓላፊ ብፁዕ አቡን ማርቆስ ጋር በመሆን በጎበኙበት ወቅት



ስዕል *10*፡ ጉዳት ከደረሰባቸው ምእመናን መካከል በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ህክምናቸውን ሲከታተሉ

### 5.3.10 መቱ

በአገራችን በተከሠተው ለውጥ እንቅስቃሴ ምክንያት ጥቅምት 9 ቀን 2009 ዓ.ም ከገቺ አካባቢ ከ1330 በላይ አባዋራዎች የተፈናቀሉ ሲሆን ከተፈናቀሉት መካከል 1200 የሚሆኑት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ናቸው። በተጠቀሰው ዕለት የገቺ ደብረ ዕንቍ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አራት ቤቶች ወድመዋል፡፡ ቤቶቹን ተከራይተዋቸው የነበሩ ሰዎች በሚልዮን ብር የሚገመት ንብረት ወድሞባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሚያዚያ 8 ቀን 2011 ዓ.ም በገቺ ወረዳ ሴከቻ ገበሬ ማኅበር የሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የቤተ ክርስቲያኑን መቃጠል ሰምተው ከሄዱ የጸጥታ አካላት መካከል ኢንስፔክተር ግርማ የተባለው ሰው በቤተ ክርስቲያኑ መቃጠል በማዘን ሰው እንዳቃጠለው ሲናገሩ ከነበሩት መካከል አንዱን ሰው በጥይት መትቶ ጉዳት አድርሶበት ሆስፒታል መግባቱ ነው። የኢንስፔክተሩ ድርጊት ትክክል እንዳልሆነ ተጠቅሶ ለሕግ የቀረበውን የክስ አቤቱታ አንቀበልም ብለው የጣሉት ሲሆን ከሳሾቹ ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት ዕለት ድረስ ችግር ላይ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአገራችን በተከሠተው ለውጥ እንቅስቃሴ ምክንያት ጥቅምት 9 ቀን 2009 ዓ.ም ከገቺ አካባቢ ከ1330 በላይ አባዋራዎች የተፈናቀሉ ሲሆን ከተፈናቀሉት መካከል 1200 የሚሆኑት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ናቸው። በተጠቀሰው ዕለት የገቺ ደብረ ዕንቍ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አራት ቤቶች ወድመዋል፡፡ ቤቶቹን ተከራይተዋቸው የነበሩ ሰዎች በሚልዮን ብር የሚገመት ንብረት ወድሞባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሚያዚያ 8 ቀን 2011 ዓ.ም በገቺ ወረዳ ሴከቻ ገበሬ ማኅበር የሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የቤተ ክርስቲያኑን መቃጠል ሰምተው ከሄዱ የጸጥታ አካላት መካከል ኢንስፔክተር ግርማ የተባለው ሰው በቤተ ክርስቲያኑ መቃጠል በማዘን ሰው እንዳቃጠለው ሲናገሩ ከነበሩት መካከል አንዱን ሰው በጥይት መትቶ ጉዳት አድርሶበት ሆስፒታል መግባቱ ነው። የኢንስፔክተሩ ድርጊት ትክክል እንዳልሆነ ተጠቅሶ ለሕግ የቀረበውን የክስ አቤቱታ አንቀበልም ብለው የጣሉት ሲሆን ከሳሾቹ ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት ዕለት ድረስ ችግር ላይ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 5.3.11 ለገጣፎ

ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የለገጣፎ ቅሩብ ሳሌም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ውሳኔ በግሬደር ፈርሷል።

### 5.3.12 አዳማ

በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት፣ ሊበን ወረዳ በሚገኘው ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ደን መጋቢት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ከቀትር በኋላ የእሳት ቃጠሎ ተቀሰቅሶ ነበር። ከደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ከርቀት የተቀሰቀሰው እሳት፣ የቅዱሳን ከተማ እየተባለ ወደ ሚጠራው ምዕራባዊ አቅጣጫ በፍጥነት ሊስፋፋ ችሏል፡፡ የቃጠሎው መቀስቀስ እንደ ተሰማ የሊበን ወረዳ አዱላላ ከተማ አስተዳደር ሕዝቡ ሥራ አቁሞ እሳቱን ወደማጥፋት እንዲሰማራ መቀስቀሱ የተሰማ ሲሆን፣ ነዋሪውም ወደ ስፍራው በመንቀሳቀስ የበኩሉን ጥረት አድርጓል። የመከላከያ ኃይልን ጨምሮ ሌሎችም አካላት አፋጣኝ እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ተጠይቆ እሳቱን ለመቈጣጠር ጥረት ተደርጓል። ለእሳቱ መነሳት ትክክለኛ ምክንያቱን ማወቅ ባይቻልም፣ "ከሰል አክሳዮችን ነው የምንጠረጥረው፤" ሲሉ በአካባቢው ምእመናን ገልጸዋል። በወቅቱም የተቀሰቀሰውን እሳት ለማጥፋት ሌሊቱን ሲረባረቡ ከነበሩት ምእመናን መካከል ወጣት ሽገና ሉሉ(ወስመ ጥምቀቱ ወልደ ዮሐንስ) እሳቱ በተቀሰቀሰበት ስፍራ ባለ ገደል ወድቆ ጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት ጉዳት የውስጥ ደም መፍሰስ ስላጋጠመው ሕይዎቱ አልፏል።



*ስዕል 11፡ መጋቢት 1 ቀን 2009 ዓ.ም. በደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ዙሪያ የደረሰውን ቃጠሎ ለማጥፋት ሲረባረቡ ከነበሩ ምእመናን መካከል*

### 5.3.13 በጅማ እና አከባቢዋ

በ2009 ዓ.ም ብዙአየሁ አየለ የተባለ ትጉህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በአፍንጫው ደም እየፈሰሰ ጫካ ውስጥ ሞቶ እንደተገኘ ወዲያው ለምርመራ ወደ ጅማ ሆስፒታል ተልኳል። በተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት በየም ልዩ ወረዳ ሳጃ ከተማ 4 ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በገጀራ ተጨፍጭፈው ተገድለዋል።

## 5.4 ከ2010 ዓ/ም የደረሱ ጥቃቶች በኋላ

### 5.4.1 ኮካ ወረዳ፡-

የቤተ ክርስቲያን ንብረት በሚገኝበት ቤት ውስጥ የእስልምና እምነት ተከታይ በጉልበት በመግባት አልወጣም በማለቱ ጉዳዩን ለጸጥታ አካላት ማሳወቅ ቢቻልም መፍትሔ ሳይሰጠው ቀርተዋል።

### 5.4.2 ዶዶላ

ከጥቅምት 12 እስከ 15 ቀን 2012 ዓ. ም ባሉት አራት ቀናት የጃዋር መሐመድን የድረሱልኝ ጥሪ ተከትሎ የወጡ የተቃውሞ ሰልፎች ጥቃታቸውን ወደ ክርስቲያኖች አዙረውታል። በዚህ ምክንያት በዶዶላ ከተማ የብዙ ኦርቶዶክሳውያን ሕይወት ተቀጠፈ። በሙቶ የሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን ቤትና ንብረታቸው ስለወደመባቸው ለስደት የዳረገ ሆኗል፡፡ በወቅቱ 10 ኦርቶዶክሳውያን የተገደሉ ሲሆን ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ቆስለዋል፤ ግምቱ በትክክል ያልታወቀ ንብረት ውድሟል፡፡

**የተገደሉ ኦርቶዶክሳውያን**

1) ዝናቡ ጌታነህ
2) ምሕረተ አብ ደጄኔ
3) ኃይሉ አስማረ
4) ጸጋዬ ገ/መስቀል
5) ባሕሩ በቀለ ደሱ
6) ወ/ሪት ዘኑሼ ሲሳይ
7) ወጣት እሸቱ ተሰፋዬ
8) አነጋግር ደሴ
9) እሸቱ ግርማ
10) ግርማ ተሰፋዬ

**አሟሟታቸውን በተመለከተ**

ሀ) ወ/ሪት ዘኑሼ ጡቷን ቆርጠው አሰቃይተው የገደሏት ሲሆን ሌሎችን ደግሞ በገጀራ አርደው ገድለዋቸዋል። አቶ ኃይሉ አስማረ የወደቁትን ሰዎች አስከሬን ሲያነሣ በመገኘቱ በጥይተ ተመቶ ከወደቀ በኋላ በዱላ ቀጥቅጠው መስጊድ ውስጥ አስገብተው በዛገ ቆርቆሮ አርደው ገድለውታል።

ለ) ተደብድበው ሐኪም ቤት ለሕክምና በገቡበት በመርፌ ተወግተው የተገደሉ፣ በፖሊስ በቍጥጥር ሥር ከዋሉበት ተወስደው የተገደሉም አሉ።

ሐ) የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ከጥቃት እንከላከልላችሁ ብለው በመንግሥት መኪና ጭነው ከወሰዷቸው በኋላ ከከተማ አውጥተው ያሳረዷቸው አሉ።

መ) በድብደባ እና በጥይት ተመተው ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው 28 ሰዎች አሉ።

## የመንግሥት የደኅንነት እና የአስተዳደር መዋቅር ሁኔታ

በጥቃቱ ወቅት የመንግስት ኃላፊዎች ግዴታቸውን በአግባቡ አልተወጡም፡፡ በተለይ የወረዳው የደህንነት ኃላፊ ለአጥቂዎቹ ሽፋን በመስጠት ሲያስጠቁ እንደነበርና፣ በአንዳንዶቹ የጥቃት ድርጊቶችም በቀጥታ ተሳታፊ እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ ፡፡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሸሽተው የገቡና፣ በሕግ ጥላ ሥር የነበሩ ሰዎች ለገዳዮች ተላልፈው ተሰጥተው በመንግስት መሥርያ ቤት በቀበሌ ውስጥ ተገድለዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የሚያሳዩት ብዙዎቹ የመንግስት መዋቅራት በወረዳው የአጥቂው ወገን በመሆን ኃላፊነታቸውን የተው መሆናቸውን ነው፡፡

## የሌሎች ሃይማኖቶች ሚና

በዚህ ከተማ በተፈጸመው ጥቃት የእስልምና እምነት ተከታዮች በቡድን ሆነው ሲያጠቁ ነበር፡፡ በኦርቶዶክሳውያን ላይ የደረሱት ጥቃቶች ሙሉ በሙሉ የተፈጸሙት በእስልምና እምነት ተከታዮች ነው፡፡ እስልምና አንደ ተቋምም ሱታፌ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ መጀመርያ በጥይት የተመቱት ሰማእት አቶ ኃይሉ አስማረ በዱላ ከቀጠቀጧቸው በኋላ ሕይወታቸው ያለፈው ጎትተው ወስደው መስጊድ ውስጥ አስገብተው በዛገ ቆርቆሮ በማረድ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው ከተርታ ግለሰቦች ጥቃት በተጨማሪ መስጊድ ውስጥ እንዲህ ያለ ድርጊት ሲፈጸም የእምነቱ መሪዎች ሙሉ ተባባሪነት እንዳለም የሚያሳይ ነው።

## የኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ሁኔታ

ምእመናን ጥቃቱ ከመጀመሩ በፊት ያለውን ሁኔታ አይተው ለመንግስት ለወረዳውና ለከተማው የደህንነት ቢሮ አመልክተው ነበር። ነገር ግን "አርፋችሁ ተቀመጡ" የሚል መልስ ነው የተሰጥቷቸው፡፡ ጥቃቱ ከተከፈተባቸው በኋላ ቁጥራቸው ፍጹም ተመጣጣኝ እንዳልነበር እና አጥቂዎች እጅግ ብዙ ነበሩ። በተወሰነ መልኩም ራሳቸውን ለመከላከል ቢሞክሩም ስላልቻሉ፣ የሞቱት ሞተው የቻሉት አካባቢያቸውን ጥለው በመውጣት ቤተ ክርስቲያን ተጠልለዋል፡፡ እስከ ቀርብ ጊዜ ድረስም እርዳታ እዛው ሲጫንላቸው የቆየ ሲሆን፣ በቅርቡ በከተማዋ እርቀ ሰላም ተፈጽመዋል

## ንብረታቸው የወደመባቸው ኦርቶዶክሳውያን

በዚህ ጥቃት የበርካታ ኦርቶዶክሳውያን መኖርያና ንግድ ቤቶች በዝርፊያ እና በቃጠሎ የወደሙ ሲሆን ባጠቃላይ የ135 ኦርቶዶክሳውያን መኖርያ ቤት፣ ንግድ ቤት እና የቁም እንስሳት የተዘረፉ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 121 ከተዘረፉ በኋላ በእሳት

እንዲጋዩ የተደረጉ ናቸው፡፡ ከ640 በላይ የቁም እንስሳት ከኦርቶዶክሳውያን ተዘርፈው ተወስደዋል፡፡ ይህም የአንድ መቶ ሠላሳ አምስት አባወራዎች ንብረት ነው፡፡

### 5.4.3 ኤጀሬ

በ2010 ዓ.ም በአብይ ጾም በኤጀሬ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የጥምቀት ታቦት ማደሪያ ስፍራ ላይ መሬቱ የኛ ነው በሚል በቦታው ላይ በሬ በማረድ “እኛ ዋቄ ፈታ ነን” ብለው በምዕመናን ላይ ሃይማኖታዊ ስርዓት ለማጥፋት ሞክረዋል፡፡

### 5.4.4 ፍቼ

በ2010 ዓ.ም በፍቼ ከተማ የአቡነ ሀብተ ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ለመዝረፍና ለማቃጠል ሲገቡ የተገኙ ሁለት ሰዎች አንዱ ሸሽቶ ሲያመልጥ አንዱ የዕለቱን ጥበቃ ሰራተኛ በጩቤ ወግቶ ለመግደል ሲሞክር ሁለተኛው የጥበቃ ሰራተኛ ትኩሶ ባልደረባውን ማዳኑና በቁጥጥር ስር እንዲውል አድርጓል።

### 5.4.5 ባሌ

ባሌ ጎባ ሀገረስብከት በሐምሌ 14/2010 በተፈጠረው የሃይማኖት ግጭት 11 ምዕመናን ተገለዋል፤ እንድሁም 3 የኦርቶዶክሳዊያን ሱቅ ተዘርፏል። የኦርቶዶክሳውያን ቤቶች በድንጋይ ተመተዋል። ሁለት ቤቶች ተቃጥለዋል፤ ተዘርፏል፤ በክርስቲያኖች ላይም አካላዊ ድብደባ ደርሶባቸዋል፡፡ በሲናና ወረዳ አሰንበሬራ ቅ/ጊዮርጊስ የጥምቀት ስፍራ አጥር ለማፍረስ ተሞክርዋል። በዚህም የሃየማኖት ግጭት ተነስቶ በሁለቱም በኩል ሰዎች ተጎድተዋል። በጥምቀት እና የመስቀል ክብረ በዓላት ግዜ ምዕመናን ላይ ድንጋይ የመወርወር ሙከራዎች ይደረጋሉ። በተጨማርም ለአገልግሎት የሚንቀሳቀሱ ዲያቆናትን መደብደብ ሁኔታዎች አሉ። በኮካሳ ወረዳ የቤተክርስቲያን ንብረት ቤት ውስጥ የእስላም እምነት ተከታይ በኃይል በመግባት ከቤቱ አልወጣ በማለቱ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ቤተክርስቲያን አቤቱታ ብታቀርብም እስከአሁን ተገቢው ምላሽ አልተሰጠም።

### 5.4.6 በጅማ እና አከባቢዋ

ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም የአቶ ጌታ እንዳለ ባለ81 ቆርቆሮ ቤት ከነንተራው (3 ቤቶች) እና የሌሎች 4 ገበሬዎችን ቤቶች አቃጥለው ከነሙሉ ቤተሰባቸው አካባቢያቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ተደርጓል።

ጥር ወር 2010 ዓ.ም. የአቶ ጉባይ አደራው ቤትን ሌሊት በመስበር ወደ ውስጥ ሲገቡ ራቁቱን በውስጥ ሱሪ ብቻ ሆኖ በመውጣት ሮጦ አምልጧል። እርሱን ለመምታት ሲታኮሱ እርስበርስ ስለተመታቱ (አንዱ እጁ ላይ ተመትቷል) "እርሱ ነው እንዲህ ያደረገን" በማለት ቤቱ ውስጥ ያለውን ንብረት አውድመው ቤተሰቡን አሳድደዋል፡፡ የተመታው ለመርዳት ሲሞክሩ በነበረበት ወቅት አጋጣሚዉን ተጠቅመው ሚስቱና ልጆቹ ወጥተው ተሰውረዋል፡፡ ጥሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረ ሲሆን በአካባቢው ያሉ ከፍተኛ ጥቃቶች በግላጭ የተጀመሩት በእሱ ላይ ነው፤ ከዛን ጊዜ ጀምሮም የት እንደገባ አልታወቀም፡፡

በአዲስ ልማት ቀበሌም እንዲሁ የክርስቲያኖች ቤቶች ተደብድበዋል፣ ክርስቲያኖቹም ተሰድደዋል፡፡የችግሩ መኖር በመንግሥት የበላይ አካላት ተሰምቶ መከላከያ ሠራዊትን ጨምሮ አጣሪ ሲላክ በወረዳውና በቀበሌው የሚገኙ የመንግሥት አመራሮች እንዲያጣራ የሚልኳቸው አካላት የአክራሪነት አስተሳሰብ ያላቸውን መርጠው ሲሆን ጥፋቱን ሸሽገው የቤተ እምነታቸው ተልእኮና በሚመስል መልኩ መረጃዎቹ

ተዛብተው ሪፖርት እንዲደረጉ ተደርጓል፡፡ ወደ ቄስ ገበዙም በመሄድ "ዝም በል፤ አንድ ምእመን እስኪቀር ድረስ እንኳን መናገር የለብህም፤ ለምን ወደ ሌላ ቦታ ትደውላለህ፤ አርፈህ ተቀመጥ" የሚል ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል፡፡ ከወረዳው ጸጥታ ዘርፍ አቶ ጃፈር የሚባልና አድማ በታኝ ነው የተባለ ግለሰብም በተደጋጋሚ ለዚሁ ጉዳይ ወደ ቄሰ ገበዙ ይመላለሱ ነበር። ይሁን እንጂ ቄስ ቢተው ገረመው፣ እንደ ሌሎቹ ክርስቲያኖች ቤታቸው ሌሊት ሌሊት ሲደበደብ ስለሚያድር አይነ ስውር ባለቤታቸውንና 6 ልጆቻቸውን (ህጻናትን ጨምሮ) ከአንድ ዓመት በፊት ታኅሳስ ወር 2010 ዓ.ም. ውስጥ ወደ ትውልድ ቀዬአቸው መልሰው ልከው እርሳቸው ግን የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነችውን ታቦተ ኪዳነ ምሕረት ጥሎ ላለመውጣት በጸሎትና በለቅሶ ተግተው ከአንድ ዓመት በላይ ከቅጽር ጊቢዋ ሳይወጡ ቆይተዋል፡፡

ሆኖም መከራው ሲበረታባቸው፣ በዙሪያቸውም ያሉ ምእመናን በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለውና ተሰድደው ሲያዩ፣ አብረዋቸው የሚቀድሱ 13 ካህናት (1 መሪጌታ፣ 8 ካህናት እና 4 ዲያቆናት) በመከራው ጽናት ምክንያት መጋቢት ወር 2010 ዓ.ም. ውስጥ ጥለው ሲሰደዱ፣ የቤተሰባቸውም ውትወታ አላስቀምጥ ቢላቸው፣ ምእመናን ሳይኖሩም ታቦትና ካህን ህልውና የላቸውምና ሚያዝያ 24 ቀን 2011 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያኗን ቁልፍ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሊያስረክቡ ከከተቱበት ደብር ወጥተው ወደ ጅማ ሄደዋል፡፡ ወደ ጅማ የቄሱ መሄድ ሲሰማ ሊሙ ገነት ድረስ በሞተር ተከትለው ሊሙ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ስለዩዋቸው ጸሎተኛ በመምሰል በአጸዱ ስር ሆነው ሲጠባበቁ ባለመውጣታቸው ስልክ በመደወል የትም እንዳይሄዱና በሞተር ይዘዋቸው ለመሄድ እየጠበቋቸው እንደሆነ ይነግሯቸዋል፡፡ ካህኑም ወዴትም መሄድ እንደማይፈልጉ በስልክ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ከዕይታ ተሰውረው በማምለጥ ጅማ በሰላም ደርሰዋል።

ሊቀ ጳጳሱን አቡነ እስጢፋኖስን አግኝተው ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላይ ስለደረሰው ግፍ ሁሉ በእንባ ተሞልተው አስረድተዋል። የቄስ ቢተው "ክርስቲያን በየአቅጣጫው እየተገደለና እየተሰደደ ነው፤ ለችግራችንም የሚደርስልን አልተገኘም፡፡ በዚህ ዙሪያ ኦርቶዶክስ ተዳክማለች። እኔም ከዚህ በኋላ ኦርቶዶክስ ረዳት የላትምና በየትኛው ቦታ ቢሆን ቄሰ ገበዝ ሆኜ አላገለግልም፡፡ ቤተ ክርስቲያን መብቷን ማስከበር አለባት፡፡ ሕገ መንግሥቱም ቢሆን ለሁሉም እኩል የሚሠራ ከሆነ መተግበር አለበት፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ይህ ሰቆቃ ለክርስቲያኖች ከደረሰ፤ ከዚህ በኋላ ብሞትም አይቆጨኝ" በማለት ስለጉዳዩ አሳሳቢነት ተናግረዋል። ይህ ሁሉ ሰቆቃ ሲፈጸም "ሸፍታ ናቸው" በሚል ሽፋን የሚጠሩና ለዚሁ እኩይ ተግባር፣ ለሃይማኖታቸው አውቀው ከሸፈቱ አካላት መካከል ብዙዎችን የገደለ፣ የዘረፈና ያሳደደው አቶ መሃመድ ሳኒ እንደናው ነው። የመከላከያ ሠራዊት ሲመጣ ሽፍታ ናቸው የተባሉት የሚገኙት እንደ ሽፍታ ጫካ ሳይሆን በከተማው ውስጥ ለዚያውም የወረዳ ባለሥልጣናት ተብዬዎች በሚያውቋቸው መሸሸጊያዎች መሆኑ ለዚህ ማረጋገጫ ነው። የወረዳው ባለሥልጣናትና የፖሊስ አባላት ችግሩን ከመስማትም በላይ ቢያዩም በሃይማኖት መሰሎቻቸው ለሆኑት አጥፊዎች በመወገን ለጋራ ዓላማ የተሠለፉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ፖሊስ የሚገደሉ ክርስቲያኖቸን አስከሬን ለማንሳት እንኳን በማግስቱ እንጂ በሰዓቱ አይደርስም፤ የሚቾችን አስከሬን ለማስመርመር ወደ ጅማ ለመውሰድ ለትራንስፖርት ከ6ሺህ እስከ 7ሺህ ይከፈላል። ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሲደጋገሙና ህዝበ ክርስቲያኑ ሰሚ በማጣቱ ምክንያት አብዛሃኛው ተሰድዶ ይሄዳል፡፡ጥቃቱ በክርስቲያን "ጥንተ መጠሪያ" በተለምዶ "አማራ ላይ ያነጣጠረ" ይባል እንጂ ግልጽ የሃይማኖት ጦርነት ነው፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው ከአማራ ጎሳ ጋር አብረው ሰፍረው የነበሩ የሸዋ የመጡ ኦሮሞዎችም አብረው የገፈቱ ቀማሽ፣ የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል፡፡

በደዴሳ ወረዳ ግንቦት ወር 2010 ዓ.ም ውስጥ 3 ክርስቲያኖች ደዴሳ ወንዙ ዳር በመሮ ጢሳ ቀበሌ መሻገሪያ በኩል (አትናጎ ወረዳ ክልል ውስጥ ይገባል) የተገደሉ ሲሆን ሊሙ ገነት ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል፡፡ አንደኛው ሮጦ አምልጧል፤ ቤተሰብናልጆቻቸውም ተሰድደዋል፡፡ ችግሩ የተጀመረው የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም ነው፤ ብዙአየሁ እንዳሰኘው የተባለ ሰው ተገድሎ ጫካ ውስጥ ተጥሎ ተገኝቷል። ይህንን የተመለከቱ ኦርቶዶክሳውያን መጋቢት 3 ቀን 2010 ዓ.ም አካባቢውን ለቅቀው እቃቸውን በተሽከርካሪ ላይ ጭነው ሊወጡ ሲሉ ግርማ ጋሹ እና ፋንታ ታሪኩ የተባሉ 2 ሰዎችን ከተሽከርካሪው አስወርደው የኋሊት አስረው ገድለዋቸዋል። በወቅቱ ሾፌሩ ያየውን በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ቀርቦ አመልክቷል፡፡ ገዳዮቹ ሙስሊም መሆናቸውንም ታዝቧል። ከመጋቢት 5 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ድረስ አሥራ ሁለት ምእመናን ተገድለዋል። ግንቦት 7 ቀን 2010

ዓ.ም. አካባቢ አቶ ጋሻው ታመነ የሚባል የሸዋ ኦሮሞ ምሽት 2፡00 ላይ በገደሞ (ገጀራ መሠል ብረት) አንገቱን በመቁረጥ ገደሞውንም ጥለው ሄደዋል፤ የጣር ጩኸት ሲያሰማ ሰው ቢደርስም ወዲያው ነፍሱ ከሥጋው ተለይታለች፡፡ ጋሻው ትዳር ያልያዘ ወጣት ሲሆን ቤተሰቦቹ (ወላጆቹና ወንድም እህቶቹ) እዛው ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቀብረውት "እዚህ አንኖርም" በማለት አካባቢውን ለቅቀው ተሰደዋል።

### 5.4.7 ወልዲያ ከተማ

በ2010 ዓ.ም ጥምቀት በዓል ማግስት የቃና ዘገሊላ ዕለት የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት በዝማሬ አጅበው የተመለሱ 9 ክርስቲያኖች የተገደሉት በመንግሥት ወታደሮች ነው።

### 5.4.8 ጅግጅጋ

ሐምሌ 28 ቀን 2010 ዓ.ም በጅግጅጋ ሒጎ በሚል ስም በተደራጁ ኃይሎች የአድባራትና የገዳማት በእሳት መቃጠል፣ የካህናትና ምእመናን በገጀራና በድንጋይ፣ በቢለዋና በጥይት ተቀጥቅጦ በግፍ መገደልና በእሳት መቃጠል ተፈጽሟል። በሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃት ደርሷል። 7 ካህናት በግፍ ተገድለዋል፤ በእሳት ተቃጥለዋል። በአጠቃላይ 29 ሰዎች ሲገደሉ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ድብደባና ማሰቃየት ተፈጽሞባቸዋል። ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናት ሳይቀሩ ሴቶች በአሰቃቂ ሁኔታ ተደፍረዋል። የሊቀ-ጳጳሱ መኖሪያ መንበረ ጵጵስና በርና መስኮቱ ተገነጣጥለው እያንዳንዱ ዕቃ ተወስዷል። ጥቃት ፈጻሚዎቹ መውሰድ የሚችሉትን ወስደው ያልቻሉትን ደግሞ አቃጥለው ሄደዋል። የበርካታ ምዕመናን ቤት እየተሰበረ ዘረፋ ተፈጽሟል። በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች አካባቢያቸውንና ቀያቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ሆኗል፡፡

የሕዝብ ሀብትና ንብረት ተዘርፏል፤ ረዥም ዓመታት ያስቆጠሩ የቤተ ክርስቲያን ሀብት፣ ንብረት፣ ቅርሶችና ንዋየ ቅድሳት ወድመዋል።ድርጊቱ በተቀናጀና በተጠና መንገድ የተፈጸመ ስለነበር ብዙ ውድመት ደርሷል። ጥቃቱን በዋናነት የክልሉ ፕሬዝዳንት እና ካብንያቸው በበላይነት እንደመሩት የሚታመን ሲሆን የክልሉ ምክር ቤት የካብኔ አባላት ዓርብ ዕለት ሐምሌ 27 ቀን 2010 ዓ.ም በጽ/ቤታቸው ተሰብስበው በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከሱማሌ ተወላጆች ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ላይ ዘርፉያና ግድያ፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ አብያተ ክርስቲያናቻችንን በቃጠሎ የማዉደምና በአገልጋዮቿ ላይ የግፍ አገዳደል እንዲፈፀም፣ እና እንዲቃጠሉ አዋጅ በመንገር ዘመቻውን መርተዋል፡፡ ዓርብ ዕለት በየመስጊዶቹ በለሆሳስ መመሪያና ትእዛዝ እንዲተላለፍ አድርገዋል። የጥቃቱን ሚስጢታዊነት ለመጠበቅ ሲባል ከሱማሌ ተወላጅ ዉጭ የሆኑ ሹፌሮችና ሠራተኞች ቀድመዉ ረጅም እረፍት እንዲወስዱ እና ቁልፎቻቸው እንድያስረክቡ የተደረገ ሲሆን ከመንግሥት በጀት በተገዙና ለመንግስትና ለሕዝብ ስራ ብቻ በተመደቡ ተሽከርካሪዎችና የመንግስት ነዳጅ ተጠቅመው አደጋዉን አድርሷዋል። የጥቃቱ ዋና ተዋናዮች ለረጅም ጊዜ ለዚሁ አደጋ አፈጻጸም የቅድመ ዝግጅት ስልጠና የወሰዱ ወጣቶች በአካባቢው አጠራር ሒጎ ተብለው የሚጠሩ የልዩ ሐይል ፖሊስች አባላትና ከ4 ክ/ጦር እንደማያንስ የሚገመተዉ በመንግስት በጀት በቂ የጦር መሣሪያ የታጠቁ ናቸው ፡፡

#### 1) የካህናት እና የምእመናን ሞት

**ቄስ ጌጤነው ወረታው** ፡- የደብረ ሰዋሰው ቅድስት አርሴማ ገዳም አገልጋይ የነበሩት ቄስ ጌጤነው ወረታው ፤ በምስራቅ ጸሐይ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ቤተክርስቲያኗን ከመጣው አደጋ ለመከላከል በሚያደርጉት የመከላል እየሞከሩ በነበረበት ወቅት በአጥፊ ኃይሎች በድብደባ ተገለው በቤንዚን አርከፍክፈው ያቃጠሏቸዋል። ቄስ ጌጤነው ወረታው የ13 ዓመትና 8 ዓመት ሴት ልጆች አባት ነበሩ። አባ ገ/ማርያም አስፋው፡- የቤተ ክርስቲያኑ ጽዳትና ደዋይ የነበሩ ሲሆን በድብደባ ከገደሏቸው በኋላ በእሳት አቃጥለዋቸዋል።

**መሪጌታ አብርሐም ጥጋቡ፡-** መሪጌታ አብርሃም ጥጋቡ የደብረ ሰዋሰው ቅድስት አርሴማ ገዳም የቁጥጥር ሰራተኛ የነበሩ ሲሆን- በድብደባ ሕይወታቸው ያለፈና የተቃጠሉ ናቸው፡፡ መሪጌታ አብርሐም ጥጋቡ ሁለት ልጆች የነበሩ ናቸው።

**ቄስ ኪዳነ ማርያም ንብረቱ፡-** በደጋ ሀቡር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቀዳሽ ቄስ የነበሩ፣ በድንጋይ ተወግረው የተሰዉ፣ 5 ዓመት እና 6 ወር ሕጻናት አባት ነበሩ። ቄስ ያሬድ ሕውዕ፡- የዋርዴር ደብረ ብስራት ቅ/ገብርኤል ቤተክርስቲያን አገልጋይ ቄስ የነበሩ፣ በድንጋይ ተወግረው የተሰዉ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ተችሏል።



*ስዕል 12፡ በጂጂጋ ሐምሌ 28 ቀን 2010 ዓ.ም ሒጎ በሚል ስም በተደራጁ ኃይሎች ተገለው በእሳት የተቃጠሉ ካህናት በከፊል*

**2) የሰው የአካል ጉዳት (ድብደባ)**

**አባ ሳሙኤል፡- ዋርዴር ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ ቀዳሽ ሲሆኑ በድብደባ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፤ በትራንስፖርት ችግር ምክንያት በወቅቱ ህክምና ያላገኙ፡፡**

**መላከ ፀሐይ ቆሞስ አባ ገ/ጻዲቅ** ፡- የም/ፀ/ቅ/ኪ/ምሕረት አስተዳዳሪ ሲሆኑ በድብደባ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፤ ደብድበው ከጣሏቸው በኋላ በቤንዚን ሊያቃጥሏቸው ሲሉ በእግዚአብሔር ሐይል የተረፉ፤

**መ/ር ጌራወርቅ አበባው**፡- የምስራቀ ፀሐይ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት የመፅሐፍት መምህር፤ በድብደባ ጎድተዋቸው ሞተዋል ብለው ሊያቃጥሏቸው ሲሉ በእግዚአብሔር ቸርነት የተረፉ፤

**መ/ር ሃይማኖት ውብሸት**፡- የምሥራቀ ፀሐይ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል የአቋቋም መምህር፣ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፤ ዲ/ን **የሺዋስ ገነቱ፡-** የምሥራቀ ፀሐይ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ሰባኬ ወንጌልና ቀዳሽ ፣ ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ዲ/ን ገብሩ **ቶኒ**፡- የካቴድራሉ ሂሳብ ክፍልና ሰባኬ ወንጌል ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፤

***ዲ/ን አዕምሮ ታረቀኝ፡-*** የደብረ ይድረስ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤ/ክ አገልጋይ በድብደባ ሙሉ ፊቱ ላይ ከባድ ጉዳት አድርሰውበት በሕክምና ላይ የሚገኝ፤

***መርጌታ ታደሰ ገብረ ማርያም፡-*** የቅዱስ ሚካኤል አገልጋይ በገጀራ እጃቸው ላይ ከባድ ጉዳት አድርሰውባቸው ህክምና ላይ የሚገኙ፤ ሌሎች የተደበደቡ ዝርዝር

1. ዲ.ን ሲራክ ጥበቡ
2. እማሆይ ወለተ ትንሣኤ ተሰፋ
3. ግዛው አበበ
4. ወ/ት ስዕርተ
5. ወ/ሮ ፍሪ
6. አቶ አባተ
7. ገብሩ ኃይሌ
8. ወ/ሮ ዘነቡች
9. አቶ አትክልት

### 3) በአደጋ ምክንያት የተሰደዱ አገልጋዮች

1. ሊቀ ሕሩያን አይነኩሉ ፍቅሬ፣ የደብረ ይድረስ ቅዱስ ጊዮርጊስ አስተዳዳሪ፣
2. መሪጌታ ፍሬው ካሳ፣ የደብረ ይድረስ ቅዱስ ጊዮርጊስ አገልጋይ፣
3. ቄስ የኔነህ ዘላለም፣ የደብረ ይድረስ ቅዱስ ጊዮርጊስ አገልጋይ
4. መልአከ ገነት ፍሰሓ ቢራራ፣ የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት አስተዳዳሪ፣
5. መ/ሣህል አባ ገብረ ሥላሴ መንግሥቱ የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት አገልጋይ፣
6. ቄስ መርሻ ነጋው፣ ቀ/ዳሃር ደብረ መድኃኒት ቅድስት ማርያም አገልጋይ፣
7. ቄስ መርሐ ጽድቅ ልየው፣ መ/መ አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ፣
8. ቄስ በቃሉ ምስጢር፣ መ/መ/ አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ፣
9. ሊ/ሊ.ቃውንት ያሬድ አፈ ወርቅ፣ መ/መ አድባራት ቅ/ሚካኤል የአቋቋም መምህር፣
10. መ/ር ፍሬ ስብሓት፣ መ/መ አድባራት ቅ/ ሚካኤል የድጓ መምህር፣
11. ግሩም ባሻህ ውረድ፣ መ/መ አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ፣
12. ዲ/ን ዓለምነህ አስማረ፣ መ/መ አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ፣
13. ዲ/ን ዳዊት አለሙ፣ መ/መ አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ፣
14. ዲ/ን ብርሃኑ አሰፋ፣ መ/መ አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ፣
15. ዲ/ን የሺህዋስ ገነቱ፣ የቅድስት ኪዳነ ምሕረት አገልጋይ በሕክምና ላይ ያለ
16. መላከ ጸሐይ ቆሞስ አባ ገ/ጻዲቅ፣ በሕክምና ላይ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት አስተዳዳሪ፣
17. መ/ር ጌራ ወርቅ አበባው፣ በሕክምና ላይ ሐረር የኪዳነ ምሕረት አገልጋይ፣
18. መ/ር ሃይማኖት ውብሸት፣ በሕክምና ላይ ሐረር የኪዳነ ምሕረት አገልጋይ፣
19. ቄስ ኤፍሬም ፋንታሁን፣ መ/መ/አድባራት ቅ/ ሚካኤል አገልጋይ ካህን
20. መ/ር ክፍሌ ሞቱማ፣ የስብከተ ወንጌል ኃላፊና ዲያቆን የኪዳነ ምሕረት አገልጋይ፣

### 4) በአብያት ክርስቲያናትና በምእመናን ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት

## መልዕልተ አድባራት ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን

በዙሪያው በሚገኙ የገቢ ማስገኛ ባለ 4 ሕንፃ መስታወት፣ በር እና መስኮት ተሰባብሯል። ግምቱ የማይታወቅ በሕንፃዉ ውስጥ የነበረ የተከራዮች ንብረት ተዘርፏል፣ ሕንጣ ቤተ ክርስቲያኑ በምእመንና በአገልጋዮች ጥረት ቢተርፍም በዙሪያዉ የነበሩ የቤተ ክርስቲያኑ ትምህርት ቤት አንድ ክፍል ከነሙሉ ንብረቱ ተቃጥሏል፤ ሦስት ሱቆች ተቃጥለዋል፤ በ2 መጋዘን የነበረ ንብረት ተዘርፏል፤ በሮቹም ተሰብረዋል። በላሜራ የተሠራ የብረታ ብረት ማምረቻና መሸጫ የነበሩ ሁለት ቤቶች ተዘርፈዋል፤ አንድ መኖሪያ ግቢ ቤት ወደ 8 ክፈል የሚሆን ንብረቱ መዘረፉና መሰባበሩ ተረጋግጧል።

## ምሥራቀ ፀሐይ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል

ሐምሌ 26 2010 ኀሙስ እለት በጅግጅጋ ዜድ ኤም ኢንተርናሽናል ሆቴል የክልሉ ፕሬዝዳንት ደጋፊዎች ተሰብስበው በከፍተኛ ደረጃ ሲመክሩ ውለዋል፡፡ በበነጋው ሐምሌ 27 ዓርብ ምሳ ሰዓት ላይ “እስከ መገንጠል” የሚል አሳብ ሲናገሩ ተሰምተዋል፤ በየሆቴሉም የሚያውቋቸውንና ተናጋሪ የሚሏቸውን እየሰበሰቡ፣“እኛም ከኢትዮጵያ እንገነጠላለን” እያሉ ሲቀሰቅሱ ውለዋል። ፕሬዝዳንቱም፣ “ኦሮሞና አማራ ነዳጁን ወስዷል፤ የሚያስተዳድረው ኦሮሞና አማራ ነው፤ እኔ አያገባኝም፤ የነዳጅ ገቢው 5 በመቶ ነው የሚደርሳችሁ ተብሏል፤ ከአሁን በኋላ ራሳችሁን ነፃ የምታውጡ ከሆነ አውጡ፤ እኔ አላውቅም፤” በማለት ለተወሰኑ ሰዎች ተናግሯል፡፡




ስዕል 13፡ ሐምሌ 28 2010 የጂጅጋ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በአጥቂዎች በተቃጠለበት ወቅት




*ስዕል 14፡ በጂጅጋ ቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ አደጋው ከደረሰ በኋላ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ምእመናን ያደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ*

ቅዳሜ ጠዋት ወደ 2 ሰዓት አካባቢ የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ዐደባባይ ላይ ረብሻ ተነሣ። በአጠገቡ ከነበረ ትልቅ የገበያ አዳራሽ ያገኙትን ሰው ሁሉ መደብደብ፣ ንብረት መዝረፍ ጀመሩ። "ዐቢይ ዳወን"፣ "ሎንግ ሊቭ አብዲ ዑመር" በማለት አጥቂዎቹ መፈክር ያሰሙ ነበር፡፡ የዲ ኤም ሲ ተሳቢ መኪኖች፣ የግልና የመንግሥት ተሽከርካሪዎችና የግለሰብ ባጃጅ ተወስደዋል። የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ እና የቡና ባንክ ገንዘባቸውን ከዘረፉ በኋላ፤ ሰነዶችን አወጥተው አስፋልት ላይ በትነዋል፡፡ ከዚያ በመቀጠል አብያተ ክርስቲያኑን ወደ ማቃጠል ተሸጋግረዋል። ከረፋዱ አራት ሰዓት ጀምረው፣ መንበረ ጵጵስናው የሚገኝባትንና በብፁዕ አቡነ ያሬድ ቅዳሴ ቤቷ የተመረቀውን የምሥራቀ ፀሐይ ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ልሔም፣ ግብር ቤትና ጠቅላላ ንብረቷን አቃጠሉ፤ ተቋሞቿን አፈራረሱ፤ መንበረ ጵጵስናውን ሰባበሩ፡፡ 12 መኖርያ ቤቶች፣ 8 የመማሪያ ክፍሎች ያሉት የቅዱስ ያሬድ ት/ቤት፣ አንድ የእንጨት ሥራ ቤት፣ የካቴድራሉ ቢሮዎች የቻሉትን ያህል ንብረት ዘርፈው የቀረውን ገነጣጥለውና አቃጥለዉታል።



ስዕል 15፡ ቃጥሎ የደረሰበት የምሥራቀ ፀሐይ ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን፣

## ደብረ ሰዋሰው ቅድስት አርሴማ ገዳም መቃኞ ቤተ ክርስቲያን

በ 2009 የተመሠረተች የደብረ ሰዋሰው ቅድስት አርሴማ ገዳም መቃኞ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ በነበሩት የክልሉ ፕሬዝዳንት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ተብሎ ለመካነ መቃብር የተሰጠንና የይዞታ ማረጋገጫ ባለው ቦታ ላይ የተሠራች ናት። ዋናው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ጎን ለጎን እየተሠራ የነበረ ሲሆን በማኅበረ ቅዱሳን፣ የአብነት ት/ቤት ለመገንባትም የታቀደባት ገዳም ናት። ሐምሌ 28 ቀን 2010 ዓ. ም በተደራጁና ራሳቸውን ሔጎ ብለው በሚጠሩ አካላት መቃኞዋ ተቃጥሏል።

## ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል

በከተማው የሕዝበ ክርስቲያኑ ንብረት እየተመረጠ አንድም ሳይተርፍ እንዲዘርፍና እንዲቃጠል ከተደረገ በኋላ፡ ሕዝቡም ወደ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ገብቶ ተጠልሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተደራጁት አጥቂዎች ወደ ቦታው በመሔድ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን እናቃጥላለን ሲሉ ሕዝቡ ተቃውሞ ደወል የተደወለ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑን ማቃጥል ሳይችሉ ቀርተዋል። ነገር ግን በዙሪያው በላሜራ ተሠርተው የተከራዩትን 3 ሱቆች አቃጥለዋል፡፡ ጥቃቱን ለመከላከል ከሞከሩ ሰዎች መካከል ሦስቱ የሊቀ ሥዩማን ጥበቡ ልጅ የሆነው ዲያቆን ሣራክ ጥበቡ፣ ቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የምትኖር ፍሬ የምትባል የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይና ዲያቆን የሺዋስ ጥቃት ተፈጽሞባቸው ካራማራ ሆስፒታል ሕክምና ተደረጎላቸዋል።

## የደጋሐቡር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

ከጅግጅጋ ከተማ ውጭ፣ የደጋ ሐቡር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል፡፡ ዕቃ ቤቱ፣ የሰንበት ትምህርት ቤቱ አዳራሽና ባለ 24 ክፍል ቤቶች ተዘርፈው ተቃጥለዋል።



ስዕል 16፡ ሐምሌ 28 2010 የደጋሃቡር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በአጥቂዎች በተቃጠለበት ወቅት

### ዋርዴር ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

ዋርዴር ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ተቃጥሏል፤ ቤተ ክርስቲያኑ ሦስት ቀዳሽ ካህናት የነበሩት ሲሆን፣ ቄስ ያሬድ ኀቡእ የተባሉት ተገድለዋል፤ ከከተማ ውጭ ጎትተው አውጥተው ደብድበው የጣሏቸው አንድ መነኮስ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በዙሪያው የሚገኙ ቤቶች በአደጋው ሳቢያ ተዘርፈዋል ተቃጥለዋል።

### የቀብሪ ደሐር ደብረ መድኃኒት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

የቀብሪ ደሐር ደብረ መድኃኒት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስትያኗ የተረፈች ብትሆንም ቢሮዎችና ቤቶች ተቃጥለዋል፤ ሁለት ካህናት ወደ ጅግጅጋ ከተማ አምልጠዋል፤ የቀሩት መከላከያ ሠራዊት ደርሶ ተርፈዋል፡፡

### የጎዴ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያኑ

የጎዴ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያኑ፣ አጥሩና የተከራየ መጋዘኑ ቢቃጠልም ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ተርፏል፡፡ ከድሬዳዋ ወደ ጅቡቲ በሚወስደው መንገድ የሚገኙት የአይሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና የደወሌ ቅዱስ ሚካኤል አብያተ ክርስቲያናት፣ በሶማሌ ሕዝብ ጠባቂነትና ተከላካይነት ጭምር ከቃጠሎ ሊተርፉ ችለዋል።

### ደብረ ይድራስ ቅዱስ ጊዮርጊስ

በቤተ ክርስቲያኑ እቃ ቤት ቅዳሜ ላይ ጉዳት ካደረሱበት በኋላ ቤተ ክርስቲያኑን ደግሞ እሁድ ተመልሰው በእሳት እንዲቃጠል አድርገዋል። የዕቃ ቤቱና አንድ ቢሮ የሚገለገሉበት ከቆርቆሮ የተሰራ ቤት ከነ ሙሉ ንብረቱ ተቃጠሎ ወድሟል።

## ቀላፎ ፈለገ ዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ እና ቅዱስ ሚካኤል

ቤተ ክርስቲያኑና በዙሪያው የሚገኙ ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተቃጥለዋል።



*ስዕል 17፡ የተቃጠለው ቀላፎ ፈለገ ዮርዳኖስ ቅድስት ሥላሴ እና ቅዱስ ሚካኤል በከፊል*

### 5.4.9 ሙቱ (ኢልባቡር)

ሚያዚያ 8 ቀን 2011 ዓ.ም በገቺ ወረዳ ሴከቻ ገበሬ ማኅበር የሚገኘው ቅ/ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የቤተክርስቲያኑን መቃጠል ሰምተው ከሄዱ የጸጥታ አካላት መካከል ኢንስፔክተር ግርማ የተባለው ሰው በቤተክርስቲያኑ መቃጠል በማዘን ሰው እንዳቃጠለው ሲናገሩ ከነበሩት ውስጥ አንዱን ሰው በጥይት መትቶ ጉዳት አድርሶበት ሆስፒታል ገብቷል፡፡ የኢንስፔክተሩ ድርጊት ትክክል እንዳልሆነ ተጠቅሶ ለህግ የቀረበውን የክስ ደብዳቤ አንቀበልም ብለው የጣሉት ሲሆን ከሳሾቹ እስከአሁን ድረስ ችግር ላይ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**አስገድዶ ማስለም**

ሙቱ ገቺ ወረዳ ሴከቻ ገበሬ ማኅበር በሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያ የጥበቃ ሠራተኛ የነበሩትን አቶ ሙሉጌታ የተባሉትን ሃይማኖታቸውን ቢቀይሩ የቀበሌ ሊቀ መንበር እንደሚያደርጓቸው ቃል በገቡላቸው መሠረት አስልመው ሊቀ መንበር አድርገዋቸዋል፡፡ ለመሰናዶ ትምህርት ቤት መሥሪያ ቤተ ክርስቲያን በሰጠችው መሬት ላይ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መስጊድ ተሠርቶበታል።

**የፈረሱና ይዞታቸውን የተነጠቁ አብያተ ክርስቲያን**

1. ኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ያዮ ወረዳ ቁራ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
2. ኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ያዮ ወረዳ ሰዴ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን
3. ኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ሑሩሙ ወረዳ ባሮ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን
4. ኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ጮራ ወረዳ ድልቢ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን
5. ኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ጮራ ወረዳ ኩዌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
6. ኢሉባቡር ሀገረ ስብከት ቆሎ ኮርማ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን
7. ምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ታጠቅ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

**በኢሉባቡር ዞን በተለያዩ ጊዜያት በሚፈጸሙ ትንኮሳዎች የተሰደዱ**

- ያዮ ወረዳ መዝገበ ምሕረት ቅድስት ማርያም አጥቢያ 10 አባዎራዎች፣
- የንቦ ቅዱስ ጊዮርጊስ 15 አባ ወራዎች፣
- ኢሉ አባዲንካ ቅዱስ ገብርኤል ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ምእመናን፣
- ጮራ ወረዳ አባጎሮ ቅዱስ ሚካኤል 21 አባዎራዎች፣
- አቦ አቡነ አረጋዊ 50 አባዎራዎች፣
- ሑምቤ ቅዱስ ገብርኤል 40 አባዎራዎች ተፈናቅለዋል።

### 5.4.10 ጎሬ ከተማ

ጎሬ ከተማ ጎሬ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በ2011 ዓ.ም የተተከለውን የታላቁ ሰማዕት የአቡነ ሚካኤል ሐውልት ከቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት በሚገኘው አደባባይ ላይ እንደሚተከል ከመንግሥት እንዲሁም ከዐርበኞች አባቶች ታምኖበት ነበር፡፡ ሆኖም በጎሬ ሬድዮ ጣቢያ በሚሰራ ካሊድ ተብሎ በሚጠራ አክራሪ ሙስሊም አስተባባሪነት ፕሮቴስታንቶችን ጨምሮ "ሐውልቱ አደባባይ ላይ ከተተከለ ሞተን እንገኛለን፤ እሳቸው የሞቱት ሲሞቱ ነው፤ ኦሮሞ አይደሉም፤ አናውቃቸውም፤አይወክሉንም" ብለው በመቃወም አሁን ባለበት ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ እንዲተከል ሆኗል፡፡

### 5.4.11 ግራር ጃርሶ ወረዳ

በጥር 10ቀን 2011 ዓ.ም በግራር ጃርሶ ወረዳ የአሌ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት ዋዜማ በዓል ላይ የተደራጁ ቡድኖች ካህናቱንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን የደበደቡ ሲሆን በድጋሚ መጋቢት 27 ቀን 2011 ዓ.ም የቤተ ክርስቲያኑን ዘበኛ ደብድበው ጉዳት አድርሰውባቸዋል።

### 5.4.12 በያያ ጉለሌ ወረዳ

ጥር 26 ቀን 2011 ዓ.ም በያያ ጉለሌ ወረዳ ዋቄፈታ ነን የሚሉ የተደራጁ ቡድኖች ተሰብሰበው በሬ አርደው ደሙን በግንባራቸው በመቀባት የኦሮሞ ባህልና ሃይማኖት ይሄ ነው ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የእኛ አይደለም፣ የቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ የሆነውን መሬት ለቄሮዎች ተከፋፍሎ መሰጠት አለበት በሚል መፈክር ማሰማት እና በግንባራቸው የተቀቡትን ደም በአቡነ ሀብተማርያምና በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠበል ታጥበዋል።

### 5.4.13 ጫንጮ ወረዳ

በየካቲት 2011 ዓ.ም በጫንጮ ወረዳ ቤተ ክህነት ስር የሚገኘውን የመነ አብቹ ደብረ ሳህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለ24 ዓመት ይዞታ የነበረውን ባህር ዛፍ ሸጦ ለህንጻ ግንባታ ገቢ ለማገኘት ቢሞክርም የተደራጁ አካላት ባህር ዛፍ የገዛውን አካል እንዳይቆርጥ ማገዳቸው እና "ታቦታችሁን አንሱልን ስርታችሁ ብትጨርሱም እንኳን ለእኛ ታስረክባላችሁ እኛ እንገባበታለን" በማለት የማስፈራራት ድርጊት ፈጽመዋል።

### 5.4.14 ደገም ወረዳ

የካቲት 16 ቀን 2011 ዓ.ም በደገም ወረዳ የሚገኘውን የማሲ ቅዱስ ገብርኤል ህንጻ ቤተ ክርስቲያንን ሙሉ በሙሉ መቃጠሉና በቤተ ክርስቲያኒቱ የነበሩትን ታቦታትንና ነዋየ ቅድሳትን ወደ ባሕር ውስጥ ጥለው በምዕመናን ፍለጋ የቅ/ገብርኤል ጽላት ሲገኝ በደባልነት የነበረው የቅዱስ ባለወልድ ጽላት ግን ሳይገኝ ቀርቷል። በሚያዝያ 16 ቀን 2011 ዓ.ም በዚሁ በደገም የሚገኘውን የኤፌርሶ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን ቁልፍ ሰብረው ገብተው ክብሪትና ላይተር ይዘው ለማቃጠል ሲሞክሩ አንዱ ግለሰብ ሲያዝ ሰባቱ ግብረ አበሮች አምልጠዋል።

### 5.4.15 ሂደቡ አቦቴ ወረዳ (ሰሜን ሸዋ ሰላሌ)

ታህሳስ 28/2011 ዓ.ም የሂደቡ አቦቴ ወልዴ በዓለወልድ ቤተ ክርስቲያን የልደት በዓል ዋዜማ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን ከአዳራሽ አስወጥተው ዘፈን ሲዘፍኑበት አደሩ።

- መጋቢት 13 ቀን 2011 ዓ.ም በሂደቡ አቦቴ ወረዳ ኤጀሬ ከተማ የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ቤተክርስቲያንን ቁልፍ

ሰብረው በመግባት ጽላቱንና ንዋያተ ቅዱሳቱን በሙሉ ዘርፈው ሹንቁራ በሚባለው ተራራ ላይ ወስደው ንዋየ ቅደሳቱን ሲያቃጥሉ ጽላቱን ማቃጠል አቅቷቸው ተገኝቶ ተመለሷል።

- መጋቢት 10 ቀን 2011 ዓ.ም የሂደቡ አቦቴ ስሬ ሞሮሴ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን 13 ጸበሎች ቆፋፍረው ማጥፋታቸው እና የጸበሉን ቧንቧ መሰባበራቸው መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም በሂደቡ አቦቴ ወረዳ የሚገኘውን የአድዓ ቅዱስ በዓለወልድ ቤተ ክርስቲያን ቀን በቀን በእሳት ለኩሰው ነዋያተ ቅድሳቱ ሲቃጠል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ በሕዝብ ርብርብ መትረፉ፣

### 5.4.16 በኤፍራታና ግድም ወረዳ

በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚገኘው የቆሪ ሜዳ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በታጠቁ ኃይሎች በደረሰበት ጥቃት የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ክፍል እና ንዋየ ቅድሳት የተቃጠለ ሲሆን ምእመናን ተገድለዋል።

### 5.4.17 ኩዩ ወረዳ

የተደራጁ አካላት በኩዩ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የደሮ የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ይነሳልን በሚል ጫና እየፈጠሩ ሲሆን፣ በሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት በኤጀሬና ደገም ወረዳዎች በአራት አብያተ ክርስቲያናት ላይ አደጋ ሲደርስባቸው የትንኮሳ ሙከራ በኩዩ፣ በሱሉልታ፣ ያያ ጉለሌ ወረዳዎች ለማድረግ ተሞክሯል።

### 5.4.18 በጅማ እና አከባቢዋ

- ሚያዝያ 5፣ 2011 ዓ.ም. በጋሌ ሥርጤ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚኖር አንድ ወጣት ከሌሊቱ 6፡00 ላይ ከቤቱ ጠርቶ በማስወጣት በአሠቃቂ ሁኔታ በጠብ መንጃ ተገድሏል፡፡
- አቶ ገበየሁ ወርቅነህ የሚባሉ ብዙ ጋሻ መሬት የነበራቸው ታዋቂ ባለሀብትና ቀደምት የአካባቢው ነዋሪ ሲሆኑ ልጆቻቸውን ሁሉ እዛው ወልደው፣ ድረው፣ የልጅ ልጅ አይተዋል፡፡ ሆኖም አሁን ንብረታቸውን ሁሉ ጥለው ቤታቸውን ዘግተው ወጥተው ተሰድደዋል፡፡ እንደሳቸው ሁሉ ሌሎች ብዙ ንብረት ያላቸውም ተሰድደዋል፡፡
- በቡርቃ ጉዲና እና በአዲስ ልማት ቀበሌዎች ከ200 በላይ አባወራ ይኖር ነበር፡፡ ሆኖም መጋቢት ወር 2011 ዓ.ም በተደረገ የክርስቲያኖች ቆጠራ 185 አባወራ ይኖር የነበረ ሲሆን የክርስቲያኖች ግድያና ስደት ስለተባባሰና መፍተሔ የሚሰጥ አካል በመጥፋቱ ሚያዝያ ወር መጀመሪያ ላይ 15 አባወራዎች ብቻ በጋሌ ሥርጤ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቤተ ክርስቲያኗ ቄሰ ገበዝ (አስተዳዳሪ) ጋር በድንኳን ተጠልለው ቀርተው ነበር፡፡
- ጉርሙ መካነ ጥበብ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ፡- በዚህ አካባቢ ያሉ ክርስቲያኖችም ከላይ በአጎራባች አጥቢያዎች ላይ እንደተፈጸመው ሁሉ በዚህም አጥቢያ ባሉት ክርስቲያኖች ላይ አሰቃቂ መከራዎች እየደረሱባቸው ይገኛል፡፡ በጥቂቱ ለመግለጽ ያህል፡በአካባቢው በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ የብዙዎቹ ቤት ፈርሷል፤ ከፊሉ ተቃጥሏል፡፡ ባለቤቶቹን ደግሞ በግፍ በመደብደብ ሁልጊዜ በሌሊት ቤታቸውን እየደበደቡ በማስፈራራት ከቦታቸው እንዲለቅቁ ተደርጓል፤ ንብረታቸው ተዘርፏል፡፡ ሳይወጡ የዘገዩትም በመሣሪያ እየተተኮሰባቸው ተመትተው ተጎድተዋል፡፡ ለአብነት ያክል

- ሚያዝያ 5 ቀን 2011 ዓ.ም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን በሰበካ ጉባኤ ሊቀመንበርነት እያገለገለ የነበረን ቅንና ታታሪ፣ የቤተ ክርስቲያኒቷ የቁርጥ ቀን ልጅ የሆነን ስሙ ማርሸት የሚባል በጠብመንጃ ተኮሰው ደረቱ ላይ መትተው ክፉኝ ተገድቶ የነበረ ሲሆን ጅማ ሆስፒታል ለህክምና እርዳታ ቢሄድም መትረፍ አልቻለም፡፡
- ጥቅምት 2011 ዓ.ም. አቶ ጥላሁን በዜ የሚባል በወርኃ ጽጌ በቤተ ክርስቲያን ሲዘክር ቆይቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ተደብድቦ ሳይሞት ተርፏል፤ ለወረዳው የመንግሥት ኃላፊዎች አመልክቶ ምላሽ ሲያጣ ለህይወቱ ሰግቶ አካባቢውን ለቅቆ ሄዷል።
- ኅዳር 8 (በግምት) ቀን 2011 ዓ.ም ወንድሙን አሳድደነው እርሱ ቀርቷል ብለው የአቶ ጥላሁን በዜ ወንድም የሆነውን አቶ ዘሪሁን በዜንም በገጀራ አንገቱን ሊቆርጡ ሲሰነዝሩ በእጁ ሲመክት የእጅ ጣቶቹ ተቆርጠው ስለተጎዳ እርሱም አካባቢውን ጥሎ ወጥቷል።
- በዚሁ ኅዳር ወር 2011 ዓ.ም ውስጥ የአቶ ሲሳይ አለሙ ልጅ ዋለልኝ ሲሳይን ሜዳ ላይ ብቻውን አግኝተው ሊገድሉት ሲሉ "አትግደሉኝ ተዉኝ፤ እቤት ያለውን መሣሪያ አውጥቼ እሰጣችኋለሁ" በማለት ሲማጸን ትተውት እቤት ድረስ ተከታትለው በመሄድ መሣሪያውን አውጥቶ እንዲሰጣቸው ቢጠይቁት "ጫካ ውስጥ እንዳትገድሉኝ ፈርቼ እንጂ መሣሪያ የለንም" በማለቱ እስከነ አባቱ ከፍተኛ ድብደባ አድርሰውባቸዋል፤ የቤታቸውንም በርና መስኮት ገነጣጥለዋል። በዚህም ምክንያት ከአካባቢው ወጥተው ተሰድደዋል፡፡
- ታህሣሥ 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ወ/ሮ ጥሩ ካሴ የምትባለውን እና አቶ አስቻለው የሥጋት የተባሉትን ክርስቲያኖች ቤቶቻቸውን ደብድበው ንብረቶቻቸውን በመሰባበር አሳድደዋቸዋል፤ ልጆቻቸውም ጠፍተዋል፡፡

- በሊሙ ሰቃ ወረዳ በወረዳው ያለው የምእመናን ቁጥር ጥቅምት ወር 2011 ዓ.ም ላይ 101 አባወራ የነበረ ሲሆን መጋቢት ወር መጨረሻ ላይ 65 አባወራ ቀርተዋል፡፡ ጨንጌ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከ100 በላይ አባወራ የነበረ ሲሆን ብዙዎቹ ተሰድደዋል።በአጠቃላይ እየደረሰ ባለው ግድያ፣ ዝርፊያ፣ የቤት ድብደባና ዛቻ ምክንያት 185 አባወራ እና 13 ቄስና ዲያቆን በድምሩ 198 አባወራ ከቀዬአቸው ተፈናቅለው ተሰድደዋል፡፡ ከ15 በላይ ክርስቲያኖች በአሰቃቂ ግድያ ተገድለዋል፡፡ ለአብነት ያክል

  - በኅዳር ወር 2011 ዓ.ም የአቶ አሳዬ ዋሴ እና የታናሽ ወንድሙ 3 ቤቶች ተቃጥለዋል፣ ግለሰቦቹም አካባቢያቸውን ጥለውም ተሰደዋል። የአቶ ተሾመ እንየውም ቤት ተቃጠለ፤ ከነቤተሰቡ ጥሎ ጠፍቷል፡፡
  - ታህሣሥ 9 ቀን 2011 ዓ.ም. አዲሱ ይታየው የተባለው ክርስቲያን ወደ አጎራባቹ የኢሉባቦር ክልል ለእርሻ ሄዶ ሲመለስ አንገቱን በስለት ቆርጠው የተገደለ ሲሆን አስከሬኑም ወደ አማራ ክልል ተወስዶ ተቀብሯል ፡፡
  - ሚያዝያ 4 ቀን 2011 ዓ.ም ለሚዘከረው የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጽዋ ቀጤማ ሊያጭድ በሄደበት ሚጡ ወንዝ ዳር አቶ ልየው ጌትነትን አንገቱን ቀልተው በመጸዳጃ ቤት ጉድጓድ ውስጥ ጥለው በላዩ ላይ የከብት ፍግ ጨምረውበታል፡፡ የመጸዳጃ ጉድጓዱ የአቶ መሃመድ ሃምዛ ሲሆን ቤተሰቡና በእርሻው ሥራ ላይ ያሉ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ወዳጅ ዘመዶቹም ቀጤማ ሊቆርጥ ወጥቶ የጠፋውን አቶ ልየው ጌትነትን ፍለጋ ቢወጡም ሊያገኙት አልቻሉም፤ ያገኙትን የደም ነጠብጣብ ተከትለው ሲሄዱ ግን ለማመን የሚከብድና ለሰው ቀርቶ ለአስከሬን እንኳን የሚሰጠውን ኢትዮጵያዊ ክብር በሚንድ መልኩ ከአጨደው ቀጤማ ጋር በመጸዳጃ ቤት ጉድጓድ ውስጥ ቀብረውት ተገኝቷል፡፡ አቶ ልየው ጌትነት መቀሌ ዩኒቨርሲቲ የሚማር ታደለ ልየው የሚባል ልጅና ሌሎችም ልጆች የነበሩት ጠንካራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበረ፡፡

- በወረዳው መሮ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ላይ በግምት 200 ሺህ ብር የሚያወጣ ባሕር ዛፍ በቁሮ ስም የሙስሊሙ ወጣቶች ተከፋፍለውታል፤ 10ሺህ ብር የሚያወጣ መጠን ያለው ብቻ ቀርቷል፡፡ ዛፎቹን ወገብ ወገቡ ላይ በመቁረጥም መልሶ እንዳያቆጠቁጥ በማድረግ ተስፋ የማስቆረጥ ተግባር ፈጽመዋል፡፡
- ጩንጌ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከ100 በላይ አባወራ የነበረ ሲሆን ብዙዎቹ ተሰድደዋል፡፡ለወረዳው የመንግሥት ኃላፊዎች ፖሊስ ብናሳውቅም ምላሽ አልተሰጠም፤ በወረዳው ላይ ኦርቶዶክስ ተኮር የሆኑ ሰብአዊ፣ ማኅበራዊና ሕገመንግስታዊ የሙብት ጥያቄዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

- ከሊሙ ወደ ጅማ 17 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኘው አምቡዬ የምትባል ከተማ ላይ "ኦሮሞ ብሎ ኦርቶዶክስ የለም" ብለው ጫና በማሳደር አንድን አባወራ ባለፈው የ2011ዓ.ም ዓቢይ ጾም ላይ በማስገደድ እንዲሰልም የተደረገ ሲሆን ባለቤቱ ግን "ጾም እስኪፈታ ድረስ ልቆይ" ብላ ምክንያት በመስጠት ቆይታለች፡፡
- በሊሙ ሰቃ ወረዳ፡ አቶ ሰይፉ ታደሰ ይባላሉ። በጅማ ዞን አትናጎ/ሊሙ ሰቃ/ ወረዳ የአትናጎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያንን ያሰሩና ሰፊ የእርሻ ልማት ያላቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚረዱ ኦርቶዶክሳዊ ባለሀብት ግንቦት ወር መግቢያ ላይ በሊሙ ኮሳ አካባቢ በሚንቀሳቀሱ ሙስሊሞች ከሾፌራቸው ጋር በጥይት ተገለው ከተገደሉ በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ አካላቸው ተቆራርጦ ተጥለው ተገኝተዋ፣ እዚህ ክርስቲያን የአራት ልጆች አባትና የቤተሰብ ሓላፊ ነበሩ፡፡የመንግስት አካላት ጉዳዩን አፍነው ይዘዋል፣መረጃም እንዳይወጣ በከፍተኛ ደረጃ ከልክለዋል፡፡



ስዕል 18፡ የሟች አቶ ሰይፉ ታደሰ ፎቶ

- ከጳጉሜ 2010 ዓ.ም እስከ መስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም በመስከረም ወር 2011 ዓ.ም በመላው ሀገሪቱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት መንግስት እንዲያስቆም ለመጠየቅ ሊደረግ ታስቦ ዝግጂ ሲደረግበት የነበር የሰላማዊ ሰልፉ በጅማ ከተማ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆነው አቶ ቤተም ማሞ ከማለዳው 12፡00 ላይ ከመኖሪያ ቤቱ ከ50 በላይ በሚሆኑ ፖሊሶች ተይዞ ታሰሯል፡፡ የሀገረ ስብከቱን ሥራ አስኪያጅ ጨምሮ የመመሪያ ኃላፊዎችና የአድባራት አስተዳዳሪዎች በከንቲባው ጽ/ቤት በሰላማዊ ሰልፉ ዙርያ አስቸኳይ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን በሀገረ ስብከቱ ጥብቅ ክትትል እና በካህናት አባቶች ከፍተኛ ጥረት አቶ ቤተም ማሞ በታሰረ በሁለት ሰዓታት ልዩነት ውስጥ እንዲፈታ ተደርጓል። በወቅቱ ከደረሱ ጉዳቶች መካከል፡-

- በጅማ ከተማ መርካቶ በተለምዶ ስሙ የአጅፕ ታክሲ ማዞሪያ አካባቢ በግምት ከቀኑ 7፡15 ላይ የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት የሆነው መቋሚያ በአክራሪ ወጣቶች የተቃጠለ ሲሆን በከተማው የሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ በሆኑ የባለ ሦስት ጎማ ተሽከርካሪዎች (ባጃጆች) ላይ ጥቃት ደርሷል፡፡

- አቶ ሲሳይ የተባለ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ (በጅማ ደ/ኤ/ቅ/ድ/ማርያም ቤ/ክ የማኅበረ ሰላም መንፈሳዊ ማኅበር አባል) መቋምያ ለምን ታቃጥላላችሁ በማለቱ ከፍተኛ ድብደባ ደርሶበት ሆስፒታል ቢገባም ሕይወቱን ማትረፍ ባለመቻሉ በሰማዕትነት አልፏል።

- አክራሪዎቹ ወደ ቅድስት  ማርያም ቤ/ክ በመሄድ የደጀ ሰላሙን መግቢያ በር ታቤላ ላይ ድንጋይ በመወርወር ትንኮሳ ጀምረዋል፡፡ የመንግሥት ባለስልጣናቱና ሕዝበ ክርስቲያኑ በማርያም ቤ/ክ በስብሰባው ላይ ሳሉ የአክራሪዎቹ ቡድን ወደ ቤ/ክ ቅጽረ ግቢ ድረስ በመምጣት ጥቃት ለማድረስ እና ምእመናንን ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በቢራ ጠርሙስ ነዳጅ በማዘጋጀት በቤ/ክኑ አጥር ሥር አስቀምጠው እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ተችሏል።

- በዚሁ ዕለት ማታ በግምት ከምሽቱ 2፡00 አካባቢ በተለምዶ ስሙ መርካቶ ባጃጅ ተራ ከዳሽን ባንክ ፊት ለፊት የሚገኙ በርካታ ሱቆች ተቃጥለዋል (ሱቆቹ የኦርቶዶክሳውያን እና የሌሎች እምነት ተከታዮችም ጭምር የነበረ ነው።  መንግሥት የእሳቱ መንስሔ የኤሌክትሪክ አደጋ ነው ማለቱ የማይዘነጋ ነው)።

- በጅማ ፈ/ሰ/ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን እየጠበቁ ለማደር ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚሄዱ ልጆች መካከል ወጣት መልአኩ ተፈራ ላይ በቁጥር 12 የሚደርሱ የአክራሪዎቹ ቡድን አባላት ድብደባ በመፈጸም ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ ወጣት መልአኩ በዕለቱ ቤተ ክርስቲያን ለማደር ዝግጅቱን ጨርሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ላይ ሳለ ነበር ጉዳቱ የደረሰበት።

- በጅማ ፈ/ሰ/ቅ/ግብርኤል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ የሆኑ የሱቅ ነጋዴ ለክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ሲሄዱ የታሸገ ውኃ ሸጠሃል በማለት አቶ ሽጉጤ የተባሉትን ግለሰብ ፖሊስ አስሮታል።

- ከምእመናን አንገት ላይ ማዕተብ የመበጠስ ተግባር ተፈጽሟል፣ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑ የአለባበስ መገለጫዎችን በለበሱ ምእመናን ላይ እና የኢትዮጵያን ባንዲራ ቀለም የያዘ ልብስ በለበሱ ክርስቲያኖች ጥቃት ደርሷል፡፡

- ቅዱሳት ሥዕላት ከባጃጅ እና ከታክሲዎች ላይ በማውረድ እንዲቃጠሉ እና እንዲቀዳደዱ ሆኗል፡፡

- አስራ ሦስት ክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶ በጅማ ሆስፒታል የሕክምና ርዳታ ተደርጎላቸዋል፡፡

- ጥቂት የማይባሉ ወጣቶች ለእስር ተዳርገዋል፡፡ በተለይም የጅማ ደ/መ/መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት ሰብሳቢ የሆነው ወጣት ሰሎሞን እና የሰንበት ት/ቤቱ አባል የሆነችው ወጣት ሕይወት ለእስር ተዳርግል፤

- በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ከጅማ ደ/ኤ/ቅ/ድ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን አንድ ካህን እና አንድ ዲያቆን ሀገር ለቀው ተሰድደዋል።

- ይህ ድርጊት በተፈጸሙባቸው ዕለታት የጅማ ከተማ ነዋሪ ያልሆኑ ነገር በጅማ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል

አንዱ በሆነው የሰርቦ ወረዳ እንደሚኖሩ ማረጋገጫ የቀረበባቸው ሦስት ግለሰቦች ድርጊቱ ተጀምሮ እስከሚያበቃ በጅማ ከተማ እንደቆዩ ተረጋግጧል፡፡ የሰዎቹም ማንነት የሚከተለው ነው፡-

- ✓ የሰርቦ ወረዳ ግብርና ባለሙያ የሆነው አቶ ጌታቸው አባ መጋል
- ✓ በወረዳ አስተዳደር ውስጥ የካቢኔ አባልና በተለያዩ ጊዜያት በወረዳውና በዞኑ በደረሱ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዎች ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንደነበረው የሚጠረጠር እና በአክራሪነቱ የሚታወቀው አቶ ቲጃኒ ሼህ ከማል።
- ✓ ሥራ አጥ የሰርቦ ወረዳ ነዋሪ የሆነው አባ ዝናብ አባገሮ በዕለቱ በጅማ መናኸሪያ አካባቢ የሚሊሻ ልብስ በመልበስ ታይቷል።

በመጨረሻም የጥቃት አድራሾችና የድርጊት ፈጻሚዎችን በተመለከተ "አክራሪ ወጣቶች" በሚል ለመግለጽ የተፈለገው ከየት እንደመጡ የማይታወቁ፣ በጅማ ከተማ የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ የሌላቸውና በስውር ድጋፍ የሚደረግላቸው በዕድሜ በወጣትነት ክልል የሚገኙ መሆናቸውን በወቅቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስማቸው ከዚህ በታች የተዘሩት በሙሉ የየሰፈር ቄሮ ቡዱን አስተባባሪ ሲሆን ከጅማ ከንቲባ እና አባ ገዳ ደጋፍና አውቅና ያለችው እና ከጳጉሜን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ኦርቶዶክሳውያንን በማሳደድ የነፍስ ግድያ የአካል ጉዳት የንብርት የቤት ማቃጠል ማፍርስ እንዲሁም ከ53 በላይ ኦርቶዶክስ ወጣቶችን ቤተ ክርስቲያን እንዳይቃጠል ሄድው ስለተከላከሉ አንገላለን አብን ናችው በሚል ዛቻ ለስደት ዳርገችዋል።

የአክራሪ ቄሮ ስም ዝርዝር

1. ቦሳ አዲስ ከተማ 'ሳር ሰፍር 'የቄሮ ሰብሳቢ ዋና የሆነው መሐመድ ዘይን።
2. ሣር ሰፈር ቄሮ በመባል የሚታወቀው ሙስጥፋ ሞጋ።
3. አስማይል ሞጋ
4. አህመድን ለግቃር የጂማ ከተማ ቄሮ አዛዝ እና ሰብሳቢ
5. አብዲ ጃል (መንትኢና ቄሮ
6. አብዲ ሉባባ (ምንትኢና ቄሮ )
7. ሚፍታ ያሲን (መንትኢና ፍራፍሬ ነጋዴ )
8. ፍአዴ (ፋአድ ቡሴር መንትኢና )
9. ሙባሪክ (መንትኢና )
10. ነጋ (መንትኢና )
11. ሞትኢ (ቢሺሼ )
12. ቶፊቅ ወሺ ( ሰራተኛ ሰፈር )
13. ሀንሳር ተማም (ሰራተኛ ሰፈር )
14. ሀይደር ተማም (ሰራተኛ ሰፍር )
15. ሀይደር ተማም (ሰራተኛ ሰፈር )
16. ኪሉ (ሰራተኛ ሰፍር )
17. ሰቦ (በግ ተራ ቄሮ አዛዝ ና ሰብሳቢ )
18. ፉአድ (ሸዋ በር ሰብሳቢ )
19. ተመኪ ሽሪፍ (አባ ገዳ ቄሮ ዋና ሰብሳቢና የዳውሮ በር ቄሮ ሰብሳቢ )
20. አሚር (ሰራተኛ ሰፍር ቄሮ )

21. አብዲ ቄሮ (ፀጉረ ጎፈሬ ዋና ቄሮ ሰብሳቢ )
22. ጉቴ ( አባ ገዳ ቄሮ አባል )
23. ፈሪድ ( አባ ገዳ ቄሮ አባል )
24. ዲኮ
25. ፈሪድ የማም (ጫት ተራ ቄሮ ሰብሳቢ )
26. ጅንፍል (ሰራተኛ ሰፍር ቄሮ )
27. ጃፍር አሊ (ሰራተኛ ሰፍር ቄሮ )
28. መሃምድ ሊኬ (ሰራተኛ ሰፍር ቄሮ )
29. አውሌ ቀውሴ (ሰራተኛ ሰፍር ቄሮ )
30. ማሙሽ ደምበላሽ ( ሰራተኛ ሰፍር ቄሮ )
31. ሰይፍ ሙሳ (ሰቃ በር )
32. ለሚ ( አባ ገዳ አባል )

በተጨማሪም ይህንን ችግር በዋናነት ሲያስተባብሩ ከነበሩት ገለሰቦች መካከልና በወቅቱ የነበራቸው መለያ ከታች የተቀመጠውን ይመስላል፡፡

1. አብዱ ለጢፍ
2. አንሳር ተሚም
3. ቶፊቅ
4. አቢያ ጀማል
5. ሃይደር እስማኤል
6. መሐመድ አሊ
7. ቴዎድሮስ ዘርፉ /ነጂብ/
8. ኢዘዲን አሊ
9. መሐመድ ጀማል
10. አብዱለዚዝ
11. አመዲን የቴሮ ሓላፊ ነኘ ባይ
12. ሰባሲን
13. የሱፍ አብደላዚዝ /ምክር ቤት/
14. በሲሮ /የቴር አለቃ/

*ሠንጠረዥ 1፡ ከላይ በተገለጹት አስተባባሪዎች አመራር ሰጭነት በኩል የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት ምዕመናንና የደረሰባቸው ጉዳት የሚያሳይ መረጃ*

| የተጎጂ ስም | የጉዳት ዓይነት |
|---|---|
| ሲሳይ ከበደ | ግድያ |
| ሙላለም አሻግሬ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| በላይ በቀለ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ገበየሁ በቀለ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ማህሌት አዳሙ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| አባት አየለ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ምትኩ ኃይሉ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ኪዳኔ አበራ | የንብረት እና የአካል ጉዳት የደረሰበት |
| ጥላሁን ታደሰ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| አማኑኤል አስረስ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ታሪኩ አስፋው | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| አንዱአለም ጌታቸው | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| አንዱአለም ማሞ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ሔኖክ በቀለ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ቃልኪዳን ከነቤተሰቡ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ሙሉቀን ቢረጋ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ጌትነት መዝሙር ቤት | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ዝናሽ ሳህሌ አየለ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ታደሰ ኪየ ከነቤተሰቡ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |
| ሚኪያስ አፈወርቅ | የንብረት ጉዳት የደረሰበት |

### 5.4.19 በአፍራታና ግድም ወረዳ (ሰሜን ሸዋ)

በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአፍራታና ግድም ወረዳ የሚገኘው የቆሪ ሜዳ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢት 29ቀን 2011 ዓ.ም በታጠቁ ኃይሎች በደረሰበት ጥቃት የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ክፍል እና ንዋየ ቅድሳት የተቃጠለ ሲሆን ምእመናንም ተገድለዋል፡፡ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት የዕቅድና ልማት ክፍል ኃላፊ ሊቀ ካህናት ሀብተ ጊዮርጊስ ዘውዱ እንደ ገለጡት በታጠቁ ኃይሎች /የኦነግ ታጣቂዎች / አማካኝነት በአጣዬ፣ በካራ ቆሬና በማጀቴ 60 ሰዎችን መገደላቸውን ከነዚህ ውስጥ 3ቱ የሌላ እምነት ተከታይ ሲሆኑ 57ቱ ኦርቶደክስ መሆናቸውን 74 የሚሆኑ ሰዎችም ደግሞ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው የሕክምና እርዳታ እየተደረገላቸው መሆኑን በአካባቢው ከሚገኙ ምእመናንና የመንግሥት አካላት መረጃውን እንዳገኙ ገልጸዋል፡፡ የታጠቀው ቡድን በካራ ቆሬ የቆሪ ሜዳ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን መጋቢት 29 ቀን 20 11 ዓ.ም በዕለተ እሑድ በቅዳሴ ላይ እንዳሉ ተኩስ በመክፈት የቤተ ክርስቲያኑን ጥበቃ፣ የሰበካ ጉባኤውን ምክትል ሊቀ መንበርና ገንዘብ ያዡን ገድለው የሰበካ ጉባኤውን ጸሐፊ በጥይት በማቁሰል ወደ ቤተ ክርስቲያኑቅጽረ ግቢ በመግባት የቤተ ክርስቲያኑን የውስጥ ክፍልና በውስጡ ያሉ ንዋየ ቅድሳት መንበሩን ጭምር ማቃጠላቸውንና በቤተ ክርስቲያኑ ጣሪያ ላይ ቦንብ

በመወርወር ጣራው መበሳቱን እንዲሁን የሰ/ትቤቱ አዳራሽ በከፊል መቃጠሉን ተናግረዋል፡፡ጥቃቱ ቤተ ክርሲያንና ምዕመናን ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ገልጸው ሆን ተብሎ ተከባብሮ የነበረውን እስላምና ክርስተና እምነት ተከታይ የሆነውን ማኅበረሰብ ለመለያየት የታቀደ ተግባር ስለሆነ ድርጊቱን አውግዘዋል፡፡ የሰሜን ሸዋ ሃገረ ስብከት ልኡካን፤ በማኅበረ ቅዱሳን የደ/ብርሃን ማዕከል የሥራ አስፈጻሚ አበላትና የአጣዬ ወረዳ ማዕከል አባላት ቦታው ድረስ በመገኘት ምእመናንን የማጽናናትና የማረጋጋት ተግበር ማከናወናቸውን የጠቀሱት ሊቀካህናት ሀብተ ጊዮርጊስ በሃገረ ስብከቱ በኩል የተቃጠሉትን ንዋየ ቅድሳት በማሟላት በቀን 12/08/2011 ዓ.ም መቃኞ ቤትና ጸበሉ ተባርኮ አገልግለት እንዲጀመር የተደረገ ሲሆን ዕለተ ሆሳእና የሀገረ ስብከተ ልኡካን በተገኙበት በልዩ ሁኔታ መከበሩንና ትምህርተ ወልጌል መሰጠቱን አውስተዋል። ሊቀ ካህናትሙሉጌታ የሰ/ሸዋ ሃገረ ስብከት የትምህርት ክፍል ኃላፊ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ እንዲህ አይነት ፈተና መምጣቱ አዲስ አለመሆኑን ከተመሰረተችበት እለት ጀምሮ በርካታ ፈተናዎችን እንዳሰለፈችና በዚህ ዘመንም በልዩ ልዩ ቦታዎች ፈታና እንዳሉ ገልጸው ካህናትና ምዕመናን ሀብት ንብረታቸው ስለተዘረፈ ሁሉም ክርስቲያን በጉልበቱ በገንዘቡ በእውቀቱ በመደገፍና አለሁ ሊላቸውና አስፈላጊውንም ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል፡፡

በአካባቢው ከዚህ በፊትም ቢሆን በዚህ መልኩ ባይሆንም የማስፈራራት እና ለግጭት የማነሳሳት የትንኮሳ ድርጊት ሲፈጸም የነበር ቢሆንም ችግሩ የተፈጠረው በአካባቢው ያልወን የአማራ ልዩ ሃይል ፖሊስ ወግቶ መሆኑን ስናይ ደግሞ በምን ያህል ደረጃ የተጠናከር መሆኑን የሚያመለክት ነው። ቦታው የአከራሪ ሙስሊም ማሰልጠኛ ካምፓስ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ጫካ ውስጥ ከተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች እየመጡ ስልጠና ሲወስዱ እንደነበር የአካባቢው ህዝብ ያውቃል ። ጭፍጨፋውን ከማሰለጠኛ ካምፕ ወጥተው የፈጸሙት ሲሆን በወቅቱ የነበረው ልዩ ኃይልም ብዙ አቅም አልነበረዉም። እነዚህ አካላት በተደጋጋሚ ከካፕ እየወጡ የተወሰነ ነገር ዘርፈውና ገድለው በመሔድ ምዕመኑ ስያሰቃዩት ቆይተዋል። በተለይም በአሁኑ ሰዓት የስጋት ቀጠና ሆኖ እንደቀጠለ ሲሆን በኮማንድ ፖስት ትእዛዝ ውስጥ እንዲገባ የተደረገበት ወቅትም ነበረ። ህዝቡም በፍርሓት ውስጥ የገባ ሲሆን አብዛኛው ነዋሪ እየተተፈናቅለ ይገኛል ። ዘመናዊ በሆነ መሳርያ ተደግፈው የራሳቸው የሆነ የህክምና ቲም እና መሳርያ አምቡላንስ ብሎም የዘረፉትን ንብረት የሚጓጉዙበት አይሱዚዎች እና ሌሎች ትጥቆች በመደራጀት የሚያጠቁ በመሆናቸው ህዝብ ተረጋገቶ ለመኖር አልቻለም ። ይህ ብቻ ሳይሆን የመካለከያ የሚመስል ልብስ ለብሰው እንደሚመጡ የሚናገሩት ነዋሪዎች ለይቶ ለማወቅ በመቸገራቸው መከላከያ እየመሰለው ወደ እሳት እየተጣደ መሆኑን በመግለጽ ጭምር ነው ። የከፋ የሚያደርገው በግብርና ስራ የሚኖሩ ክርስቲያኖች የውሃ መሳብያ በመዝረፍ ፤የእርሻ ልማታቸው በማውደም፤ ሰብላቸው እንዳይሰበስቡ በማስፋራራት ፤በረሃብ እንዲጎዱ እንደስልት አድረገው እየሰሩ ይገኛሉ ። አሁን ባለው ሁኔታ አርሶ አደሮቸሁ አንዱ እየጠበቀ አንዱ እየተከላከለ የሰቀቀን ሕይዎታቸውን እየመሩ ይገኛል።

*ሠንጠረዥ 1፡ በመጋቢት ወር 2011ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአፍራታና ግድም ወረዳ በተፈጠረው ችግር ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች መረጃ*

| ተ.ቁ | የሟች ስም | ወረዳ | ቀበሌ | የሞተበት ቀን | የሞተበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢ/ር ጌታቸው በየነ ዘነበ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 2 | ሳጅን ዮሃንስ ተስፋዬ ከብረት | ኤ/ግድም | ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 3 | አበበ ሹሙቴ የምሩ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 4 | ደበበ አየለ ሸዋመን | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 5 | ጌታቸው ታደሰ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 6 | አሰፋ በረደድ አቡዩሆይ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ተሰማ ጌታነህ ገ/የስ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 8 | አየለ ሻረው ኃ/ሥላሴ | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | 29/07/2011 | ኮበኮብ ቆላ | |
| 9 | ካሳሁን ሞልቶት በየነ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 10 | የቻለ ይገዙ ገብሬ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 11 | መኮንን የምሩ ደርቤ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 12 | አድነው እሸቴ ወ/መድህን | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | 29/07/2011 | ኮበኮብ ቆላ | |
| 13 | እንግዳሰው አስፋው እሸቴ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 14 | ቦጋለ ውብሸት ሃይሉ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | 29/07/2011 | አግላ ማጀቴ ቆላ | |
| 15 | ደምሰው ምትኬ ክብረት | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | 29/07/2011 | ኮበኮብ ቆላ | |
| 16 | ሽጋው ታደሰ ሙላቱ | ኤ/ግድም | ገተም | 29/07/2011 | ገተም ቆላ | |
| 17 | ሁሴን አህመድ ዋሄር | ኤ/ግድም | ገተም | 29/07/2011 | ገተም ቆላ | |
| 18 | ተፈራ በየነ እሸቴ | ኤ/ግድም | ገተም | 29/07/2011 | ገተም ቆላ | |
| 19 | ቸሬ ባሻው ሸዋታጠቅ | ኤ/ግድም | የሰርዶ | 29/07/2011 | አጣዬ 01 ቀበሌ | |
| 20 | ሻንበል ጋሻው ታደሰ | ኤ/ግድም | አላላ | 29/07/2011 | ሞሎ | |
| 21 | ታደሰ አባተ የሻው | ኤ/ግድም | አላላ | 29/07/2011 | ሞሎ | |
| 22 | ተሻለ ውብሸት ተፈራ | ኤ/ግድም | አላላ | 29/07/2011 | ሞሎ | |
| 23 | ቅጣቸው ተሸመ ታደሰ | ኤ/ግድም | ይምሎዎ | 29/07/2011 | ሞሎ | |
| 24 | አያሌው መኮንን ወ/አገኘ | ኤ/ግድም | ካራቆሪ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 25 | ምንዳዬ ማርዬ ዳምጤ | ኤ/ግድም | ካራቆሪ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 26 | ሙላት ተፈራ በየነ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 27 | ምንዳዬ መኮንን አንተን አገኘሁ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 28 | ላቀው ሽፈራ መንግስቴ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 29 | ሹመት ደጉ በለጠ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 30 | ኃ/ጊወርጊስ መኮንን ጀማው | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 31 | ሻረው ታደሰ ጋሻው | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 32 | አስር አረቃ ንጉሽ አሸኔ አለምዬ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 33 | አማረ ግዛው ብሩ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 34 | አያልነሽ ጌታቸው አዘነ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 35 | ካሳው ፋንታ አግዜ | ኤ/ግድም | ሰለሎ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | በለጠ መሸሻ ባንቲደር | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | 29/07/2011 | ቆሪሜዳ | |
| 37 | አስዋብ እስማኤል አበበ | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | 29/07/2011 | አንቃር ቆላ | |
| 38 | ከፈተው መኮንን በየነ | ኤ/ግድም | አላላ | 29/07/2011 | ሞሉ | |
| 39 | አቶ ተስፋ በቀለ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ03 | 29/07/2011 | አጣዬ03 | |
| 40 | አቶ ዘውዱ ተጋፋው | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ03 | 29/07/2011 | አጣዬ03 | |
| 41 | አቶ ሁሴን እንድሪስ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ03 | 29/07/2011 | አጣዬ03 | |
| 42 | አቶ እንዳለ መሸሻ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ02 | 29/07/2011 | አጣዬ02 | |
| 43 | አቶ ስዩም ሀይሌ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ02 | 29/07/2011 | አጣዬ02 | |
| 44 | አቶ አማረ ማኪያው | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ02 | 29/07/2011 | አጣዬ02 | |
| 45 | አቶ ወንደወሰን አለማየሁ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ02 | 29/07/2011 | አጣዬ02 | |
| 46 | አቶ ደበበ ይልማ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ03 | 29/07/2011 | አጣዬ03 | |
| 47 | አቶ ውብሸት አማረ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |
| 48 | አቶ መተኪያ ናደው | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |
| 49 | አቶ ጋረደው ገብሬ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ02 | 29/07/2011 | አጣዬ02 | |
| 50 | ወ/ሮ ዘነበች ጋሻው | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ02 | 29/07/2011 | አጣዬ02 | |
| 51 | ወ/ሮ አሚናት አሊ | አጣዬ | አጣዬ03 | 29/07/2011 | አጣዬ03 | |
| 52 | ወጣት ሁሴን እንድሪስ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |
| 53 | ህፃን አቡበከር ኡመር | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 54 | አቶ አየለ አባተ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |
| 55 | ወጣት አህመድ አደም | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |
| 56 | አቶ ንጉስ ወርቅሸት | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ03 | 29/07/2011 | አጣዬ03 | |
| 57 | አቶ በለጠ ደጉ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |
| 58 | ፋሲካው ተስፌ | አጣዬ ከ/አስ | አጣዬ01 | 29/07/2011 | አጣዬ01 | |

*ሠንጠረዥ 2: በመጋቢት ወር 2011ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአፍራታና ግድም ወረዳ በተፈጠረው ሁከት የቆሰሉ ሰዎች መረጃ*

| ተ.ቁ | የቆለው ስም | ወረዳ | ቀበሌ | የቆሰሉበት ቦታ | የቆሰለበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አበበ በላይነህ ምንጉዳይ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 2 | በቀለ ንጉሴ ባንጃው | ኤ/ግድም | ካራቆሪ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 3 | አልታዬ ከብረት | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 4 | ገለታው ደበበ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 5 | ሻምበል ተፈራ ደምሴ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 6 | ጥላሁን በላቸው | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 7 | ሻጋው ተምትሜ መኩሪ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 8 | አሳልፍ ከበደ ወርቄ | ኤ/ግድም | ቆሪሜዳ | ቆሪሜዳ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 9 | ምናለ ወርቅሸት | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 10 | ፈለቀ ሙላቱ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 11 | ቶማስ በለጠው | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 12 | ዘመድኩን ኤለ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 13 | አየለ ጌታነህ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 14 | ሙላቱ ከበደ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 15 | አስረስ ፀጋው | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | ይማም ገስጠው | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 17 | ወርቅሸት አወቀ | ኤ/ግድም | አግላ ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 18 | ሻምበል ትርፌ | ኤ/ግድም | ማጀቴ | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 19 | ዘነበ ግዛው | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | አ/ኮበኮብ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 20 | ከፈለኝ ዘውዴ | ኤ/ግድም | መ/በር | አግላ ማጀቴ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 21 | ደምሰው ገበየሁ | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | አ/ኮበኮብ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 22 | በቀለ ግዛው | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | አ/ኮበኮብ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 23 | ደስታ ግዛው | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | አ/ኮበኮብ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 24 | ግርማ ፈረደኝ | ኤ/ግድም | አ/ኮበኮብ | አ/ኮበኮብ ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 25 | ድረሴ አበበ | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 26 | አጥላው ድረሴ | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 27 | ጌጤነህ አያሌው | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 28 | ደምስ ግዛው | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 29 | አጥላው ጌታቸው | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 30 | ሙሃባ መሀመድ | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 31 | ተስፋዬ ታፈሰ | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 32 | በቀለ ይርጋ | ኤ/ግድም | ገተም | ገተም ቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 33 | ፀጋዬ አስፋው | ኤ/ግድም | ካብ ሣራምባ | ካብሣራባቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 34 | አለሙ ሸበላው | ኤ/ግድም | ካብ ሣራምባ | ካብሣራባቆላ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 35 | አበቡ ሙብራቴ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 36 | ወንድም አያሌው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 37 | ማሞ ገረመው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 38 | ሞገስ በቀለ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 39 | ተናኜ ከልክሌ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 40 | ይርገዱ ሙሉሰው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 41 | ደጀን ገ/ሥላሴ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 42 | ጌቶ ዘውዱ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 43 | በላይነህ ሙላቱ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 44 | ማሞ ከበደ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 45 | እሸቱ አበበ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 46 | ቀለም ዝቁ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 47 | ዘነበ ዳምጣው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 48 | ብርቱካን አጥላው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 49 | ይከተት በለጠ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 50 | ዘቤ ማስረሻ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 51 | ማስረሻ ንጉሴ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 52 | ጥሩነሽ አጥላው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 53 | ንጉሴ አጥላው | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 54 | ሲገኝ ፊቄ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 55 | ጌትነት ሞገስ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 56 | ግዛቸው ወንድም | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 57 | ማሙሽ መንግስቱ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 58 | እመቤት ይታፈር | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 59 | በልዩ ይጥና | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 60 | አውራሪስ ዠቃለ | ኤ/ግድም | አላላ | ሞሉ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 61 | ሽመልስ አወቀ | ኤ/ግድም | ካራለጎማ | አጣዬ 03 ቀበሌ | 29/07/2011ዓ.ም | |
| 62 | ደምለው ካሳ | ኤ/ግድም | ካራለጎማ | አጣዬ 03 ቀበሌ | 29/07/2011ዓ.ም | |

*ሠንጠረዥ 3: በመጋቢት ወር 2011ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአፍራታና ግድም ወረዳ የማጀቴ ቀጠና አግላ ማጀቴ የደረሰ ከፍተኛ ውድመትና ዝርፊያ*

| | ዝርዝር | መለኪያ | ብዛት | ግምት ዋጋ በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የውሃ መሳቢያ ሞተር | በቁጥር | 2 | 40,000 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 2 | ተለያዩ ሞባይሎች | በቁጥር | 6 | 12600 | ከሟች ላይ የተዘረፈ |
| 3 | ገንዘብ | በቁጥር | | 13,800 | ከሟች ላይ የተዘረፈ |
| 4 | ልዩ ልዩ ጥይቶች | በቁጥር | 394 | 39,400 | ከሟች ላይ የተዘረፈ |
| 5 | ልዩ ልዩ ጠመጃዎች | በቁጥር | 6 | 124,000 | ከሟች ላይ የተዘረፈ |
| *የአግላ ማጀቴ ቀበሌ ድምር ብር* | | | _ | *229,800* | |

*ሠንጠረዥ 4: በመጋቢት ወር 2011ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአፍራታና ግድም ወረዳ በአንቃር ኮበኮበ የደረሰ የንብረት ውድመት*

| | ዝርዝር | መለኪያ | ብዛት | ግምት ዋጋ በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የውሃ መሳቢያ ሞተር | በቁጥር | 46 | 920,640 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 2 | የውሃ መሳቢያ ሽራ | በሜትር | 440 | 28160 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 3 | የተመረተ ቀይ ሽንኩርት | ኩ/ል | 520 | 728,000 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 4 | የተመረተ ሞጥሚጣ | ኩ/ል | 4.5 | 20,000 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 5 | የተከመረ ጭድ | ክምር | 37 | 139,000 | ሙሉ በሙሉ በማሳ ላይ አቃጥለዋል |
| 6 | ጠመጀ | በቁጥር | 1 | 13,000 | የአሜሪካን በልጅግ ከማች ላይ የተዘረፈ |
| 7 | ጥይት | በቁጥር | 20 | 2000 | የበልጅግ ጥይት ከማች የተዘረፈ |
| የአንቃር ኮበኮብ ብር ድምር | | | | 1,850,800 | |

*ሠንጠረዥ 5: በመጋቢት ወር 2011ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በአፍራታና ግድም ወረዳ ካብ ሰራምባ ቀጠና የደረሰ የንብረት ውድመት*

| | ዝርዝር | መለኪያ | ብዛት | ግምት ዋጋ በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተከመረ ጭድ | ክምር | 33 | 115,500 | ሙሉ በሙሉ በማሳ ላይ አቃጥለዋል |
| 2 | አካፋ | በቁጥር | 6 | 1000 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 3 | ባህላዊ የንብ ቀፎከንብ መንጋ ጋር | በቁጥር | 4 | 8000 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 4 | የውሃ መሳቢያ ሽራ | በሜትር | 330 | 22400 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| 5 | ሽንኮራ አገዳ | በሄ/ር | 1.5 | 16000 | የ60ወጣቶች ልማት የነበረ |
| 6 | ቀይ ስር | በሄ/ር | 1 | 7500 | የ60ወጣቶች ልማት የነበረ |
| 7 | ኬሚካል መርጫ መሳሪያ | በቁጥር | 1 | 550 | ከማሳ ላይ የተዘረፈ |
| *የካብ ሰራምባ ቀበሌ ድምር* | | | | 170,950 | |
| በማጀቴ ቀጠና በሦስቱም ቀበሌዎች የንብረት ዝርፊያና ውድመት በገንዘብ ሲጠቃለል 2,251,550 ብር ነው | | | | | |

ማሳሰቢያ ፡-

- የጠመጃና የጥይት ተመን የተቀመጠው በመንግስት በሚሊሻ ጽ/ቤት ተመን ነው፡፡
- የአንድ ቤተክርስቲያን ንብረት በሙሉ የጠፈበት ሁኔታ ነው ያለው ፡፡

*ሠንጠረዥ 6: በመስከረም ወር 2012 በኤፍራታ ግድም ወረዳ በተፈጠረው ሁከት የሞቱ ሰዎች መረጃ*

| ተ.ቁ | የሟች ስም | ወረዳ | ቀበሌ | የሞተበት ቀን | የሞተበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስላሽ ተዋበ | ኤ/ግድም | ላይኛው አጣዬ | 25/01/2012 | ላይኛው አጣዬ | ሃይማኖት ኦርቶዶክስ |
| 2 | ሽመልስ በየነ | ኤ/ግድም | ላይኛዉ አጣዬ | 25/01/2012 | ላይኛው አጣዬ | |
| 3 | ሙሉጌታ በየነ | ኤ/ግድም | ላ/አጣዬ | 25/01/2012 | ላይኛው አጣዬ | |
| 4 | ጎሽሜ ይፍሩ | ኤ/ግድም | አጣዬ 03 | 25/01/2012 | ሞሉ | |
| 5 | ስመኘ ሽፈራ | ኤ/ግድም | ይምላዎ | 25/01/2012 | ሞሉ | |
| 6 | ከበደ ተሾመ | ኤ/ግድም | ካራለጎማ | 25/01/2012 | ላይኛው አጣዬ | |

*ሠንጠረዥ 7: በመስከረም ወር 2012 በኤፍራታ ግድም ወረዳ በተፈጠረው ሁከት የቆሰሉ ሰዎች መረጃ*

| *ተ.ቁ* | *የቆሰለው ስም* | *ወረዳ* | *ቀበሌ* | *የቆሰሉበት ቦታ* | *የቆሰለበት ቀን* | *ምርመራ* |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግርማ ደጀኑ | ኤ/ግድም | ላይኛው አጣዬ | ላይኛው አጣዬ | 25/01/2012 | |
| 2 | ሽዋፈር ወንድምነህ | ኤ/ግድም | ላይኛው አጣዬ | ላይኛው አጣዬ | 25/01/2012 | |
| 3 | ሻንበል በልሁ | ኤ/ግድም | ላይኛው አጣዬ | ላይኛው አጣዬ | 25/01/2012 | ሃይማኖትኦርቶዶክስ |
| 4 | ሞገስ አዲሴ | ኤ/ግድም | በርግቢ | ሞሉ | 25/01/2012 | |
| 5 | ኃይለ እንደሸዉ | ኤ/ግድም | ይምላዎ | ሞሉ | 25/01/2012 | |
| 6 | በግዱ ተሸገር | ኤ/ግድም | ካራለጎማ | ላይኛው አጣዬ | 25/01/2012 | |
| ማሳሰቢያ፡- ልዩ ኃይል ሦስት /3/ የቆሰሉ ሲሆን አንድ ደግሞ የሞተ አለ ፡፡ | | | | | | |

### 5.4.20 በሲዳማ ሀገረ ስብከት

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በሲዳማና አካባቢው ሀገረ ስብከት ከዚህ ቀደም በቤተ ክርስቲያናችን ላይ በተደራጀ መልኩ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ብዙም አይታወቁም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ሰለፍ በማድረግ በሲዳማ ዞን፣ ጌዴኦ፣ አማሮና ቡርጂ ዞኖች በአብያተ ክርስቲያናትና በኦርቶዶክሳውያን ላይ በርካታ ጥቃቶች ተፈጽመዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ተገድለዋል፤ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ በርካቶች ተፈናቅለዋል፡፡ እንዲሁም ሀብት ንብረታቸዉ የወደመባቸውም ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም ፡፡ የጥቃቱ መነሻ ምክንያት በዉል በይታወቅም በ2011 ዓ.ም የሲዳማ ዞን የክልልነት ጥያቄ ለመጠየቅ በ11/11/11 አስቀድሞ የተጠራ ሰልፍ ነበር፡፡ በዚህም ዕለት በተለያዩ ከተሞች ሰልፍ የነበሩ ሲሆን፣ ባልታወቀ ሁኔታ ግን ሰልፈኞቹ በሲዳማ እና አካባቢው ባሉ ዞኖችና ወረዳዎች ቤተ ክርስቲያን እና ኦርቶዶክሳውያንን ለይተው አጥቅተዋል፡፡ ጥቃቶቹ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች፣

በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከእስልምና እምነት ተከታዮች ጋር በመጣመር እንደተፈጸመ ለማወቅ ተችሏል፡፡ አጠቃላይ ጥቃት የተፈጸመባቸው ወረዳዎች

1. ዶያ ወረዳ
2. ገተማ ወረዳ
3. ሉዳ ወረዳ
4. ጭሮኔ ወረዳ
5. ሀገረሰለም ወረዳ
6. ቃራሮ ወረዳ
7. ቦና ወረዳ
8. ጩኮ ወረዳ
9. አርቤጎና ወረዳ
10. ይርጋለም ወረዳ
11. አለታወንዶ ወረዳ
12. ቅቄ ወረዳ

ሲሆኑ በነዚህ አካባቢዎች የደረሱ ዝርዝር ጥቃቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1) ዶያ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

በዶያ ወረዳ የሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በ1947 ዓ.ም. በቀኝ አዝማች ወልደየስ ዓለሙ መሪነት በአቶ አስረስ ተስፋዬ ረዳ አስተባባሪነት እና በሌሎችም አባቶች የተመሠረተ ላለፉት 64 ዓመታት ሲያገለግል የነበረ ቤተ ክርስቲያን የተቃጠለ ሲሆን በተጨማሪም የደብሩ የጥምቀተ ባህር መቃኞች ቤትም ጉዳት ደርሶበታል፡፡ በርካታ ምእመናንም ሀብት ንብረታቸው ወድሞ ከመኖሪያ ስፍራቸዉ ተፈናቅለዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያኑን ያቃጠሉት ሰዎች ቁጥራቸው ከዘጠና እስከ መቶ የሚደርሱ ሰዎች በቡድን መጥተው እንደሆነ በወቅቱ የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በምዕመናን ሀብት ንብረቶቻቸዉ ላይ የደረሰዉ ጥቃት

- አሥር አባዎራዎች ንብረቶቻቸዉ የተዘረፋበቸው ሲሆን 18/ አሥራ ስምንት/ አባወራዎች ደግሞ ቤትና ሀብት ንብረቶቻቸው ተቃጥሎባቸዋል።
- ከ10 በላይ የሆኑ ኦርቶዶክሳዊያን የሚቃጠለዉን ቤተ ክርስቲያንን ለማትረፍ ጥረት ሲያደርጉ ቆስለዋል ፤ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።



ስዕል *19*፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች የተቃጠለው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የውጭ ገጽታ



ስዕል *20*፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች የተቃጠለው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ገጽታ

2) **ገታማ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን**

የገተማ ወረዳ የቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በ2008 ዓ.ም በአካባቢው በሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን የተመሠረት ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ሙሉ በሙሉ ተቀጥሏል፣ በምእመናን ላይም ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን የሆኑ ከ70 በላይ የሚሆኑ ንዋያተ ቅዱሳት ሙሉ በሙሉ በእሳት ወድመዋል፡፡

በምእመናን ሀብት ንብረቶቻቸዉ ላይ የደረሰዉ ጥቃት ሲታይ 13 አባዎራዎች ንብረታቸው ተዘርፏ የተረፈው የተቃጥል ሲሆን 20 አባዎራዎች ደግሞ ቤትና ሀብት ንብረቶቻቸው ተቃጥሎባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ 33 አባ ወራዎች ከሙሉ ቤተሰባቸው ጋር ከመኖሪያ ቤታቸዉ ተፈናቅለዋል።



ስዕል 21፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች የተቃጠለው ገታማ ገብረክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቅሪት



ስዕል 22፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች የተቃጠለው ገታማ ገብረክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውጫዊ ገጽታ

3) **ለዲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን**

የለዲ ቅደስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በ1928 ዓ. ም በሣር ቤት ተመስርቶ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን በተፈጸመዉ ጥቃትም የ ቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ንዋያተ ቅድሳት ሙሉ በሙሉ በእሳት ተቃጥለዋል፡፡ እንድሁም በር መስኮትና መንበር ተሰባብሯል። የቤተ ክርስቲያኑ ደጀ ሰላም ሙሉ በሙሉ በእሳት ተቃጥሎኋል ምእመናንም በሃይማኖታቸው ተለይቶ ንብረታቸው ተዘርፏል፡፡ አቶ ሽፈራው ማሞ የተባሉትን አባት በደረሰባቸው ድብደባ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

ማሳያ ፎቶዎች ለዲ ቅዱስ ገብርኤሌ ቤተ ክርስቲያን



ስዕል *23*፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የለዲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ውድመት የደረሰባቸው ንዋያተ ቅዱሳት



ስዕል *24*፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የለዲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የተቃጠሉ ንዋያተ ቅዱሳት



ስዕል 25፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የለዲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የውጭ ገጽታ





ስዕል 26፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የለዲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የተሰበረ በርና የቤተ ክርስቲያኑ ኮርኒስ

4) **ጭሮኔ ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን**

የጭሮኔ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አጥፊዎች የካህናቱን ልብሰ ተክህኖና የሰንበት ተማሪዎች አልባሳትን በመዘረፍ ለብሰው የካህናትን ቆብ አጥልቀው መስቀል በእጃቸው ይዘው በመንገድ ሊይ እየዞሩ ከጨፈሩ በኋላ ተመልሰው ቤተ ክርስቲያኑና ንዋያተ ቅድሳትን በእሳት አቃጥለዋል፡፡ በተጨማሪም የቅዱስ አማኑኤሌ ታቦተ ሕጉ በወቅቱ እንዳልተገኘ ተገልጾ ነበር፡፡

**ማሳያ ፎቶዎች ጭሮኔ ቅዱስ አማኑኤሌ ቤተክርስቲያን**



ስዕል 27፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የጭሮኔ አማኑኢል ቤተ ክርስቲያን ከቃጠሎ የተረፈው የቤተ ክርስቲታኑ የውጭ ገጽታ



ስዕል 28፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የጭሮኔ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ከቃጠሎ የተረፈው የቤተ ክርስቲታኑ ገጽታና ጉዳት የደረሰባቸው ዛፎች

5) **ይርጋ ዓለም ቅደስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርሰቲያን**

**የይርጋ ዓለም ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ በ1909 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን በደረሰው ጥቃትም ሙሉ በሙሉ ተዘርፏል፡፡ አገልግልት እየሰጡ የነበሩ መቃብር ቤቶች በርና መስኮቶች ተሰባብረዋል። ሦስት ኦርቶድክሳውያንም በአሰቃቅ ሁኔታ ተገድለዋል፤ 250 የሚሆኑ ምእመናንም ተሰደው በቦሬ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተጠልለው ነበር።**

*ሠንጠረዥ 3: በሀገረሰላም የተገደሉ ሰዎችን ዝርዝር*

| ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | አድራሻ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ግርማ መልካ | 85 | ወንድ | ሀገረሰላም | በመንገድ ላይ ተገድለዉ የተገኙ |
| 2 | አቶ የኔነህ ተስፋዬ | 50 | ወንድ | ሀገረሰላም | በቤታቸው ጉዳት ደርሶባቸው ሊታከሙ በገቡበት ሀገረ ሰላም ሆስፒታል ከአስታማሚ ልጃቸው ጋር የተገደሉት |
| 3 | ወጣት አዲሱ የኔነህ | 20 | ወንድ | ሀገረሰላም | አባቱን በማሳከም ላይ እያለ የተገደለ |



ስዕል 29፡ ስዕል 23፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የይርጋለም ቅድስት ኪዳን ምህረት ቤተ ክርስቲያን የውጭ ገጽታና የተሰበረ በር



ስዕል 30፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ጥቃት የደረሰበት የይርጋለም ቅድስት ኪዳን ምህረት ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ገጽታ

6) **ሀገረ ሰላም ቅዱስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን**

በውጭ የነበረ ወንበር፣ ጠረጴዛና በሙዲዩ ምጽዋት ውስጥ የነበረው ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ተዘርፏል መስኮትና በር ተሰብሯል።

7) **ጭሪቅ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን**

በር ላይ የሚገኘው መሥተዋት ተሰብሯል።

8) **ቄጨኖ ሴዲታ ማርያም**

2 ባንኮን በግምት 40ሺህ ብር የሚይዝ መጎናጸፍያ፣ ቀጸላ፣ በግምት 25 ሺህ ብር የሚገመት የካህናት አልባሳት፣ በግምት 10ሺህ ብር የሚገመት ጀነሬተር፣ አምፕሊ ፋየርና እስፒከር በግምት 60 ሺህ ብር የሚያወጣ ተዘርፏል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ባደረሱት ጥቃት ከሲዳማ ሀገረስብከት ስር ካሉ ወረዳዎች የተፈናቀሉ ምዕመናን ብዛት

| ተ.ቁ | ከተማ | ብዛት | የተጠለሉበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዶያ | 18 | በየሰው ቤቱ |
| 2 | ገተማ | 33 | በየሰው ቤቱ |
| 3 | ጥሮኒ | 150 | ቦሬ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል አዳራሽ |
| 4 | ሀገረሰላመ | 100 | በወረዳው አስተዳደርምክር ቤት |
| | | 453 | ቦሬ ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል አዳራሽ |
| 5 | ቦና | 4 | በየሰው ቤቱ |
| 6 | አርቤጎና | 2 | በየሰው ቤቱ |
| 7 | በንሳ | 5 | ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርሰቲያን |

ሠንጠረዥ 5፡ ከሐምሌ 11 -14 2011 ዓ/ም ባሉት ቀናት የተደራጁ ወጣቶች ባደረሱት ጥቃት ከሲዳማ ሀገረ ስብከት ስር ካሉ ወረዳዎች ንብረታቸዉ የተቃጠለባቸዉና የተዘረፈባቸዉ ምዕመናን ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | አድራሻ | የተቃጠለባቸዉ ብዛት | የተዘረፈባቸው ብዛት | ቤትና ንብረት የተቃጠለባቸው ምዕመናን (አባወራዎች) ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዶያ | 10 | | 18 |
| 2 | ገተማ | 10 | | 20 |
| 3 | ሉዳ | 12 | 4 | 25 |
| 4 | ጥሮኒ | 28 | | 17 |
| 5 | ሀገረሰላመ | 100 | | 7 |
| 6 | ቃራሮ | 7 | | 1 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | ቦና | 100 | | |
| 8 | ጩኮ | 7 | | 1 |
| 9 | አርቤጎና | 5 | | |
| 10 | በንሳ | 29 | | |
| 11 | ይርጋዓለም | 125 | | |
| 12 | አለታወንዶ | 3 | | 3 |
| 13 | ቅቄ | | | |
| | | | | |

### 5.4.21 ጅግ ጅጋ

ጥር 11 ቀን 2011 ዓ.ም በጥምቀት በዓል ታቦተ ሕጉን አጅበው የሚጓዙ ሁለት ክርስቲያን ወጣቶች በጅግጅጋ ከተማ በእስላሞች ተገድለዋል።

### 5.4.22 ድሬዳዋ

ጥር 11 ቀን 2011 ዓ.ም ታቦተ ሕጉን አጅበው በሚሔዱ ክርስቲያኖች ላይ አክራሪ እስላሞች ድንጋይ በመወርወራቸው ብዙ ጉዳት ደርሷል። በታቦቱ ሰረገላና በክርስቲያኖች ላይ የደንጊያ ውርወራ ጥቃት በመፈጸሙ በተፈጠረ ጠብና ትርምስ በተባራሪ ጥይት የተመታ አንድ ሕፃን ሕይወት ሲያልፍ በ10 ሰዎች ላይ ደግሞ የመቁሰል አደጋ ደርሷል። ከ400 በላይ ሰዎች ለእስር የተዳረጉ ሲሆን ከታሰሩት ውስጥ የሚበዙት የጥምቀት በዓል አከባበር ላይ የተገኙ ወጣቶች ናቸው።

### 5.4.23 መቱ

ሚያዝያ 25ቀን /2012 ዓ.ም ማለትም በዳግም ትንሣኤ ሳምንት በወቅታዊ የኮቪድ-19 ወረርሺኝ ጉዳይ በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ተገን በማድረግ ቅ/ሲኖዶስ በአዋጅ ባወጣው መመሪያ ካህናትና ዲያቆናት ቤ/ክርስቲያን ከፍተው እንዲያገለግሉ ተፈቅዶላቸው እንዳለ እያወቁ በዕለተ እሑድ ካሕናት እና ዲያቆናት ቀድሰው ወጥተው አፋቸውን ሳያቆሩ "እባካቹ እዚ እናውራ ፖሊስ ጣብያ አትውሰዱን ብለው ቢለምኗቸው ግቢ ውስጥ ገብተው ከሌሎች ምዕመናን ጋር ወስደው አስረዋቸዋል።

ግንቦት 8 ቀን 2012 ዓ.ም በቀኑ 10:00 አከባቢ በዕለቱ ኦርቶዶክስ ባለሀብቶችን ብቻ የኮማንደ ፖስትን ህግ ተላልፋችዋል በማለት ወደ ፖሊስ ጣብያ የተወሰዱት:

1) ወ/ሮ ብዙነሽ(ቡዜ) ማሩ

2) ወ/ሮ ትዕግሥት ድንገቱ

3) ወ/ሮ አዜብ ሄኖክ

4) ወ/ሮ አስናቀች ደምሴ

ክላይ ተገለጹት ግለሰቦች ወደ ተዘጋጀው እስር ቤት ከመግባታቸው በፊት ማኅተባቸውን(መስቀላቸውን) እንዲያወልቁ እንዲቆርጡ ተጠይቀው በፍርሐት አውልቀዋል /ቆርጠዋል። ወ/ሮ ብዙነሽ(ቡዜ) ማሩ ና ወ/ሮ ትግስት ድንገቱ ቶሎ ፈርተው አውልቀዋል። ወ/ሮ

አዜብ ሔኖክ ና አስናቀች ደምሴ የተባሉት ደግሞ አልቀረፕ ስላላቸው በምላጭ እንዲቆርጡ አድርገዋል። ከላይ የተዘረዘሩ ክርስቲያኖች ማኅተባቸውን ፖሊስ ሲያስወልቅ በቦታው የነበሩ ሰዎች፡

ሀ. መ/ርት አንድነት ደምሴ

ለ. ወ/ሮ መሠረት

ግንቦት 10ቀን 2012 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:30 ላይ ዲ/ን መ/ር ዮሴፍ ታምሩና መምህር ዋሴ ካሳሁን በቅደም ተከተል የወረዳ ማዕከሉ ሰብሳቢና ፀሐፊ የሆኑት በተራ ቁጥር 2 ላይ የተደረገውን ማዕተብ የማስወለቅ ዘመቻ በመቃወም ማኅበራዊ ብዙኃን መገናኛ ባጋሩት መረጃ ምክንያት ሁለቱም ተይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወስደዋል። እነርሱም በተራቸው ወደ እሥር ቤት ከተወሰዱ በኋላ በተመሳሳይ ሁኔታ ማዕተማቸውን እንዲያወልቁ ተጠይቀው አናወልቅም በማለታቸው ምክንያት በተለያዩ የፖሊስ አባላት ማስፈራሪያ ደርሶባቸዋል። ግርማ የተባለው የፖሊስ አባል ዲ/ን ዮሴፍ ታምሩ ወደ ተባለው መምህር ጠጋ ብሎ ሊመታው ሲቃጣ በሌላ የፖሊስ ባልደረባ ጣልቃ በመግባት ተከላክሎታል። ይህ ጉዳይ ሲፈጸም በቦታው የነበሩ

1) ምሕረት እንዳለ
2) ብልሴ ታምሩ
3) ወ/ሮ ዘርቱ እረና ናቸው

ምንም እንኳን የስልጤ ዞን በመንግስት አወቃቀር በእንዲህ ዓይነት መልኩ ቢሆንም እንደ ዞን ራሱን ከመቻሉ በፊትም ሆነ ራሱን ከቻለም በኋላ ከአካባቢው ጋር የሚኖሩ የተለያዩ ማኅበረሰቦች ፤ ኃይማኖቶች ፤ ባህሎች እና ትውፊቶች እንደነበሩ በግልፅ ይታወቃል። በተለይም ከቀድሞ ጀምሮ በአብዛኛው ወረዳዎች የክርስትና ኃይማኖት ኦርዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መኖሩን በርካታ አስረጂ ነገሮች አሉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት እንኳን በእድሜ የገፉ የሙስሊም አባቶች የሚናገሩት እውነት ይህንኑ ነው፡፡ በተለይም ፋሽስት ጣሊያን በማይጨው ጦርነት በኢትዮጵያውያን አርበኞች ከተሸነፈ በኋላ ለሀገራቸውና ለኃይማኖታቸው የተዋደቁ አባት እና እናት አርበኞች የሞራል ካሳ እና መተዳደሪያ የመሬት ስጦታ ከተበረከተላቸው የሀገራችን ቦታዎች መካከል የስልጤ ማኅበረሰብ ከሚኖርበት አካባቢም እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ አባት አርበኞቻችን ለእራሳቸው የማምለኪያ ቤተክርስቲያን ቦታ ሲያዘጋጁ እና ሲሰሩ ለሙስሊሞችም ማመለኪያ ቦታ መስጂድ እየሰጡ እና እየሰሩ በፍቅር ይኖሩ እንደነበር እነዚሁ የሙስሊም ሽማግሌዎች ይናገራሉ ፡፡ እንደ ምሳሌም የሚጠቀሱ አካባቢዎች ዳሎቻ ወረዳ ላይ አቶ አዘነ ውቤ የሚባሉ ባላባት ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ማምለኪያ ቦታ በመስጠት ፤ ቤተክርስቲያንም በመስራት ብቻ አልነበረም የሚታወቁት ለሙስሊሞችም ማምለኪያ ቦታ እየሰጡ ፤ መስጂድም እየሰሩ ሁሉን እያስማሙ በመከባበር እና በመፈቃቀር ይኖሩ ነበር፡፡ ሌላው ሊጠቀስ የሚችለው ሳንኩራ ወረዳ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ተከታይ አባቶች እና የእስልምና እምነት ተከታይ አባቶች ምን ያህል ተከባብረው ይኖሩ እንደነበር አሁን በህይወት ያሉ ሽማግሌዎች ምስክር ናቸው፡፡ ገራድ ሀጂ ከዲር ተካ የሚኖሩት ሣንኩራ ወረዳ ዓለም ገበያ ከተማ ሣንኩራ መካነ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አጠገብ በ100 ሜትር ርቀት ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን በእስልምና ኃይማኖት የተማሩ ፤ ኃይማኖታቸውንም የሚወድዱ አባት ቢሆንም ለክርስትና ኃይማኖትም ልዩ አክብሮት አላቸው፡፡ ሁሌ የራሳቸውን እምነት ተከታይ ሰዎች ከሚናገሯቸው ንግግሮች መሃል የሚጠቀሰው “ከመድኃኔዓለም ጋር አትነካኩ ፤ አትዳፈሩ” እያሉ ይመክሩ እንደነበር ይታወቃል፡፡



*ስዕል 2፡ ገራድ ሀጂ ከድር ተካ ኦርቶዶክሳውያን መገደል ፤ አብያተ ክርስቲያናትን መቃጠል የለባቸውም ብለው በሙስሊሙ ማኅበረሰብ መካከል በድፍረት እና በእውነት ሲናገሩ*

ይህ አመለካከት እና አስተሳሰብ በሁሉም ወረዳዎች የነበረ በተለይም በቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ሙስሊሞቹ ለክርስቲያኖች ያላቸው ቦታ እና ክብር ልዩ ነበር፡፡ ክርስቲያኖቹም በተመሳሳይ መልኩ ያቀርቧቸው ያከብርቸው እንደነበር አንቱታን ያገኙ እነ ኢማም ፎቶ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሙስሊም አባቶች ሕያው ምስክር ናቸው። በማኅበራዊ ህይወታቸው ፤ በኃይማታዊ በዓላቸው እስከ ቅርብ ዓመታት ይጠያየቃሉ ፤ በፋሲካ ዳቦ እና ለስላሳ ሙስሊሞቹ ይዘው ወደ ክርስቲያኖቹ ቤት ይሄዳሉ ፤ በረመዳን ፍቺ ክርስቲያኖቹ ወደ ሙስሊሞቹ ቤት በተመሳሳይ መልኩ እንኳን አደረሳችሁ ለማለት ገፀ በረከት ይዘው ይሄዳሉ። ይህንን እውነት እነ ገራድ ሀጂ ከድር ተካ አሁንም ጽንፈኞቹ ፤ አሸባሪዎቹ ክርስቲያን ስልጤ ምድር እንዳይኖር በሚፈልጉ ሰዎች  በተሰበሰቡበትም ቦታ ይናገራሉ ፤ ተው ብለውም ይቆጣሉ፤ የሚሰማቸው አላገኙም እንጂ።

ስልጤ ዞን ላይ የዞኑን መመስረት ተከትሎ ከመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የመጡ የአካባቢው ተወላጆች  ከ1994 ዓ/ም ወዲህ ክርስቲያኖችን ማሳደድ ፤ አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል እንደ ትልቅ እቅድ ይዘው መንቀሳቀሳቸው የሚታወቅ ነው፡፡ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱት ምስራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ የቂልጦ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ፤ ሳንኩራ ወረዳ ሳንኩራ መካነ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ጥቅምት 1 ቀን 1994 ዓ/ም የጥምቀተ ባህርና የመስቀል አደባባይ ቦታ አጥሩን ሰብስቦ በማቃጠል የሚገለፁ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ከዚያ በፊትም ቤተክርስቲያናትን በማጥፋት ለምሳሌ ውልባረግ ወረዳ የሌፎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አሁን ተመልሶ ቦታውን ቢይዝም ፤ ሳንኩራ ወረዳ ረግዲና ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን እስከነ ይዞታው በመረከብ ጉልላቱ ላይ ያለውን መስቀል በማውረድ የእነርሱን የአምልኮ መግለጫ የጨረቃ ምስል በማድረግ ቤተክርስቲያኑን ወደ መስጂድነት መቀየሩ የሚታወቅ ቢሆንም በህቡዕ እና በግልፅ ግን ከ1994 ዓ/ም ወዲህ በክርስቲያኖችም በአብያተ ክርስቲያናትም በርካታ ጥቃቶችን አድርሰዋል፡፡ በረከታቸው ይደርብንና የቀድሞ የሀድያ ፤ የከንባታ ፤ የጉራጌ ፤

የሀላባ እና የስልጤ አኅጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አባችን አቡነ መልከጼዴቅ ቀዳማዊ ስልጤ ዞን ላይ የሚከሰቱትን የኃይማኖት ትንኮሳ ለሚመለከተው ሁሉ ሲያመለክቱ እንደነበርም ይታወቃል፡፡ እንዲህ ዓይነት በክርስቲያኖች ላይ እጅግ የመረረ ጥላቻ ማሳደራቸው እንደቀጠለ ቢሆንም በፅሁፍ እቅድ ግን በሁሉም ወረዳዎች በሹመት ላይ ያሉ ካድሬዎች የእቅዱ አስፈፃሚ በመሆን ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ የረጅም ጊዜ እቅድ በማቀድ በ20 ዓመታት ውስጥ ማለትም እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ 2019 ዓ/ም ድረስ በስልጤ ዞን ውስጥ ምንም ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት እና ክርስቲያኖች መኖር የለባቸውም በሚል መርህ በመነሳት ይህንን ለማሳካት በየወረዳው ኮሚቴ በማቋቋም የየወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎችን የኮሚቴው ሊቀመንበር በማድረግ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ሥራ እንደጀመሩም ይታወቃል፡፡

ከማስፈፀሚያ ስልቶች መካከል

1) ሙስሊም ወንዶች ክርስቲያን ሴቶችን በትዳር ማግባት እና ማስለም ካልሆነም ማስነወር እና እንድታረግዝ አድርጎ ማስለም።
2) በተመሳሳይ መልኩ ሙስሊም ሴቶች ክርስቲያን ወንዶችን ማግባት እና ማስለም።
3) ክርስቲያን የመንግስት ሠራተኞችን አለመቅጠር ፤ ዝውውር አለመፈፀም ፤ የተቀጠሩትን ጥቅማ ጥቅም በመንፈግ ፤ የሥራ ጫና በማብዛት ፤ የትምህርት እድል በመከልከል እና በመሳሰሉት ዞኑን ለቅቀው እንዲወጡ ማድረግ።
4) በረመዳን ጾም ፤ በአረፋ በአል እና በሌሎችም ማኅበራዊ በአላት ላይ ክርስቲያኖችን በኢኮኖሚ በመጥቀም ፤ በመደለል ፤ጫት በማስቃም ፤ በአላቱ ላይ በማሳተፍ እና በማታለል ማስለም
5) ት/ቤቶች ላይ ሁሉም ሴት ሙስሊሞች ሂጃብ እንዲጠመጥሙ በማድረግ ሴት ክርስቲያኖች የእነርሱን እንዲከተሉ ሻሽ በማሰር ፤ መስቀላቸውን እንዲበጥሱ በማድረግ ካልተቻለም እንዲሸፍኑ በማድረግ እና በማሳቀቅ ፤ ማንነታቸውንና ህልውናቸውን እንዲጠሉ በማድረግ ፤ ወንድ ክርስቲያኖችን ማሳቀቅ ወደ እነርሱ ባህልና ኃይማኖት በመሳብ ለክርስትና ኃይማኖት ደንታ ቢሶች ማድረግ እና ወደ እስልምና ኃይማኖት መቀላቀል ከያዙዋቸው ማስፈፀሚያ ስልቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

በመጨረሻም በዞኑ ውስጥ ያሉትን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናትን መስቀሉን በማውረድ ፤ ንዋየ ቅድሳቱን በማቃጠል ቤተክርስቲያናቱን መስጂድ ማድረግ ፤ የፕሮቴስታንት አዳራሾችን ወደ የእስልምና መድረሳ ት/ቤት መቀየር ፤ በክርስቲያኖች የተሰየሙ ከተሞችን እና ቦታዎችን ወደ እስላማዊ ስም መቀየር እና ዞኑን ፍፁም እስላማዊ ዞን በማድረግ በሃያ ዓመታት ውስጥ ታሪክ በመቀየር ዓለምን በአንድ መድረክ የመምራት ጽንሰ ሃሳብ መተግበር የሚለውን በ1999 ዓ/ም የረጅም ጊዜ እቅድ አቅደው እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ይህንን የረጅም ጊዜ እቅዳቸውን በሃያ አምስት ገፅ የተፃፈውን ስልታዊ እቅድ እና አስፈፃሚ የኮሚቴ አባላት ዝርዝር የያዘውን በወቅቱ ለነበሩት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ለቡፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ቀዳማዊ ደርሷቸው ብፁዕ አባታችንም በጉዳዩ ተንቀሳቅሰውበት እኩይ ምግባራቸውን አክሽፈውባቸዋል። የስልጤ ዞን አብያተ ክርስቲያናትንና ክርስቲያኖችን ለማጥፋት የተነሱት ፤ ያሰቡት እና ያቀዱት ዛሬ እንዳልሆነ እና ከአስራ አምስት ዓመት በፊት በህቡዕ እና በእቅድ እንደተነሱ ከዚያ በፊት ደግሞ በሃሳብ ብቻ እዚህም እዚያም ሲንቀሳቀሱ እንደነበር መረጃዎች እና ማስረጃዎች ያረጋግጡልናል፡፡ በዚህም እቅዳቸው በተለይም ከዛሬ አስር ዓመት በፊት የተወሰነ እኩይ ስራ በመስራት የኦርቶዶክሳውያንን ቁጥር በእጅጉ ቀንሰውታል፡፡

የስልጤ ዞን እንዳሰቡት እና እንዳቀዱት ቢሆን ምናልባትም በአሁኑ 2014 ዓ/ም 75% እና ከዚያ በላይ ክርስቲያኖችንና አብያተ ክርስቲያናትን አጥፍተው በተገኙ ነበር፡፡ የሰሩት እኩይ ስራ እንደተጠበቀ ቢሆንም ዞኑ ላይ በአሁኑ ሰዓት የአብያተ ክርስቲያናት ከዛሬ አስራ አምስት ዓመት በፊት ካለው ጋር ሲነፃፀር በተወሰነ ቁጥሩ ጨምሯል። እንዲሁም በዞኑ ላይ ያሉት የምዕመናን ቁጥር በተለያየ ምክንያት በመንግስት ሥራ ፤ በንግድ ስራ ፤ በቀን ስራ እና በመሳሰሉት ከሌላ አካባቢ በመምጣት በተወሰነ መልኩ ጨምሯል።

*ሠንጠረዥ 8፡ በስልጤ ዞን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እና ቦታዎቻቸው*

| ተ.ቁ | የወረዳው ስም | የደብሩ ስም | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዳሎቻ | ባልጪ ዳሎቻ ቅ/ድ/ማርያም ቤተክርስቲያን | |
| | | የዳንገቴ ዳሎቻ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን | |
| 2 | ውልባረግ | ውልባረግ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን | |
| | | ውልባረግ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን | |
| | | ሴፎ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን | ካጠፉት በኋላ የተሰራ |
| 3 | ስልጢ | አጅራ ቅዱስ ጊርጊስ ቤተክርስቲያን | |
| | | ዶቦ በደኖ ቅድስት ልደታ ቤተክርስቲያን | |
| | | ጋሮሬ ደ/ሠላም ቅ/አርሴማ ቤተክርስቲያን | |
| | | ቆቶ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን | |
| | | ቅበት አገታ ደ/ስብሃት ቅ/ድ/ማርያም ቤተክርስቲያን | |
| | | ኢሎስ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን | |
| 4 | ሳንኩራ | ሳንኩራ መካነ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን | |
| | | ሳንኩራ ንቡ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን | ካጠፉት በኋላ የተሰራ |
| | | ጀጀብቾ ለምለም ገብረ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን | ከ1999 ዓ/ም በኋላ |
| | | ገተም ጉርባዬ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን | ከ1999 ዓ/ም በኋላ |
| | | ረግዲና ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን /አሁን የሌለ/ | አጥፍተውት የቀረ |
| 5 | ላንፍሮ | ጦራ ደብረ ታቦር ቅዱስ በዓለወልድ ቤተክርስቲያን | |
| | | ላንፍሮ ገባባ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን | |
| 6 | ሚቶ | ሚቶ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን | |
| 7 | ወራቤ | ወራቤ ደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን | |
| | | ወራቤ ማረሚያ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን | ከ1999 ዓ/ም በኋላ |
| 8 | ምስ/አዘርነት በርበሬ | ቂልጦ ፍኖተ ሎዛ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን | አንድ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ |
| | | ቂልጦ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን | |
| | | | |
| | | ሴራ ደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | ምዕ/አዘርነት በርበሬ | ቀጫ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን | |
| | | ሙጎ ቅድስት ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን | |
| 10 | አሊቾ ውሪሮ | ምንም ቤተክርስቲያን የለም፡፡ | |
| 11 | ገርቢ በር | ምንም ቤተክርስቲያን የለም፡፡ | |

- በእያንዳንዱ ወረዳ በአማካይ እስከ 30 ቀበሌ ይኖሩታል፡፡ በአጠቃላይ ከ330 ቀበሌ በላይ በዞኑ ሲገኙ ያሉት አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ግን ከ26 አጥቢያ ቤተክርስቲያናት አይበልጡም፡፡ ይህም ሲሰላ ለ13 ቀበሌ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንደማለት ነው፡፡ የመስጂድ ቁጥር ግን ከአንድ ሺ ሃምሳ በላይ እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የስልጤ ዞን በእንዲህ ዓይነት በሁለቱም ቤተ እምነቶች ንፅፅርም ሆኖ ከዛሬ አስራ አምስት ዓመት በፊት ያቀዱትን ተግባራዊ ለማድረግ ጎንደር ላይ በተፈጠረው የሰዎች አለመግባባት እቅዳቸውን ለመተግበር እንደያመቻቸው በእነ አህመዲን ጀበል ቀስቃሽነት በእነ ሙጂብ አሚኖ አስተባባሪነት በየወረዳው ምእመናንን በመግደል እና በማሳደድ ፤ አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠል ውጥን እቅዳቸውን ለመተግበር በየወረዳው ሰዎች መልምለው አሰልጥነዋል፡፡











*ስዕል 3፡ ሙጂብ አሚኖ*

1) **ሙጂብ አሚኖ፡** ትውልዱ ስልጤ ዞን ውስጥ ነው፡፡ ከእነ አህመዲን ጀበል የጥፋት ተልእኮ በመቀበል የስልጤ ዞንን በበላይነት ከዞን እስከ ቀበሌ ያሉትን አመራሮች በማስተባበር በየወረዳው ለዚህ የጥፋት ተልእኮ ጽንፈኛ እና አሸባሪ ሙስሊም ወጣቶችን በመመልመል እና ስልጠና በመስጠት ለወንጀል የሚያሰማራቸው ግለሰብ ነው፡፡



*ስዕል 4፡ አብድረህማን ዳሪ*

2) **አብድረህማን ዳሪ፡** ተወልዶ ያደገው ስልጤ ዞን ነው፡፡ የሙጂብ አሚኖ ምልምል ሰልጣኝ ነው። ወራቤ ዩኒቨርሲቲ ላይ ኦርቶዶክሳውያንን በማሳቀቅ ፤ በማሸማቀቅ ይታወቃል። በየወረዳው ያሉትን አሸባሪዎች ከሙጂብ አሚኖ መመሪያ እየተቀበለ የሚያስፈፅም መቀመጫውን ወራቤ ላይ አድርጎ የሚሰራ ነው። የወራቤን ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን ከሁሉም በመቅደም ጉልላቱ ላይ በመውጣት እንዲፈርስ እና እንዲቃጠል ሥራውን ያስጀመረ ጽንፈኛ የዋህብየ የእስልምና እምነት ተከታይ ነው።



*ስዕል 5፡ አምራላ ዲልታታ*

3) **አምራላ ዲልታታ፡** ትውልዱም እድገቱም ስልጤ ዞን ፤ ሳንኩራ ወረዳ ዓለም ገበያ ከተማ ነው፡፡ በእግር ኳስ ጫወታ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ክለቦች ለወላይታ ዲቻ ፤ ሀድያ ሆሳዕና በመጫወት ይታወቃል። በአሁኑ ሰዓት ለወራቤ ከነማ እግር ኳስ ክለብ እየተጫወተ ይገኛል። የጥፋት ተልእኮውን ከእነ ሙጂብ አሚኖ እና አብድርህማን ዳሪ እየተቀበለ በሳንኩራ ወረዳ ላይ የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት እና የኦርቶዶክሳውያንን ቤት እንዲፈርሱና እንዲቃጠሉ ያደረገው ከሌሎች ግብራበሮቹ ጋር በመሆን ይኸው ፅንፈኛው አምራላ ዲልታታ ነው።




*ስዕል 6፡ ያሲን ወራቄ ፤ ሀሰን ሽርሞሎ ፤ ፉዓድ ረሺድ እና ሰለሀዲን ኸይሩ*

እነዚህ ስማቸው የተገለፁት ያሲን ወራቄ ፤ ሀሰን ሽርሞሎ ፤ ፉዓድ ረሺድ እና ሰለሀዲን ኸይሩ የተባሉ አሸባሪ እና ፅንፈኛ የወሃቢዬ የእስልምና ተከታዮች ከእነ ሙጂብ አሚኖ ጋር የሚሰሩ ስልጤ ዞን እና በተልእኮ ሌሎች የሀገራችን ክፍሎች በመዘዋወር በጥፋት የተሰማሩ ግለሰቦች ናቸው፡ የእነ ሙጂብ አሚኖን ስምሪት እና የጥፋት ተልእኮ በመያዝ በስልጤ ዞን ላይ የተሰማሩትን ግለሰቦች አንድ ወረዳ ላይ ያለውን መረጃ ብቻ ከዚህ በታች በሚታየው ሰንጠረዥ በስም ዝርዝራቸው የተገለጸ ሲሆን እንዲህ ዓይነቶች ምልምል አሸባሪዎች በየወረዳው እና ከተማ መስተዳደሮች ሰልጥነው በመንግስት እና ከአረብ ሀገራት በሚላክ የገንዘብ ድጋፍ ታግዘው ኦርቶዶክሳውያንን ለመግደል እና አብያተ መቅደሶቻችንን ለማቃጠል የሰለጠኑ በርካቶች ናቸው፡፡

*ሠንጠረዥ 9፡ በዳሎቻ ወረዳ የእነ ሙጂብ አሚኖን ስምሪት እና የጥፋት ተልእኮ በመያዝ በስልጤ ዞን ላይ የተሰማሩትን ግለሰቦች መረጃ*

| ቁ | ስም | የስራቸው ዓይነት | ሚኖሩበት አድራሻ |
|---|---|---|---|
| | በክር ሙንጣዝ | ና ባለሞያ | ቻ ከተማ |
| | ሙሽ ጀማል | ል | ዳሎቻ ከተማ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ለቂን ሽ/የሱፍ | ሏ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ድረዛቅ ሙዲን | ንግስት ባለስልጣን | ዳሎቻ ከተማ |
| | ዲን ሻፊ | ሏ ሥራ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ፉፊቅ ሙዜ | ንግስት ሠራተኛ ሾፌር | ዳሎቻ ከተማ |
| | ዲን ሥርባሮ | ሀብት | ዳሎቻ ከተማ |
| | ፊን ሳኒ | ሏ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ከሚል ምትኩ | ፃሪ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ሽ አብርሐም | ዴ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ዬ ሙዜ | ዴ | ዳሎቻ ከተማ |
| | በ ሙዜ | ንግስት ሠራተኛ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ሩ ሰርጊቾ | ሞህር | ዳሎቻ ከተማ |
| | ከሚል ሱልጣን | ሞህር | ዳሎቻ ከተማ |
| | ሞ | ሞህር | ዳሎቻ ከተማ |
| | ፑር ያሲን | ሞህር | ዳሎቻ ከተማ |
| | ዲን ላሉ | ክትሪሺያን | ዳሎቻ ከተማ |
| | ሞ ሱልጣን | ፃሪ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ድ ሁሴን | ዴ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ኔ በድሩ | ሊስ መኪና ሾፌር | ዳሎቻ ከተማ |
| | ረዲን ዲሎ | ላ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ድ ሁሌ ሸከ | ዴ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ሁሌ ሸከ | ዴ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ኑር ሁሌ ሸከ | ዴ | ዳሎቻ ከተማ |
| | ሐመድ ኡስማን | ንግስት ሠራተኛ ሾፌር | ዳሎቻ ከተማ |

**የሽብር ጥቃቱ የተፈፀመባቸው ቦታዎች**

**1) የሣንኩራ ንቡ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን**

ይህ የቤተክስቲያን ቦታ /ይዞታ/ ጥንት ማለትም ከደርግ ዘመን በፊት የጥምቀተ ባህር ቦታ እንደነበር አባቶች ይናገራሉ፡፡ የሣንኩራ መካነ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ይህ ቦታ ካለበት 1.5 ኪሎ ሜትር ይርቃል። አባቶች የመድኃኔዓለምን ታቦት አክብረው የጥምቀትን በዓል የሚያሳልፉት አሁን የንቡ ቅዱስ ገብርኤል የተሰራበት ቦታ እንደነበር ሁሉም

ይስማማበታል። የደርግ መንግስት ሀገሪቱን ሲቆጣጠር በወቅቱ የነበሩ ስልጤ ሙስሊሞች የመሬት ላራሹን ፖሊሲ በዚህ ቦታ ላይ ተገበሩትና ቦታውን ወሰዱት። ኦርቶዶክሳውያኑም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ከመንገድ የተከፈለውን ቦታ ላይ የጥምቀተ ባህር ፤ የመስቀል አደባባይ እና የማሳረጊያ ቦታ በማድረግ እስከ 1994 ዓ/ም ለማክበር ተቻለ። በ1994 ዓ/ም ይህንኑ የጥምቀተ ባህር ፤ የመስቀል አደባባይ እና የማሳረጊያ ቦታ በእነዚሁ ጽንፈኛ ሙስሊሞች የአጥሩን እንጨት በመነቃቀል አቃጠሉት። በዚህም ህዝበ ክርስቲያኑ ለሚመለከተው ሁሉ አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ቦታው የአረንዴ ስፍራ ነው በሚል ከወረዳው መንግስት ጋር ብዙ በመካሰስ ከብዙ ክርክር እና ክስ በኋላ እስኪወሰን ቦታውን ቤተክርስቲያን እየተጠቀመችው የለውጥ ቦታ በሚል አሁን የተቃጠለውን ቦታ ቀድሞም የቤተክርስቲያን ይዞታ የነበረውን ቦታ ተሰጠ ተብሎ ቦታውን ቤተክርስቲያን ጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓ/ም የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ታህሳስ 18 ቀን 2011 ዓ/ም ቅዳሴ ቤቱን በማክበር የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያንን ሊታነጽ ችሏል፡፡ ከተመረቀ ከሦስት ዓመት በኋላ ሚያዚያ 20 ቀን 2014 ዓ/ም በጽንፈኞች እና አሸባሪዎች የሙስሊም ወሃቢዬዎች ተቃጠለ፡፡



*ስዕል 7፡ ሚያዚያ 20 ቀን 2014 ዓ/ም በጽንፈኞች እና አሸባሪዎች ወሃቢዬዎች የተቃጠለው የሣንኩራ ንቡ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን*

### 2) የቂልጦ ፍኖተ ሎዛ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ገዳም

ይህ ቤተክርስቲያን በስልጤ ዞን ደጋማው ክፍል ምስራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ቂልጦ ከተማ ላይ የተሠራ ወረዳ ውስጥም ብቸው ቤተክረስቲያን ነው፡፡ በርካታ ችግሮችን ፤ ፈተናዎችን ፤ መከራዎችን ያየ ቤተክርስቲያን ነው። አስቀድሞ አካባቢው ላይ ከበርካታ ዓመታት በፊት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እንደነበር እና ቤተክርስቲያን አቃጥለው ፤ የሚቀድሱትን ካህን አርደው ቦታውን እንዳጠፉት የሚያውቁ ሰዎች ይመሰክራሉ። በተለይ በደጋማው የስልጤ ክፍል አሸባሪዎችና ፅንፈኞች የበዙበት አካባቢ በዚህ በቂልጦ ከተማ ነው፡፡ በመንግስት መዋቅር ሳይቀር ምንም ዓይነት ኦርቶዶክሳዊ አማኝም እንዳይኖር ይደረጋል፡፡ ለዚህም ማሳያው በዚያው በምስራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ የፖሊስ አዛዥ የነበረው ኢንስፔክተር ከማል ሳሊህ መሐመድ የተባለው ግለሰብ በ2011 ዓ/ም የፃፈው መጽሐፍ የስልጤ ህዝብ የሙብት ትግል ከጥንት እስከ ዛሬ የሚለው ጽንፈኝነትን ፤ አሸባሪነትን የሚሰብክ የስልጤ ሙስሊም በጉራጌ ፤ በሃድያ እና በአማራ ኦርቶዶክሳውያን እንዴት እንደተበደለ እና እንደተጨቆነ የሚናገር ለዚህም አፀፋ መመለስ ያለበት የስልጤ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ እንደሆነ የሚሰብክ መጽሐፍ ጽፎ

ለየወረዳዎቹ ሲታደል በመንግስት በጀት እንደነበር ደብዳቤውም ከመንግስት መስሪያ ቤት ተፅፎ እንደወጣ መረጃዎች ያሳያሉ፡
፡




*ስዕል 8፡ በምስራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ የፖሊስ አዛዥ የነበረው ኢንስፔክተር ከማል ሳሊህ መሐመድ የተባለው ግለሰብ በ2011 ዓ/ም የፃፈው መጽሐፍ*

ይህ ግለሰብ ምንም ሳይጠየቅ በ2013 ዓ/ም ጡረታ መውጣቱም ይታወቃል፡፡ ምን ያህል በመንግስት መዋቅር እየተደገፈ ክርስቲያኖችን ከዞኑ የማጽዳት ስራ እንደሚሰራ በርካታ አስረጂ ነገሮች ያሉት ወረዳ ነው፡፡



*ስዕል 9፡ የቂልጦ ፍኖተ ሎዛ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ገዳም*

በርካታ እና ተደጋጋሚ ጥቃቶች የተፈጸመበት ምስራቅ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ቂልጦ ከተማ በእነዚሁ ጽንፈኛ ፤ ጀሃዲስቶች እና አሸባሪ ሙስሊሞች በ2004 ዓ/ም ፍኖተ ሎዛ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን አቃጥለዋል፡፡ በተመሳሳይ በ2007 ዓ/ም ቤተ ክርስቲያኑን አቃጥለዋል፡፡ በ2012 ዓ/ም በኮረና ወቅት ክርስቲያኖች ተደብድበዋል ፤ ቤተክርስቲያኑ ዘረፋ ተካሂዶባታል፡፡ በ2013 ዓ/ም የቤተክርስቲያኑን አጥር በመነቃቀል ጥቃት ፈጽመዋል ፤ የንብ ቀፎ ተሰረቋል፤ ለጥበቃ የሚያገለግል መሣሪያ ተወስዶበታል። ይህንን ሁሉ በደል ቤተክርስቲያን ለወረዳው አካላት ፤ ለዞኑ ከፍተኛ አመራሮች ብታመለክትም ሰሚ በማጣት ችግሮቹ እየተባባሱ ሊመጡ ችለዋል። በ2014 ዓ/ም የገዳሙን ዛፎች በማን አለብኝነት ቆርጠው መውሰዳቸው ፤ የስፒከር ድምጽ ረበሸን በማለት የሙብራት ቆጣሪውን ነቅለው መውሰዳቸው ምን ያህል የወረዳው እና የዞኑ መንግስት እንደሚደግፋቸው ማረጋገጫ ነው፡፡ በዚህ ሙሉ ድፍረታቸው ሚያዚያ 21 ቀን 2014 ዓ/ም ቤተክርስቲያኑን ሙሉ በሙሉ እና በገዳሙ ያሉትን ቤቶች በሙሉ እስከ መቃኞ ቤተክርስቲያኑ ጭምር ያወደሙት ሲሆን ይህም በስልጤ ምድር ላይ ኦርቶዶክሳውያን እንዳይኖሩ የታቀደውን እቅድ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ያሳያል።









*ስዕል 10፡ ሚያዚያ 21 ቀን 2014 ዓ/ም በጽንፈኞች የፈረሰው ቤተክርስቲያንና በገዳሙ ያሉትን ቤቶች*

### 3) የሣንኩራ ወረዳ ጀጀብቾ ለምለም ፃድቁ ገብረ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

ይህ ቤተክርስቲያን የሚገኘው በሣንኩራ ወረዳ ጀጀብቾ ለምለም ቀበሌ ነው፡፡ በወረዳው ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ በንጽጽር በብዛት በብሔር አማራዎች ፤ በኃይማኖት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች የሚገኙት በዚሁ በጀጀብቾ ለምለም ቀበሌ ነው። የቤተክርስቲያን መስሪያ ቦታ መጠየቅ ከጀመሩ በደርግ ዘመነ መንግስት ቢሆንም ከበርካታ ዓመታት በኋላ ምዕመናኑ የራሳቸውን መሬት በመስጠት 2012 ዓ/ም የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ጥቅምት 13 እና 14 ቀን 2013 ዓ/ም በብፁዕ አባታችን አቡነ ሕርያቆስ የሀድያና ስልጤ ፤ የከንባታ ሀላባ ጠንባሮ አኅጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቅዳሴ ቤቱ ተባርኮ ቤተክርስቲያኑ ተመስርቷል፡፡ ከዚህ በኋላ በተለያየ ጊዜ እነዚሁ ጽንፈኞች ምእመናንን ሲከሷቸው ፤ ሲያንገላቷቸው እና መከራ ሲያበዙባቸው እንደነበረ ይታወቃል፡፡ እነዚህ አሸባሪዎች በዚህም ሳይወሰኑ ሚያዚያ 21 ቀን 2014 ዓ/ም ቤተክርስቲያኑን እና በቅጽረ ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች በሙሉ አውድመውታል።





*ስዕል ።፡ ሚያዚያ 21 ቀን 2014 ዓ/ም ቤተክርስቲያኑን እና በቅጽረ ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች በሙሉ አውድመውታል የተደረገው የጀጀበቾ ለምለም ጻድቁ ገበረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (ከመፍረሱ በፊት በግራ ከፈረሰ በኋላ በቀኝ)*

4) **የወራቤ ደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን**

የስልጤ ዞን ዋና ከተማ የሆነችው የወራቤ ከተማ ከላይ ከመግቢያው እንደገለጽነው በሀገራችን ካሉ የዞን ዋና ከተሞች በእድሜ ትንሻ እና በጥቂት ዓመታት ውስጥ በፍጥነት ያደገች ከተማ ናት። የከተማዋን እድገት ተከትሎ በርካታ የመንግስትም መንግስታዊ ያልሆኑም ተቋማት መመስረታቸውም የሚታወቅ ነው። የተለያዩ የእምነት ተከታዮች በመንግስት ስራም መንግስታዊ ባልሆኑ ስራዎችም ከተማዋ ላይ መጥተው ይኖሩባታል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኞችም ወደ ከተማዋ ከመጡ ማኅበረሰቦች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ በተለይም ከአዲስ አበባ ሆሳዕና በተሰራው የአስፋልት መንገድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች መቀመጫቸውን ወራቤ ከተማ በማድረጋቸው ከተማው ላይ ከሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ጋር በመሆን የቤተክርስቲያን መስሪያ ቦታ በመጠየቅ ቦታውን ካገኙ በኋላ በወቅቱ የነበሩትን ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ቀዳማዊ የሀድያና ስልጤ ፤ የጉራጌ ፤ የከንባታ ሀላባ ጠንባሮ አኅጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በማስፈቀድ ሰኔ 25 ቀን 1998 ዓ/ም የመሰረት ድንጋይ ተቀመጠ ፡፡ ህንፃ ቤተክርስቲያኑን ሰርቶ ለማጠናቀቅ የፈጀው ጊዜ ስድስት ወር ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ የስድስት ወር ቆይታ ግን ኦርቶዶክሳውያኑ በርካታ ፈተናዎችን አይተዋል፡፡ የአስፋልት መንገድ ሠራተኞች የሚያሰግቧቸውን የግንባታ እቃዎች በመስረቅ ፤ በመደበቅ እንዲሁም ክርስቲያኖች ፀሎት ሲፀልዩ የሚፀልዩበትን ቤታቸው ላይ ድንጋይ በመወርወር ፤ በር በመስበር ፤ በማስፈራራት እና በማጉላላት በርካታ በደሎችን አድርሰውባቸዋል። ይህንን ሁሉ መከራ በመቋቁመው ህንፃው ተጠናቅቆ

ግንቦት 11 እና 12 ቀን 1999 ዓ/ም ቅዳሴ ቤቱ ተባርኮ ቤተክርስቲያኑን ማስመረቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም በኋላ በርካታ ፈተናዎች ቤተክርስቲያኑ እና ምእመናን አሳልፈዋል፡፡

በተለይም የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ከተመሠረተ በኋላ ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡ ተማሪዎች ፤ መምህራን እና የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ መምጣታቸውን ተከትሎ ኦርቶዶክሳውያን በእጅጉ ቁጥራቸው በመጨመሩ ጽንፈኞቹ እና አሸባሪዎቹ ከበፊቱ ይልቅ ፈተናውን ፤ መከራውን በማጽናትና በማበርታት ኦርቶዶክሳውያንን ማስጨነቃቸው የሚታወቅ ነው፡ ፡ የግቢ ጉባኤ መኖር ፤ በዕለተ ሰንበት ወደ ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን በርካታ ምዕመናን ነጠላ ለብሶ የሚሄዱ ኦርቶዶክሳውያን ሲያዩ ፤ የሙስሊም ከተማ ነች በሚሏት በወራቤ ከተማ ሲመለከቱ ይህንን መቀበል የከበዳቸው ብዙዎች ናቸው።



*ስዕል 12፡ በጽንፈኞች ሚያዚያ 20 ቀን 2014 ዓ/ም የወራቤ ደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያንን ሲያቃጥሉ በጽንፈኞቹ ጉዳይ የደረሳባቸው ምእመናን ማከከል*

የኦርቶዶክሳውያን መብዛትና ተጋት ያናደዳቸው ጽንፈኞች ሚያዚያ 20 ቀን 2014 ዓ/ም የወራቤ ደብረ ኃይል ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያንን እና በቅጽረ ግቢ ውስጥ ያሉትን ቤቶች እና ንዋያተ ቅድሳትን በማቃጠል ሲረባረቡ የመንግስት አካላት ዝምታን መመረጥ ብቻ አይደለም ፍቃዳቸውን በመግለጣቸው የተመለከቱ የዩኒቨርሲቲው የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች እና ኦርቶዶክሳውያን ምዕመናን እሳቱን ለማጥፋት ወደ ቤተክርስቲያኑ ሲገቡ ሦስት ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች በእነዚሁ ጽንፈኞች ሲገደሉ በርካቶችን ከባድ እና ቀላል ጉዳት አድርሰውባቸዋል፡፡

### 5) የሣንኩራ መካነ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን

የሣንኩራ መካነ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በሣንኩራ ወረዳ ዓለም ገበያ ከተማ ከተመሠረተች ከ60 ዓመት በላይ /በ1952 ዓ/ም እንደተመሠረተች ይነገራል/ ቢሆነውም ብዙ ፈተናዎች ደርሰወበታል። አሁንም በከፍተኛ ስጋት ውስጥ ያለው ቤተክርስቲያን ነው፡፡





*ስዕል 13፡ የሣንኩራ መካነ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያንአጥር ቤንዚን አርከፍክፈው ሲያቃጥሉት ወጣቶች ደርሰው ያጠፉት*

ቤተክርስቲያኑ በሚያዚያ 2014 ዓ/ም ሊያቃጠሉ በአሸባሪዎቹ ከታሰቡ አብያተ ክርስቲያናት አንዳ ነበር፡፡ በከተማው ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች እና በተወሰነ መልኩ የክልሉ ልዩ ኃይል በመድረስ ከውድመት ድኗል።





<u>ሣንኩራ ገተም ጉርባዬ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ</u>  <u>ሐጂ ሺፋ ሸኩሬ</u>

### 6) ሣንኩራ ወረዳ ገተም ጉርባዬ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን

በአሸባሪዎቹ እና ጽንፈኞቹ ሊቃጠሉ ከታሰቡ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሣንኩራ ወረዳ ገተም ጉርባዬ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አንዳ ነበር። ጽንፈኞቹ ወሃቢዬዎቹ የጀጀብቾ ለምለሙን የፃድቁ ገብረ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን አቃጥለው ወደዚህ ወደ ገተም ጉርባኤ ቅዱስ ሚካኤል ቤክርስቲያን ለማቃጠል አላህ ወአከበር እያሉ ሲሄዱ ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ መካከል መልካም የሆኑ አሉና በቀበሌው በገተም ጉርባዬ የሚኖሩ ባለሀብት እና የሀገር ሽማግሌ ሐጂ ሺፋ ሸኩሬ ከሚኖሩበት ቤታቸው መኪናቸውን አውጥተው ከፈለጋችሁ የእኔን መኪና አቃጥሉ እንጂ ምንም ያላደረጉትን የክርስቲያኖችን ቤት ማቃጠል የለባችሁም፡፡ እባካችሁ ስለ አላህ ብላችሁ ተዉ ፤ ተመለሱ ፡፡ አላህን የምታመልኩ ከሆነ እረፉ ፤ አላህን ፍሩ በማለት ደግነታቸውን አስመስከረዋል፡፡ ሐጂ ሺፋ በአከባቢው ማኅበረሰብ እጅግ የተወደዱ ሰው ስለነበሩ ጽንፈኞቹ ሐጂ ሺፋን አክብረው ሳይሆን ከሌላው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ክፍል ጋር ያጣሉናል በማለት ለጊዜውም ቢሆን ቤተክርስቲያኑን ሳያቃጥሉት ተርፏል፡፡



*ስዕል 14፡ ሣንኩራ ገተም ጉርባዬ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ*

የጽንፈኝነትና ጅሃዲስትነት እንቅስቃሴ ስልጤ ዞን ላይ እንደሌሎች አካባቢዎች በስውር ሳይሆን በግልጽ ሲሆን በየገበያው ፤ በንግድ ተቋማት እና በመሳሰሉት ማስፈራራት ፤ ክርስቲያኖችን በንቀት ማየት ፤ በቡድን በመሆን በመፈክር ማሰማት እና የመሳሰሉትን እኩይ ድርጊቶች ይፈጽማሉ፡፡ በእርግጥ አብዛኛዎቹ መልካም ሙስሊሞች ይህን አሸባሪነታቸውን ባይደግፏቸውም ጽንፈኞቹ ግን በእንቢታቸው እንደቀጠሉ ነው፡፡ በተለይም የየወረዳው እና የከተማ መስተዳደሮች የመንግስት አመራሮች ለጽንፈኞቹ የኋላ ደጀን መሆኑ ፤ አንዳንዴም ገንዘብ እና በሰው ኃይል መደገፋቸው ስልጤ ዞን ላይ የክርስትና ኃይማኖትን በእጅጉ እየፈተነ ያለ ጉዳይ ሲሆን ፤ ክርስቲያኖች በሀገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋ ብቻም ሳይሆን ፍፁም የባርነት ፤ የጭቆና እና የመከራ ጊዜ ማሳለፍ ግድ ሆኖባቸዋል።

## 5.4.54 ጎንደር

በጎንደር ከተማ ከሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተከሰተው ግጭት በሕዝበ ክርስትያኑ ላይ የደረሱ ጉዳቶችን የሚያሳይ አጭር

### የችግሩ ሁኔታ

ይህ ግጭት የተከሰተው በጎንደር ከተማ ከሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን በአካባቢወ በሚንቀሳቀሱ እኩይ ዓላማ ባነገቡ አሸባሪ የጥፋት ሃይሎች ሴራ የተፈጸመና ድርጊቱ የከተማዋን ስም ከማጉደፋ ባለፈ በሁለቱም የሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ነዋሪዎችን ላልተፈለገ የሰዎች ህይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት እና የሥነ ልቡና ችግር ዳርጓል፡፡ በዚህ የለየለት የሽብር ተግባር 7 ኦርቶዶክሳዊያን በሞት የተነጠቅን ሲሆን፣ በሆስፒታል መረጃ ብቻ 52 ኦርቶዶክሳውያን ቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ከ10 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ ቤት ንብረታቸው የወደመ እና የተዘረፈባቸው

ናቸው። ስለሆነም ይህ ግጭት እንዲፈጠር ዋና ዋና የግጭት ገፊ ምክንያቶችን ቅድመ ግጭት፤ በግጭት ወቅት የተከናወኑ እና ድኅረ ግጭት የነበረው ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ቅድመ ግጭት ገፊ እንቅስቃሴወች**

ግጭቱ ከመፈጠሩ በፊት በሃገር ደረጃም ይሁን በጎንደርና አካባቢው ከፍተኛ የሆን የአክራሪ ዉሃቢይዝም እና ጽንፈኛ ብሔርተኞች እንቅስቃሴ እንዳለና ይህም በተለያየ መልኩ ሲገለጽ ቆይቷል። በጎንደርና አካባቢው ከሚያዚያ 18 ቀን ጀምሮ የተከሰተው ግጭት ድንገት የተፈጠረ ሳይሆን ቀደም ብሎ የታቀደበት እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዋናነት ለግጭቱ ገፊ ከሚባሉ ምክኛቶች መካከል፡-

- በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለዉ የአክራሪ ዉሃቢይዝም እና ጽንፈኛ ብሔርተኞች እንቅስቃሴ ካለፉት 4 ዓመታት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ በደሎች እና ሴራዎች ሲፈጽም የነበረ ሲሆን በችግሩ ተሳታፊ የሆኑ ጥፋኛ ግለሰቦችና ተቋማት አለመታረማቸዉ ወይንም መንግስት የህግ የበላይነትን አለማስከበሩ ለሌሎች አክራሪዎች የልብ ልብ መስጠቱ
- በ2012 ዓ.ም ለሽብር ስራ ከቱርክ አዝሚር የወደብ ከተማ በ10 ኮንቴነር የጦር መሳርያ ተጭኖ ወደ ሃገር ዉስጥ ለማስገባት በተደረገው ሂደት ዉስጥ 7ቱ ጎንደር ተወልደዉ ያደጉ ነጋዴዎች የነበሩበት መሆኑ (ማስረጃው በብሔራዊ ደህንነት መስሪያ ቤት የሚገኝ እና በወቅቱ በፋና እና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ማሰራጫዎች በዶክመንተሪ መልኩ የቀረበ)
- **አህመድያ ሐምዛ** በተባለዉ ግለሰብ አማካኝነት ከ 1 ዓመት በፊት ወደ ጎንደር ከተማ በሱዳን በኩል በድብቅ የገባ ኮንቴነር መሳሪያ ተጭኖ የደረሰበት አለመታወቁ ነገር ግን ከሰሞኑ በነበረው ግጭት የተማረኩ አክራሪ ሙስሊሞች ማን እንዳስታጠቃቸው በጸጥታ ኃይሉ ሲጠየቁ በስም የተገለጸው አህመድያ ሐምዛ እንደሆነ መናገራቸው ( ማስረጃ፡ - የቀድሞው የጎንደር ከተማ ከንቲባ አቶ ሞላ መልካሙ፤ እና የደህንነት ተቋሙ)
- በ 2000 ዓ.ም እርዚቅ ኢሳ የተባለ የመዘጋጃ ቤት ኃላፊ ፈቃድ ለ600 ዓመታት የልደታ ታቦት መዉረጃ ቦታ ሆኖ በሚያገለግለው ቦታ ላይ በአክራሪወች በኩል በድፍረት መስጊድ ማሰራቱ ያስነሳዉ ችግር (ከአካባቢው ህዝብ የተገኘ ምስክርነት)
- በ ጥር 12/ 2002 ዓ.ም በጥምቀት በዓል ላይ አራዳ አካባቢ ከሚገኙ የንግድ ህንጻዎች ላይ ሆነዉ በቅዱስ ሚካኤል ታቦት ላይ የጫት ገረባ በመወርወራቸው እና በወቅቱ ችግር ፈጣሪዎች ላይ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ አለመወሰዱ ያመጣው የሽብር ልምምድ (ከበቂ በላይ የሰው ምስክር ማቅረብ የሚቻልበት)
- በጠዳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በጠየቀዉ የማስፋፊያ ቦታ ላይ በኮረኔል ዘለቀ አስተባባሪነት በቤተ ክርስቲያን ቦታ ላይ ሙስሊሞች ከመንገድ አልፈው ከእነሱ የቀብር ቦታ ጋር በማይገናኝ እና በጭራሽ በማይዋሰን ቦታ ላይ ሙስሊሞች በድፍረት ለመቅበር ያስነሱት ረብሻ (የአካባቢው ህዝብ የሚመሰክረው)
- ከ1408 ዓ.ም ጀምሮ በጎንደር ቀዳሜ አድባራት አበራ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስር በነበረ የይዞታ ቦታ ላይ በ2002 ዓ.ም ፣ በ 2010 ዓ.ም ፣በ 2013 ዓ.ም ረመዳን ጾም ወቅት እና 2014 ዓ.ም ተደጋጋሚ የይዞታ ቦታ በመጋፋት ሙታንን ለመቅበር በሚያደርጉት የጠብ አጫሪነት ተግባር የተለያዩ ግጭቶች መነሳታቸዉ፣ ነገር ግን ቦታዉ በሚያስነሳው ግጭት ምክንያት ችግሩን ከስሩ ለመቅረፍ በማሰብ በወቅቱ የነበረው የመንግስት አመራር ለሙስሊሞች

ትክ የሚሆን ቦታ ጌታው ሸህ አሊ በሚባለው አካባቢ የጠየቁትን ትክ የቀብር ማስፋፊያ እንደተሰጣቸው (የከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የሚገኝ ማስረጃ)

- በየዓመቱ ሁሌም የግራኝ አህመድ የልደት ቀን ካለከበርን እያሉ ከአረብ አገር በሚመጣ ድጋፍ እና በአክራሪወች በሚዘወር ፋይናስ ሁሌም ቀጠናውን የሁከት ማእከል ለማድረግ የሚጣር እንቅስቃሴ ( ማስረጃ፡- የጎንደር ዙሪያ ወረዳ)
- 2012 ዓ.ም ጎንደር ዙሪያ ወረዳ በእንፍራንዝ ፍርቃ ተክለሃይማኖት በባህልና ቱሪዝም በቅርስነት የተመዘገበ ቦታን ቤተ ክርስቲያን አይሰራም በሚል አክራሪው ያስነሳው ግጭት ( የወረዳው ባህል እና ቱሪዝም፤ የአካባቢው ነዋሪ እና የጎንደር ዙሪያ ወረዳ ቤት ክህነት እና የማዕከላዊ ጎንደር ሀገረ ስብከት የሚያውቁት)
- በጎንደር ከተማ ባሉት አድባራት ልክ መስጊድ እንሰራለን በሚል ከየአድባራቱ ጎን የግለሰቦችን ቤት እየገዙ ከህግ ውጭ መስራታቸው (በተለያየ ጊዜ ከአብያተ ክርስቲያናት አቅራቢያ የተገዙ እና የእስልምና ትምህርት መስጫ ቤቶች/ መስጊዶች)
- የግለሰብ መኖሪያ ቤቶችን ከህግ አግባብ ውጭ መስጊድ ማድረጋቸው
- የብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ እና የክልሉ ቅርስ መስተዳድር ቢሮ ሃላፊ የሆኑት እና የቀድሞ የጎንደር ምክትል ከንቲባ በነበሩት በአቶ እርዚቅ ኢሳ የስልጣን ዘመን ዋና ከንቲባው በስራ ምክንያት ወክለዋቸው እንደሄዱ ሳይመለሱ ከዚህ በፊት ሆኖ በማያውቅ ሁኔታ በአንዴ 14 የመስጊድ ቦታወችን አፅድቀዉ የላኩበት ሙሉ ቃለ ጉባኤ ማስረጃዉ በእጃችን መኖሩ፡፡
- የጎንደር ጅምናዚየም ባለቤት የሆነው **አብድልቃድር ሙሀመድ** ጎንደር ላይ በየአካባቢዉ ወጣቶችን አደራጅቶ የሽብር እና የጅሀድ ስልጠና ሲሰጥበት የነበረዉ ከ120 በላይ የሽብር ማሰልጠኛ ማንዋሎች፤ 130 በላይ ተቀጣጣይ ፈንጅወች እና የተለያዩ የባንክ ደብተሮች እና ደረሰኞች እጅ ከፍንጅ መያዛቸዉ ፡፡ (ማስረጃ፡- የጎንደር ከተማ ፖሊስ መምሪያ፣ የጎንደር ከተማ ኮሙኒኬሽን በወቅቱ የዘገበው ዘገባ፣ ብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት)
- በ 2013 ዓ.ም ቀበሌ 10 አካባቢ የጃዋር ሙሀመድን ምስል የያዙ ቲሸርቶችን በመልበስ የግብፅ እና የኦነግን ባንዴራ በማዉለብለብ የኢትዮጵያን ባንዲራ በመርገጥ እና በማቃጠል ላይ እንዳሉ በመንግሰት የፀጥታ አካላት እጅ ከፍንጅ መያዛቸዉ (የከተማው ፖሊስ መምሪያ፤ የአካባቢው ነዋሪዎች)
- በ2013 ዓ.ም የረመዳን ፆም ወቅት ላይ በምሽት የሚቀሳቀሱ መስቀል ያለባቸው ባጃጆችን ከመስጅድ ቆይተው ሲወጡ መደብደብ እና የተለጠፈውን መስቀል ከባጃጆች ላይ በማንሳት ብጥብጥ ለመፍጠር መጣራቸው (በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች የተያዘ መረጃ)
- ለመማሪያ ብቻ የተፈቀደላቸዉን ቦታዎች ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የድማፅ ማጉያ በመስቀል ሙሉ በሙሉ የመስጊድ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸዉ (በጠቅላላው 11 ሲሆኑ ለአብነት ያህል፡- ቀበሌ 17፣ ቀበሌ 14 ገብርኤል ፊት ለፊት ፣ቀበሌ 06 ቂርቆስ ወረድ ብሎ፣ ቀበሌ 13 አባጃሌ ተክለ ሐይማኖት ጀርባ )
- ከ2013 መጨረሻ ጀምሮ በተለይ በዚህ ዓመት እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ በየሰበብ አስባቡ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ከተማ አቀፍ በሚጠሩ የመንግስት የስብሰባ መድረኮች ሙስሊሞች ጎንደር ላይ ተጨቁነናል በቅርቡ የሚፈነዳ ቦንብ አለ የሚነሳ እሳት አለ እያሉ አበክረዉ ሲያስጠነቅቁ መቆየታቸዉ (ማስረጃ፡- በተደረጉ የተለያዩ ስብሰባዎች የተሳተፉ ሰዎች እና መድረክ የመሩ አመራሮች ሊመሰክሩ የሚችሉት፡፡ በተለይ ቀበሌ 12 እና 10 አካባቢ የሚኖሩ ሙስሊሙን እንወክላለን የሚሉ ሰዎች የተናገሯቸው፡፡ ለዚህም በቂ መረጃ ማቅረብ የሚቻል መሆኑ)

- በጎንደር ከተማ ቅዳሜ ገበያ ፣ቀበሌ 18 እና ጃናሞራ ሰላምጌ ቀበሌ ላይ የሽብር ማሰልጠኛ ቦታወችን አዘጋጅተዉ ሲያሰለጥኑ እና ሲያስታጥቁ መቆየታቸዉ (ማስረጃ፡ የሰው ምስክሮች)
- የ2014 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ላይ ሙህመድ አልቃድር የተባለ አክራሪ ሽብር ለመፍጠር ተቀጣጣይ ፈንጅ ይዞ በጥቆማ እጅ ከፈንጅ የተያዘ እና በመንግስት ቁጥጥር ስር የዋለው አክራሪ ሙስሊም አሸባሪ።

ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ችግሩ ምን ያህል እንድቆየና ለዓመታት ሲሰራበት የነበረ መሆኑንና ከሚያዚያ 18 2014 ጀምሮ የተከሰተው ግጭት የነዚህ የተጠራቀሙ ችግሮች መገለጫ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች ምንም እንኳን በዚህ ሪፖርት ማካትተት አስፈላጊ ባለመሆኑ ባይካተቱም በትክክል ተሰንደው የተቀመጡ መሆናቸውን ለማሳሰብ እንወዳለን።

**ለግጭቱ መነሳት ወቅታዊ የሆኑ ምክንያቶች**

ከላይ የተጠቀሱት ለዓመታት ሲሰራባቸው የነበሩ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው በወቅቱ ቸግሩ እንዲፈጠር ገፊ ከሆኑ ምክኛቶች መካከል፡-

- የረመዳን የቅድመ ዝግጅት አካሄዶች ያለምንም የከተማ አስተዳደሩ ፍቃድ በጎንደር ከተማ በፒያሳ አካባቢ የጎዳና ላይ አፍጥር ይካሄዳል እየተባለ በመገኛ  ብዙሀን ይደረግ የነበረው ትንኮሳ  እና ዛቻ ማስፈራራት የመንግስትን ባለስልጣናት ስም በማንሳት ከባህር ማዶ እና ከሀገር ውስጥ አካላት ጋር በመቀናጀት ዘመቻ ማካሄድ  በተለይም **ቢላል ቴሌቪዥን፣ ሀሩን ሚድያ ፣ ዛውያ ቴሌቪዥን ፣Abu sumeya Dinu** የፌስ ቡክ ገጽ( ዛውያ ቴሌቪዥን ባለቤት)፤
- የረመዳን ጾም ከገባ በኋላ ይህንን ችግር ለመፍጠር ወደ ጎንደር ከተማ የገቡ የሽብር ጠማቂዎች የነበሩ መሆኑ እና የግጭቱ ዕለት ከከተማው መውጣታቸው (በቂ የምስል መረጃ በእጃችን ያለ ሲሆን የአውሮፕላን በረራ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት የሚቻል መሆኑ)
- ከአሁን በፊት የነበሩ የጦርነት ጉሰማወች እና እንዲሁም የታሪክ ማጠልሸት አካሄድ በተለይም በአፄ ቴወድሮስ ላይ የነበሩ ዘመቻዎች በአህመዲን ጀበል እንዲሁም በሌሎቹ አክራሪዎች በኩል "**ኪነት ያገነነው አፄ**"  ብለው መቀስቀስ ከዚያ በኋላ ደግሞ የወጣቱን ስስ ብልት በማወቅ ሆን ብለው አፍጥር በቴወድሮስ አደባባይ ብለው መቀስቀስ እና ለነውጥ ማነሳሳት (ከበቂ በላይ የምስል እና የቪድዮ ማስረጃዎች ያሉበት)
- በአፍጥር ስም ሲካሄድ የነበረው እንቅስቃሴ ቦታው ከፒያሳ ውጭ ሌላ ቦታ አናደርግም ብለው ከመንግስትም ሆነ  ከትላልቅ የእምነቱ አባቶች ጋር ሳይስማሙ መቅረታቸው
- ወደ ቀብር  ቦታ ሲሄዱ ሆን ብለው ተዘጋጅተውበት ተቀጣጣይ  ፈንጅ ይዘው መውረዳቸው
- ከቀብር ምላሽ የነበረውን የነውጥ እንቅስቃሴ በዛውያ እና ሀሩን፣  በቢላል ቴሌቪዥን  የቀጥታ ሽፋን መስጠታቸው ግጭቱ ሆን ተብሎ ተዘጋጅተውበት ሀገር አቀፍ ነውጥ ለማስነሳት ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት የተሰራ ለመሆኑ ቀጥተኛ ማሳያ ነው
- በረመዳን ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተከፈተው የባንክ ደብተር ከአከፋፈቱ ጀምሮ ችግር ባለበት መንገድ አካውንቱ ተከፍቶ ህገወጥ የገንዘብ ምንጭ ሆኖ ማገልገሉ እና አካውንቱን የከፈተው ግለሰብ **ጅዋር ሙህመድ ሀጎስ** ከህውሐት ጋር ግንኙነት ያለው ሰው መሆኑ

**በግጭቱ ወቅት የተፈጠሩ ሁኔታዎች**

- በ18/08/2014 ዓ.ም የተፈጠረው ችግር በክርስቲያኖች ተንኳሽነት አለመሆኑን ከቀብር ቦታው አዋሳኝ ከሆነው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ፤ አገልጋይ ካህናት፤ የአብነት ተማሪዎች፤ እና ከአካባቢው ማሕበረሰብ ጋር ባደረግነው ማጣራት የደረስንበት ሲሆን ቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነች አገልጋዮች በምንም መንገድ ግጭቱ ውስጥ ያልተሳተፉ መሆኑን አረጋግጠናል።
- በ18/08/2014 ዓ.ም ግጭቱ የተባባሰው በዋናነት ግጭት ቀስቃሾች አካላት ሰው በቦንብ ፍንዳታ እንዲሞት ካደረጉ በኋላ ነውጥ ለመፍጠር እየመሩ ወደ ከተማ ማምጣታቸው እና ቅዳሜ ገበያ አካባቢ ብቻውን የተገኘ አንድ ታዳጊ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን በገጀራ፣ በፌሮ ብረት እና በተለያዩ የእጅ መሳሪያዎች "**አሏህ አክበር**" እያሉ ቀጥቅጠው መግደላቸው በከተማው ያለውን ህዝብ ያስደነገጠ እና ከባድ ቁጣ የቀሰቀሰ ጉዳይ መሆኑ ( በቪድዮ የተደገፈ ማስረጃ አለ)
- በዕለቱ ማለትም በ18/08/2014 ዓ.ም ፒያሣ አካባቢ ከሚገኘው አዲስ መስኪድ እና ቀበሌ 12 አካባቢ ከሚገኘው የእጨጌ ቤት (ሙስሊሞች የሚኖሩበት ቤት ነው) ከፍተኛ ቁጥር ያለው ገጀራ መገኘቱ እና በፖሊስ ኢግዚቢትነት መያዙ እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪዎች ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑ።
- የፒያሣውን ርግብ በር መስጊድ በተቀነባበረ ሁኔታ ለማቃጠል ተቀጣጣይ ርችት ሲተኩሱ መታየታቸው እና ከመስጊዱ ጎን የነበሩ ሱቆች በርችቱ መንደዳቸው (ርችት ሲተኮስ የቪድዮ ማስረጃ አለ)
- በዕለቱ በዚህ ድርጊት የተበሳጨው ሰው ንፁሀን ሙስሊሞችን እንዳያጠቃ እና ጉዳት እንዳይደርስባቸው ከመንገድ እየሰበሰቡ በየአብያተ ክርስቲያኑ ተጠልለው  እና ችግሩ እንደበረደ ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲቀላቀሉ መደረጉ ( ለአብነት በመንበረ መንግስት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን እና በደብረ ገነት አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን)፤
- ችግሩ እንደተፈጠረ የአክራሪው እስልምና ኃይል ከውስጥ ካለው ኃይል ጋር በመናበብ በከፍተኛ ደረጃ ዓለም አቀፍ የሚዲያ ዘመቻ በማድረግ ለህዝቡ የተሳሳተ መረጃ ሲሰጥ የቆየ መሆኑ
- በዕለቱ በተለያዩ የቴሌግራም ቻናሎች በኦርቶዶክሳውያን ላይ ጅሀድ ሲያውጁ እና "**ክርስቲያኖችን ግደሉ፣ ከወዳጆቻችሁ፣ ከጎረቤቶቻችሁ ጀምሩ፣ በሽንኩርት ቢላዋም ጭምር ግደሏቸው**" እያሉ ለተጠናከረ የሽብር ስራ ሲያዘጋጇቸው ማደራቸው (ከቴሌግራም ገጾቻቸው የተወሰዱ የድምጽ መልዕክቶች ማስረጃ) (**ኤሊያስ አዲሳለም ቀቤለ 8 ተወላጅ ኖሪነቱ አዲስ አበባ )**
- በ19/08/2014 ዓ.ም የአማራ ክልል የእስልምና ምክር ቤት ምንም ተጨባጭ መረጃ በሌለው ሁኔታ ላይ ያወጣቸው ፍጹም ስህተት እና ቤተ ክርስቲያኒቱን ጨፍጫፊ አድርጎ ያወጣው ኦርቶዶክሳያንን ያሳዘነ አሸባሪዎችን የልብ ልብ የሰጠ መግለጫ (በሰነድ የተቀመጠ)
- በ20/08/2014 ዓ.ም በግጭቱ የሞቱ ሙስሊሞችን ለመቅበር የወጣውን ህዝበ ሙስሊም ወደ ብጥብጥ ለመከተት እና የባሰ ነውጥ ለመፍጠር በማሰብ በተለይም በጎንደር ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ከ7 በላይ በሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ግለሰቦች ህንጻዎች ላይ እና በመኖሪያ ቤቶች አድፍጦ በመቀመጥ አክራሪው የሽብር ቡድን በከባድ መሳሪያዎች የታገዘ ከ3 ሰዓታት በላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ህዝባችን እየተኮሰ  ውጊያ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በዚህም ችግሩ አስቀድሞ የተዘጋጁበት የሽብር ተልዕኮ መሆኑን ያመላክታል። በዚህ ውጊያ 2 የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ተገድለዋል። ዋናው የአክራሪው የጦር መሪ ቆስሎ

ሲማረክ ሌሎቹም በየቦታው በፈቃዳቸው ለመንግስት ኃይሎች እጃቸውን ሰጥተዋል፡፡ ( ማስረጃ፡- የአካባቢው ማሕበረሰብ፣ የመንግስት የጸጥታ ተቋማት)

- ትላላቅ የቡድን መሳሪያወችን በመተኮስ እና ንጹሀንን በመግደል ሲያሸብሩ መዋላቸው እና ማደራቸው በዚህ ተግባርም እጅ ከፍንጅ ቆስለው መያዛቸው እና ህክምና በሚሰጡበትም ቦታ ከአንዴ ሁለት ሦስቴ እራሳቸውን ቀይረው ሊያመልጡ ሲል መያዛቸው (**ለምሳሌ አብዱ አዱኛ አደም** )
- በ20/08/2014 ዓ.ም በአክራሪው የእስልምና ኃይል በተደረገው ከፍተኛ የጦር ሽብር የተማረኩ እና የቆሰሉ ከሱዳን የመጡ/ የሱዳን ፓስፖርት የያዙ/ ሙስሊም የህውሃት ሰዎች መገኘታቸው። (ማስረጃ፡- የፖሊስ መረጃ እና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል)
- በ20/08/14 በከተማ ውስጥ ባሉ በተመረጡ ታላላቅ ህንጻወች እና የመስጊዶች የመጨረሻ ፎቅ ላይ ሁነው ሲያዋጉ የነበሩ ሰዎች መኖራቸው ( ማስረጃ፡- የምስል ማስረጃ የሚቀርብባቸው)፤
- በተሳሳተ እና በተለያየ መታወቂያና ፓስፖርት ሲንቀሳቀሱ ቆስለው መያዛቸው (**አንዋር አህመድ/ሙሉ ደሳለኝ ሀጎስ**)
- ቀበሌ 10 አካባቢ በአንድ ቤት ውስጥ ብቻ ከ35 በላይ አክራሪ ውሃቢያውች ሲዋጉ ውለው ከነ ሙሉ ትጥቃቸው (ብሬል መትረየስ፣ ስናይፐር፣ ክላሽ እና ገጀራ) እጃቸውን ለመንግስት ኃይሎች መስጠታቸው፡፡
- ሙሉ መረጃው በ2ኛ ፖሊስ ጣቢያ የሚገኝ ቢሆንም የአሸባሪው አክራሪ ኃይል ሙሉ ጭምብል በተገለጠበት በ20/08/2014 ዓ.ም በነበረው ከጦርነት ያልተናነሰ ውጊያ በዕለቱ ከአክራሪው ኃይል የተማረኩ ብዛት ያላቸው ብሬን፣ መትረይሶች፣ ስናይፐሮች፣ ክላሾች፣ የእጅ ቦንቦች እና የተለያዩ መሳሪያዎች በመንግስት እጅ ገብተዋል። ( ማስረጃው በሙሉ በ2ኛ ፖሊስ ጣብያ እና በአስተዳደር እና ጸጥታ በኩል ይገኛል።)
- የክርስቲያኖችን ቤት በእጅ ቦንብ ወርውረው ማውደማቸው (ጃፋር በሚባል ግለሰብ ቅዳሜ ገበያ ቅቤ ለምኔ ዘይት ቤት አካባቢ 2 የክርስቲያን የንግድ ቤቶች ከነንብረታቸው የወደመባቸው፤ የወ/ሮ አጸደ ታደሰ ቤት ቀበሌ 07) (ማስረጃ፡- በአካቢው የሚኖሩ ሰዎች ምስክር እና የወደሙ ቤቶች)
- ከህወሀት ፣ከሳምሪ ፣ከኦነግ ሸኔ፣ከአልሸባብ የሽብር ቡድኖች ጋር እጅግ በተናበበ እና በተቀናጀ ሁኔታ መስራታቸዉን በደረሱን የአካል ጉዳት የሆስፒታል ማስረጃወች እና የባንክ ደብተር እንዲሁም የቀበሌ መታወቂያ ማረጋገጣችን ጉዳዩ ከጀርባዉ የሌላ አካላት መሰረታዊ ፍላጎት ማስፈፀሚያ መንገድ መሆኑን ያስረዳል (**ጅዋር ሙህመድ ሀጎስ**)
- በግጭቱ ወቅትም ሆነ በኋላ ይወጡ የነበሩ እጅግ ከእውነት የራቁ መረጃወችን ማሰራጨት። ለአብነት ያህል አንድም መስጊድ ሳይቃጠል 12 መስጊዶች ተቃጥለዋል ፣ የሞቱ ሰወች ከ50 በላይ ነው ብሎ ማስነገር መቀስቀስ፣ ጎንደር የደም ምድር መንቀሳቀስም ሆነ መስራት አልቻልንም እያስባሉ ሚዲያዎች ላይ ማስነገራቸው
- ከዓለም አቀፍ የእነሱ ሀሳብ ደግፈው ከሚቀሳቀሱ ሚዲያዎች ጋር በቅንጅት መስራት (ከግብጽ፣ከቱርክ፣ ከአልጀዚራ)
- ከግጭት በኋላ በሚፈጠሩ መድረኮች ዕጅግ በተናባበ እና በተቀናጀ መልኩ በመግባት እኛ ብቻ ተበደልን በመንግስት ጫና ተደረገብን እያሉ ስህተታቸው እንዳይወጣ እና እንዳይታወቅ በመንጋ መዝመት የሀይማኖት አባቶችን የመንግስት ባለስልጣናትን ማጠልሸት (ጎንደር ላይ የተደረጉ መድረኮች) ።

**የጉዳት መጠን ትንታኔን**

ከ18/08/204---21/08/2014 ባሉት ቀናት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ብቻ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በድንገተኛ ክፍል እና በመለስተኛ ቀዶ ጥገና ክፍል የታከሙ ኦርቶዶክሳውያን የሸብር ተጎጅ ታካሚወች ብዛት 46 ሲሆን ህይወታቸው ያለፉ ኦርቶዶክውያን ብዛት 7 ነው።

*ሠንጠረዥ 10፡ ከ18/08/204---21/08/2014 ባሉት ቀናት በነበረው ጥቃት ሕይወታቸውን ያጡ ምእመናን*

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጻታ | የህክምና ካርድ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ገሉ ገበየ | | ወ | |
| 2 | ገ/ስላሴ | | ወ | |
| 3 | ስሙ ያልታወቀ | | ወ | 1038299 |
| 4 | ስሙ ያልታወቀ | | ወ | 1038087 |
| 5 | ስሙ ያልታወቀ | | ወ | 1038069 |
| 6 | በዱላ እና በስለት ተቀጥቅጦ በመጀመሪያው የተገደለ ልጅ | 17 | ወ | ያልገባ |
| 7 | ጊዮርጊስ አካባቢ የነበረ ከመንግስት የጸጥታ ኃይሎች በተባራሪ በብሬን ጥይት ተመትቶ የሞተ ልጅ ሆስቲታል ሳይገባ ደባርቅ የተቀበረ | | ወ | ያልገባ |
| 8 | ከ38 ኩንታል በላይ በርበሬ የተቃጠለባት ሴት በራስ መጨናነቅ እራሷን ያጠፋችበት ሁኔታ | | ሴ | ያልገባ |

*ሠንጠረዥ 11፡ ከ18/08/204---21/08/2014 ባሉት ቀናት በነበረው ጥቃት ተጎድተው ህክምና ሲከታተሉ የነበሩ ምእመናን ዝርዝር*

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጻታ | የህክምና ካርድ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ደርሶ ክብረት | 40 | ወ | 1038054 |
| 2 | አቡሽ ከተማ | 22 | ወ | 1037955 |
| 3 | መቅደስ ሰንደቁ | 22 | ሴ | 1037960 |
| 4 | አሰፋው ወረቀት | 30 | ወ | 1037517 |
| 5 | ባበይ ሻንቆ | 25 | ወ | 1038393 |
| 6 | መኩሪያው አየለ | 35 | ወ | 1037826 |
| 7 | ነፃነት ፀዳለ | 42 | ወ | 1037883 |
| 8 | ነጋ አዲሱ | 23 | ወ | 1037885 |
| 9 | ብርሃኑ እሸቴ | 28 | ወ | 1037829 |
| 10 | ቢኒያም አዱኛ | 20 | ወ | 1037888 |
| 11 | ብሬ ታከለ | 40 | ወ | 1037855 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 12 | አስናቀ ደሴ | 12 | ወ | 1038140 |
| 13 | አድየ መንግስቱ | 40 | ሴ | 1038158 |
| 14 | ስማው አለሙ | 22 | ወ | 1038145 |
| 15 | አስንቅ ጌቱ | 18 | ሴ | 1038118 |
| 16 | ዳዊት ነብዩ | 19 | ወ | 1038228 |
| 17 | ጌታቸው ዘገየ | 18 | ወ | 1038253 |
| 18 | መልካሙ ተሾመ | 25 | ወ | 1037924 |
| 19 | ደጀን አለሙ | 40 | ወ | 1038057 |
| 20 | አላምር ሲሳይ | 25 | ወ | 10389128 |
| 21 | ሙሉቀን ዋጋ | 36 | ወ | 1038127 |
| 22 | ሀብታሙ አለሙ | 32 | ወ | 1038135 |
| 23 | እንግዳው ጌጡ | 19 | ወ | 1037990 |
| 24 | ሙሉቀን ደሴ | 36 | ወ | 1037920 |
| 25 | ድረስ አስፋው | 37 | ወ | 1038171 |
| 26 | ደሴ አለሙ | 27 | ወ | 1037781 |
| 27 | ደረጀ አስፋው | 32 | ወ | 1038160 |
| 28 | ያለው ተረፈ | 31 | ወ | 1038209 |
| 29 | እንየው መሳፍንት | 25 | ወ | 1029057 |
| 30 | ዮርዳኖስ የሻው | 11 | ሴ | 109316 |
| 31 | አዛናው አስረስ | 21 | ወ | 1038175 |
| 32 | አማረ ተክሉ | 53 | ወ | 1037451 |
| 33 | ባዘዘው አድነ | 43 | ወ | 1024007 |
| 34 | መልካሙ ተሾመ | 25 | ወ | 1037924 |
| 35 | እናዳልከ ሙሉ | 27 | ወ | 143526 |
| 36 | ኤርሚያስ ሲሳይ | 17 | ወ | |
| 37 | ፈለጉሽ ውድነህ | 28 | ሴ | |
| 38 | ሀብቴ ታደሰ | 50 | ወ | |
| 39 | አበበ እንየው | 42 | ወ | |
| 40 | አብይ ጣሰው | 50 | ወ | |
| 41 | ጫቅሌ ጺጋ | 65 | ወ | |
| 42 | አዲሴ አግንቸው | 32 | ወ | |
| 43 | ሞገስ ምህረት | 22 | ወ | |
| 44 | ያለው ደሴ | 23 | ወ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 45 | ዳዊት ምህረቱ | 27 | ወ | |
| 46 | አዛናው አሻግሬ | 21 | ወ | |

*ሠንጠረዥ 12፡ ከ18/08/204---21/08/2014 ባሉት ቀናት በነበረው ጥቃት ጉዳታቸው ከፍተኛ ሆኖ ቀዶ ጥገና የተሰራላቸው ኦርቶዶክሳውያን ታካሚዎች*

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | የህክምና ካርድ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፈንታሁን ታድሎ | 20 | ወ | 1037057 |
| 2 | ያለምበር አበራ | 30 | ወ | 1038031 |
| 3 | አምሳሉ ታምሩ | 17 | ወ | 1038090 |
| 4 | ባበይ ተገኘ | 39 | ወ | 1037782 |
| 5 | መብራቱ ቀኘ | 40 | ወ | 1038248 |
| 6 | ወንዜ ተዘራ | 40 | ወ | 1038255 |

*ሠንጠረዥ 13፡ ከ18/08/204---21/08/2014 ባሉት ቀናት በነበረው ጥቃት በኦርቶዶክሳውያን ንብረት ላይ የደረሰ የንብረት ውድመት በጥቂቱ*

| ተ.ቁ | ንብረት የወደመባቸው እና የተዘረፉ ኦርቶዶክሳውያን | የተሰማሩበት ዘርፍ | ቀበሌ | ሰልክ | የጉዳት ደረጃ | የገንዘብ ግምት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አንደበት ሀብቱ | ሞባይል ጥገና እና አክሰሰሪ | 05 | 0918409269 | ሙሉ ለሙሉ | 1,466,097 |
| 2 | ምስጋናው ወርቁ | ሞባይል ጥገና እና አክሰሰሪ | 05 | 0918155855 | ሙሉ ለሙሉ | 184,000 |
| 3 | ሔለን ባየ | ሞባይል ጥገና እና አክሰሰሪ | 05 | 0912132624 | ከፊል | 8000 |
| 4 | የኔነሽ ዱቤ | የበርበሬ ቢጋዝን ዝርፍያ | 09 | 0918729641 | 38 ኩንታል ሙሉ በሙሉ | 262,200 |
| 5 | ሙላት አያሌ | ምርጥ ዘር እና ፕላስቲክ | 09 | 0918046733 | ሙሉ በሙለሉ | 750,000 |
| 6 | ብርሃኔ ይርጋ | የፕላስቲክ ምርቶች ማከፋፈያ | 09 | 0918733195 | ሙሉ ለሙሉ | 300,000 |
| 7 | ደረጀ ልጃለም | ካፌ እና ሬስቶራት | 11 | 0918770423 | ሙሉ በሙሉ | 180,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የወ/ሮ አፀደ ታደሰ | መኖርያ ቤት | 07 | | ሙሉ ለሙሉ | 900,000 |
| 9 | | | | | | |
| 10 | | | | | | |
| | **በአጠቃላይ በጥቂቱ** | | | | | **4,050,297** |

### 5.4.55 በምሥራቅ ሸዋ ሃ/ስብከት በ2014 ዓ.ም በቤተ ክርስቲያናችን እና በምዕመናን ላይ የደረሱ ጥፋቶች እና ጉዳቶች

የምሥቅ ሸዋ ሃ/ስብከት በሥሩ 12 ወረዳ ቤተክህነት እና 408 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ከወቅታዊ አፅራረ ቤተክርስትያን ጋር በተያያዘ በተለይም ከኦነግ ሸኔ እና የአክራሪ እስላም ጥምር እንቅስቃሴ  በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በተለያየ ግዜ ጥቃቶች በመፈፀም ላይ ይገኛሉ። በስጋት ላይ የሚገኙ ምዕመናን እና አጥቢያዎች ይገኛሉ።ከነዚህም በሃገረ ስብከቱ የአዳማ ፣ ቦሰት (ሆለንጪቲ) እና ፈንታሌ ( መተሓራ) ወረዳዎች ላይ በጣም በተደጋጋሚ ጉዳት እየደረሰባቸው ያሉ ወረዳዎች ናቸው፡፡ የምሥራቅ ሸዋ ዞን ዋና ከተማ የሆነቸው አዳማ ከተማ በ2012 እና 2013 ዓ.ም በኦሮሚያ በነበረው ጥቃት  ምእመኑንና ቤተክርስቲያናትን ጥቃት ለማድረግ ሙከራዎች ተደርገው ፤ አጽራሪያን የሚጠብቁትን ያህል ጥቃት ሳያፈጽሙ በመቅረታቸው እና ብዙ ኦርቶዶክሳዊ የሚኖርበት ከተማ በመሆኑበአሁኑ ወቅት አንዱ የጥቃት ኢላማ ከተማ ናት፡፡ ምሥራቅ ሸዋ የኦርቶዶክስ የበላነት ያለበትና ቅይጥ ማንንት የሚታይበት ዞን በመሆኑ ፤ የኦሮሚያ የፖለቲካ ዋና እምብርት ተደርጎ ሰለሚታይ ውስብስብ ችግሮች ሊያጋጥሙት የሚችል ሃ/ስብከት ነው፡፡   አሁን እያጋጠሙ ያሉ  ችግሮችን ለአብነት ያክልም፡-

1) <u>አዳማ ወረዳ ቤተክህነት ስር እየደረሱ ያሉ ጥፋቶች</u>

- **አዳማ ከተማ፡-**  ባለቤትነቱ የቤቴክርስቲያን የሆነው የጥምቀተ ባሕር ቦታ ፤ በከተማው ማስተር ፕላን መሠረት የስፖርት ሜዳ በሚል ተሠርቶ ተወስዷል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትጠቀመው የከተማ መስተዳድሩ ሲፈቅድ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም  በከተማው የሚገኙ አብዛኞቹ አጥቢያዎችን ካርታና ፕላን ላለመስጠት እያጓተቱ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ የና/ደ/ታ/ም/ጸ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤ/ክ ለ40 ዓመታት ስትጠቀምበት ከነበረው ይዞተዋ ፡፡  7 ሄክታር መሬት  በከተማ መስተዳድሩ ግፊትና ጫና በፍ/ቤት ለግለሰቦች እንዲወሰን ተደርጎ ቤ/ክኗ በይግባኝ እየተከራከረች ነው፡፡
- ከአዳማ ከተማ በ 14 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው  **በአዳማ ወረዳ ቤተክህነት ስር በሚገኘው ሮጌ ባለወልድ** አጥቢያ አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች ከኦነግ ጋር በመደራጀች አንዳንድ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛል። በአጥቢያው 142 አባወራዎች የሚኖሩ ሲሆን ጥቃቱ እየተፈጸመባቸው ያሉ አካባቢዎች ገንደ መምሬ ፣ ገንደ ጭቋላ ፣ጮሮቃ እና ባቶ በመባል ይታወቃሉ። በአካባቢው የነበረ አንድ ኦርቶዶክሳዊ ግለሰብ ከነልጁ የተገደለ ሲሆን የአጥቢያውን ካህናትም ብር አምጡ በማለት እያስፈራሩ ስለነበር ካህናቱ ከቦታው ወጥተው አገልግሎቱ ላልተወሰነ ግዜ ተቋርጦ የነበረ ሲሆን ፤ በአዳማ ወረዳ በሚኖሩ ምእመናን ድጋፍ ከተወሰነ ግዜ በኋላ አግልግሎቱ አልፎ አልፎ እንዲሰጥ ተደርጎ ነበር። በተጨማሪም ሁለት ጥበቃ በመቅጠር ደብሩ  እንዲጠበቅ ለማድረግ ተሞክሯል። በጥቃት አድራሾቹ የተገደሉት ምእመናን ስም አባት ደብሩ አበበ እና  ልጅ ታደሰ ደብሩ ይባላሉ።  ማታ በቤታቸው እራት እየበሉ በቤታቸው ላይ ተኩስ በመክፈት ልጅ በር ለመዝጋት ሲነሳ ደረቱን በመምታት አባትን ደግሞ ግንባራቸው ላይ በመምታት ገድለዋቸዋል።  መሞታቸውን ካረጋገጡ በኋላ የአቶ ደብሩን ባለቤት አስረው በመግረፍ እና በማንገላታት መሳሪያ

ዘርፈው ሔደዋል። የሟቹ አባውራ ቤቱ ከቤተክርስቲያኗ ጎን ሲሆን ሰውዬው ዝክር በመዘከር የሚታወቅ እና ሃይማኖታዊ ሱታፌው ከፍተኛ የነበረ ነው። በተለይ የጥምቀትን በዓል ከብት በመጣል (በማረድ) ጭምር እያዘከረ ምዕመናንን ይመግብ ነበር። በተመሳሳይ ጊዜ ስሙ ያልታወቀ ሌላ ሶስተኛ ሰው በነዚሁ ኃይሎች ተገድሏል። በተጨማሪም የአጥቢያው አስተዳዳሪ መልአከ ብርሃን ለማ ጋር በመደወል እንዲሁም ባለቤታቸው ጋር ጭምር ተዘጋጁ በማለት እና ብር እንዲሰጧቸው አስፈራርተዋቸዋል። የደብሩ አለቃ ባለቤታቸው የምትሰራበት ሱቅ በእነዚሁ ሃይሎች ተዘርፏል። በአጥቢው ያሉ ምዕመናን ይህንን ዛቻ እና ማስፈራራት በመፍራት ከትውልድ ቀያቸው በመሰደድ ወደ ዋቄ ፣ አዋሽ እና አዳማ ላይ በመፍለስ ላይ ይገኛሉ፡፡ እኒሁ ኦርቶዶክሳዊ ምዕመናን ከመኖርያ ቤታቸው ተሰደው ወደ ሌላ ቦታ ከሄዱ ባኋላ ንብረታቸው በዚሁ ኃይል እንዲቃጠል ተደርጓል። በተለይም ግዜው የአዝመራ ወቅት በመሆኑ፤ ከአውድማ ላይ የነበረ የእህል ክምሮች በብዛት ተቃጥለዋል፡፡ ጥቃቱን የሚፈፅሙ የነበሩ አካላት እናንተ አማራዎች በማለት ነበር ጥቃቱን ሲፈፅሙ የነበሩት፡፡ የጥቃቱ ተጎጆዎች በሙሉ ኦርቶዶክሳዊያን ብቻ ነበሩ፡፡



*ስዕል 15፡ በጥቃት ፈጻሚዎቹ የተገደለው ወጣት ታደሰ ደብሩ*

ከዚህም በተጨማሪ በ22/ 04/2014 ከለሌቱ 5 ሰዓት 4 ሰው ገድለዋል። እነሱም፡-

1) መንግስቱ ዘነበ
2) መኮንን ጥበቡ
3) ገብሬ መንግስቱ
4) ቢንያም ይባላሉ

**ሮጌ ባለወልድ** ቤተክርስቲያን ጥንታዊ ሲሆን የብራና መፀሐፋትና የተለያዩ ቅርሶች ያለበት ነው። በአሁን ሰዓት የአጥቢያም ምዕመናን ወደ አጎራባች ቦታዎች ተሰደዋል ቤተ ክርስቲያኑ ምንም ጥበቃ እየተደረገለት ባለመሆኑ በከፍተኛ ስጋት ላይ ይገኛል። በተያያዘ ጉዳይ ባቶ ደጋጋ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ስጋት ያለበት ደብር ነው፡፡

2) **በቦሰት ወረዳ ቤተክህነት ስር እየደረሱ ያሉ ጥፋቶች**

ቦሰት ( ሆለንጭቲና ) እና ፈንታሌ ወረዳዎች በሃረር መስመር ወደ አፋር ክልል መሄጃ የሚገኙ በመሆናቸው ፤ በአሁኑ ሰዓት የኦሮሚያ ነጻነት ሠራዊት (መንግሥት ሸኔ በማለት የሚጠረው ኃይል) በከፍተኛ ሁኔታ የተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ናቸው፡ ፡ የአካባበው የመንግሥት መዋቅርም በነዚህ ጽንፈኞች የተጠለፈ ነው፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ብዙ ክርስቲያኖችና ከመንግሥት ጋር ሆነው ለሃገር አንድነት ይሠራሉ ተብለው የሚታሰቡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሃገር ወደዳ ግለሰቦች የተገደሉበት አካባቢ ነው፡፡

- በቦሰት ወረዳ ደንገሬ መድኀኔዓለም ቤተክርስቲያን በ27/08/14 ቀሲስ ቴዲ፣ ዲ/ን እሱባለው፣ ቀሲስ ጎሹ የሚባሉ ካህናት ከሁለት ምዕመናን የደብሩ ሰበካ ጉባኤ አባላት እና ሰንበት ተማሪዎች ታግተዋል። አንዱን የታገተ ወጣት ምዕመን እናት መቶ ሺ ብር ተከፍሎ እንዲለቀቅ ተደርጓል። የተቀሩት ታጋቾችም በነፍስ ወከፍ 100ሺ ብር እየከፈሉ እንዲፈቱ ነግረዋቸዋል፡፡ በ01/09/14 ደንገሬ መድኀኔዓለም ቤተክርስቲያም የተቃጠለ ሲሆን የቃጠሎው መጠን አካባቢው ላይ ሔዶ ማየት አስቸጋሪ በመሆኑ ለማወቅ አልቻለም። አካባቢው ላይ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች በብዛት ስላሉ እና ወደ ደብሩ እሳቱን ለማጥፋት የሚሔዱ ምዕመናንን ስለሚጠቁሙአቸው ምዕመናን ወደ ደብሩ ሔደው እሳቱን ማጥፋት አልቻሉም። ከዚህም በተጨማሪ በወረዳው በቁርቁራ በዓለ ወልድ ቤ/ክ በሌሊት እንዳታገለገሉ ተብለው የተከለከሉ ሲሆን፣ነኔ ማርያም፣ፌጦ ገብርኤል ፣ጨሌ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያናትም ካህናቱ አገልግሎት እንዳያገለገሉ ተከልክለዋል። ምክንያቱ ምንድነው ሲባል ከነርሱ ጋር ተቀላቅሎ ሰላይ ይገባል ስለዚህ አገልጋዮቹን እንዳይመጡ በሚል ነው። አሁን ላይ በቦሰት ወረዳ ከተማዋ እና ለአማራ ክልል አጎራባች ቦታዎች ብቻ ያልተያዙት ሌሎቹ ሁሉም ቦታዎች በሙሉ በኦሮሚያ ነጻነት ሠራዊት (ሸኔ) ተይዟል፡፡
- ጨሌ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ከምሽቱ 2፡30 አካባቢ ወደየቤታቸው በሜድ 7 ኦርቶዶክሳውያንን በማገት ለመለቀቅ በነፍስ ወከፍ 300 ሺብር እንዲከፍሉ የጠየቋቸው ሲሆን ከታገቱት መካከል 3ቱ ብሩ እንዲቀነስላቸው በመደራደር 200ሺ ብር ከፍለው የተለቀቁ ሲሆን የተቀሩት 4ቱ ብር እንዲቀነስላቸው በመለመን ላይ እያሉ የተባለውን ብሩን ማቅረብ ስላልቻሉ ተገድለዋል፡፡ አሬሳቸው እንኳን አልተገኘም በደም የተጨማለቀ ልብሳቸው ብቻ የተገኘ ሲሆን አሁን ቤተሰባቸው የመረረ ሃዘን ላይ ይገኛሉ፡፡
- በ 05/09/2014 ፌጦ ገብርኤል በ4 ሰዓት የደብሩን ጥበቃ ገድለዋቸዋል። ከዚህ በፊት የእህል አዝመራውን ዘርፈውት እና የጥበቃ መሳሪያውን ወስደውበት የነበረ ሲሆን በምሽት ቤተ ክርስቲያኑን የጠበቁ የነበሩ ሁለቱንም ጥበቃዎችን ውጡ ብለው ካስወጡአቸው በኋላ ከደብሩ በታች ባለ ቦታ አንደኛውን ጥበቃ የገደሏቸው ሲሆን ሁለተኛው ጥበቃ ደሞ አምልጠዋል። የአመለጡት ጥበቃ ስለማንነታቸው ሲጠየቁ ፀጉራቸውን ያሳደጉ እና የኦነግ ታጣቂ እንደሆኑ ገልፀዋል።

3) **ፈንታሌ ወረዳ ቤተክህነት ስር እየደረሱ ያሉ ጥፋቶች**

- በፈንታሌ ወረዳ ጡጡጢ ደ/መንክራት ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስፋልት ዳር ሆነው ምፅዋተ ሙዳይ በመጠበቅ እና ገንዘብ በመሰብሰብ የነበሩ አንድ ካህን በተጨማሪም በጡጡጢ ደ/መንክራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አገልጋይ የሆኑት ቀሲስ ወርቁ ሞገስ የሚባሉ ካህን በቦታው ላይ የነበሩ ህፃናት እንደገለፁት በአካባቢው ከነበረ ጫካ

የወጡ ሶስት ሰዎች በ13/06/14 ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ በአራት ጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፍል። ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ጅቡቲ ሲመጣ የነበረው የከባድ መኪና አሽከርካሪ ካህኑ ሲጠብቁት ከነበረው ሙዳየ ምፅዋት መባ ሰጥቶ እና ተባርኮ ለደቂቃዎች ከኋላው እየመጣ የነበረውን የከባድ መኪና አሽከርካሪ ጓደኛውን ሲጠብቅ የነበረ ሲሆን ከጓደኛው ጋር በነበረው የስልክ ልውውጥ ካህኑ ያሉበት ቦታ መድረሱን እና ከእሳቸው ጋር እያወራ እንደሆነ ተነጋግረው ከአፍታ ቆይታ በኋላ ተነስቶ ጉዞውን ይጀምራል። በቀጣይ እየመጣ የነበረው ከባድ መኪና ቦታው ላይ ሲደርስ ካህኑ ተመተው ሕይወታቸው ማለፉን ሲያይ ቀድሞ ከሳቸው ጋር እንደነበረ ለነገረው ጓደኛው ደውሎ የሆነውን ይነግረዋል። የተነገረውም የከባድ መኪና አሽከርካሪ አካባቢው ወደ ነበረው አጥቢያ በመግባት እዛ ለአገልግሎት ተሰብስበው ለነበሩ ሰዎች ጉዳዩ እንዲጣራ መረጃውን አድርሷል። ይህንን የሰሙት ሰዎች ወደ ቦታው ደውለው ሁኔታው ገልፀዋል መረጃው የደረሳቸው በቦታው ላይ ሔደው ሲያጣሩ የካህኑ ሕይወት አልፎአል። በተፈፀመው አሰቃቂ ግድያ ምክንያት አስከሪኑን ማቆየት ስላልተቻለ በማግስቱ በጠዋት እንዲቀበሩ ተደርጓል። ይህን እና ይህንን በመሳሰሉ ጥቃቶች ሐገረ ስብከቱ በተደጋጋሚ እና በቅርብ ርቀቶች እና ግዜያት ልዩነት መሰል ጥቃቶች በመከሰት ላይ ይገኛሉ።ተመሳሳይ ችግሮች ወደፊትም ሊከሰቱ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል። በግዜ መፍትሔ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው።ከዚህም በተጨማሪ ወረዳው ሀሪቦና ማርያም ፣ጡጡጢ ገብርኤል በተያያዥ ጉዳዮች አደጋ የተጋረጠባቸው ደብራት ናቸው፡፡




*ስዕል 16፡ በ13/06/14 በታጣቂዎች የተገደሉት ቀሲስ ወርቁ ሞገስ*

- በፈንታሌ ወረዳ አልጌ ኪዳነምህረት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ተሰብስበው DSTv እያዮ ያሉ 40 ወጣቶች ላይ በተከፈተ ተኩስ 10 ሰዎች በኦነግ ሸኔ በሚባል ተገድለዋል። የቆሰሉትም ወደ ህክምና ለመውሰድ መንገድ ተዘግቶ ስለቆየ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር።በዚህም ምክንያት ድርጊቱ በተፈፀመ ማግስት ጠዋት ነው ቆስለው አዳማ ሆስፒታል በመውሰድ ህክምና እንዲያገኙ ተደርገዋል። የሚቾች ስማቸውም

    1. ሙሉቀን
    2. ታደለ ኤልያስ
    3. ልዑል መለሰ
    4. ቡቸች ዳንኤል (ጽዮን)
    5. ዘሪሁን ደምሴ
    6. ሔኖክ
    7. ቢንያም ወልዴ
    8. ደባልቀው እሸቱ የተገደሉ ልጆች ናቸው።






*ስዕል 17፡ በእለቱ የተገደሉ ወጣቶች ፎቶ*

**4) በቦራ (ዓለም ጤና) ወረዳ የተፈፀመ የንብረት ስርቆት**

በቦራ ወረዳ ዶዮ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ፅላት በመስከረም 25/2014 ዓ.ም የተሰረቀ ሲሆን ፅላቱን የማፈላለግ ሥራ ሳይሰራ ቀርቷል፡፡ ፅላቱን እንደሰረቁ ሲጠረጠሩ የነበሩት ካህን ለህግ የተጠቆሙ ቢሆንም ከአካባቢው ላይ ንብረታቸውን እና ቤተሰቦቻቸውንን አሸሽተው ከቦታው ተሰውረዋል፡፡ ሃገረ ስብከቱም በተሰረቀው ፅላት ምትክ ከዝዋይ ተወስዶ በቦታው እንዲተካ አድርጓል፡፡

# 6 ማጠቃልያ

በየጊዜው የሚከሠተውን እንዲህ ያለውን ችግር ለማስወገድ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ በየደረጃው በአገልግሎት ላይ የሚገኙ አካላት ከመንግሥት ጋር በመተባበር መሥራትና አውቀው የሚያጠፉትን የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ማጋለጥ ይገባል።

## 6.1 ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚጠበቀው

ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኗ የበላይ እረኛ በመሆኑ በየዕለቱ ስለመንጋው ውሎና አዳር መከታተልና መጠበቅ ፤ ማሰማራት አማላካዊ አደራው ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ እና ልጆቿ በአክራሪዎች፣ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በባለ ሥልጣናት እና በመንግሥት ጭምር ጥቃትና በደል ሲደርስባቸው፣ በገዛ ሀገራቸው ግፍ ሲፈጸምባቸው ጊዜና ማንኛውም ሁኔታ ሳያዘገየው ቀድሞ መድረስ መፍትሔ ማቅረብ ገባዋል። የሚፈጸመውን እኩይ ድርጊት ለማጋላጥ ቀዳሚ መሆንም ይገባዋል። የሚደርሰውን ጥቃት በመከላከል ሂደትም የሚመለከታቸው ወገኖች ምን ማድረግ እንዳለባቸው እና እርምጃቸው ምን መምሰል እንዳለበት አቅጣጫ በመስጠት የመምራት ሚናውን መወጣት ይኖርበታል። ተናግሮ ለመሰማት፣ አድርጎም ለማሳየት

ቅዱስ ሲኖዶስ አምላካዊም፣ ሕጋዊም፣ ሞራላዊም ኃላፊነት አለበት። የአቅምም ብቃትና የትክክለኝነት መሠረት ያለው በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተ ክርስቲያን ልዕልና ማስጠበቅ ዘመኑ የሚጠይቀው ኃላፊነት ነው። ከተግባራቱ መካከልም፡-

ሀ. ጉዳዩን ወደ ሕግ መውሰድ፡- የመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎችን ለማነጋገር እና የዲፕሎማሲም ሆነ ሌሎች ተግባራትን በማከናወን ለተጎጂዎች ቶሎ ደርሶ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እንዲያገግሙ፣ እንዲጽናኑ እና እንዲበረታቱ ለማድረግ አስፈላጊውን የመረጃ መረብ ዘርግቶ ጥቃቶች ሳይፈጸሙ ቀድሞ ጥቆማና ማስጠንቀቂያ መስጠት የመጀመሪያው ተግባሩ ነው። በኦርቶዶክሳውያን ላይ ጥቃት የሚፈጽሙ የሌሎች እምነት ተከታዮችን መሪዎች አማኞቻቸውን ሥርዓት እንዲያስይዙ ማድረግ፣ በዚህ መፍትሔ ካልተገኘ ጉዳዩን ለሕግ ማቅረብ ይገባል። የጥቃት ፈጻሚዎችንና የመንግሥትን እኩይ ድርጊትና ሴራ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማጋለጥም ቸል ሊባል አይገባም። ችግሩ እንዴት በዘላቂነት እንደሚወገድ ምእመናን እንዲወያዩ ማድረግም ይገባል።

ለ) ቅዱስ ሲኖዶስ አስተዳደራዊ እና ሌሎች ጉዳዮች እንዳሉበት ቢታወቅም ቤተ ክርስቲያ እየወደመች፣ ምእመናንን የሰው አውሬ እየበላቸው ሆደ ሰፊ መሆን የለበትም። ከዚህ ሌላ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር የለም። ማኅበረ ቅዱሳንም ሆነ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ማኅበራት፣ ወጣቶችና ክርስቲያኖች ለተፈጻሚነቱ ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል። በቤተ ክርስቲያን በየደረጃው በአገልግሎት ላይ ያሉ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማገዝም ይገባል።

ሐ) ቅዱስ ሲኖዶስ አስተባባሪነት በሁሉም ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ያሉትን ክርስቲያኖች የማምለኪ ቦታዎችና ገዳማትን ለማከበር ግልጽ ዋስትና እንዲሰጥየሚቻለውን ሁሉ መሥራት ይገባዋል። በሁሉም ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች በኦርቶዶክሳውያን ላይ የሚደርሰውን ግፍ ተከታትሎ ለሕግ የሚያቀርብና ዘመኑ ባስገኘው መሣሪያ ለዓለም የሚሰራጭበትን አሠራር መዘርጋት ይገባል። በቤተ ክርስቲያንና በየደረጃም ሥልጣን ላይ በሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች በመተባበር የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸትም ሌላው ተጋባር ነው። ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በመላው የአገሪቱ ክፍል በኦርቶዶክሳውያን ላይ የደረሰው ግድያ፣ የንብረት ውድመት፣ የአምልኮ ቦታ መነጠቅ ከመነገር በላይ ነው። የተፈጸመው ገጽታ ማጠልሸት፣ የተከተለው ስደት ምርመራ ተድርጎ፣ ተቄጥሮ፣ ተመዝኖ የሥነ ልቡና ሕክምና የገንዘብ ካሳ ያስፈልገዋል።

## 6.2 መንግሥት

የመንግሥት ግምባር ቀደም ተግባር ሕግና ሥርዓትን ማስከበር በመሆኑ ክርስቲያኑ "መንግሥት ይጠብቀኛል" ብሎ እምነት እንዲጥልበት የሚያደርግ ተግባር መፈጸም ይገባዋል። ኃላፊነቱን ይልተወጣ ወይም ግዴታውን ወደ ጎን በማለት አድሎ የሚፈጽምን አካል ተጠያቂ ማድረግ ይኖርበታል። የቤተ ክርስቲያንን መቃጠል፣ መዘረፍና በኦርቶዶክሳውያን ላይ እየተፈጸመ ያለውን እንዳልሰማ እያለፈ ቢሆንም ይህን ማስቆም ይገባል። በገሃድ የተፈጸሙ ጭፍጨፋና ግፎች ደግሞ ጉዳዩን ፍጹም ተቃራኒ መልክ በመስጠት በግለሰቦች መካከል እንደ ተፈጠረ ተራ ግጭት እንዲዘገብ እየተደረገ እውነታን እያሳፈነ ነው፡፡

የመንግሥት ባለሥልጣናት በግጭቶች ውስጥ መሳተፋቸው በጅማ፣ በሐረርጌ፣ በድሬ ዳዋ በግልጽ ታይቷል። ከሐረርጌ እስከ ጅማ፣ ከወለጋ እስከ ወሎ፣ ከወልቂጤ እስከ ጅግጅጋ በኦርቶዶክሳውያን ላይ በተፈጸመው የዘር ማጥፋ ጭፍጨፋ መንግሥት አንድም ጊዜ የኀዘን መግለጫ አልሰጠም። ካሳ አልተከፈለም፤ ቤተ ክርስቲያንን ያወደሙ አካላት መልሰው እንዲታነጹ አልተደረገም። የእስልምና ጉዳዮች እንደ ተቋም አልተጠየቀም። ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ ጥቃት ለተፈጸመባቸው አካባቢዎች የመንግሥት ኃላፊዎች እና የጸጥታ አካላት ተጠያቂ ማድረግ ይኖርበታል። መንግሥት ኃላፊነቱን ቢወጣና ትኩረት ሰጥቶ ቢሆን አንድም ችግሮቹ ሳይፈጸሙ ይከላከል ነበር። ቢፈጸሙ እንኳ ቶሎ በመድረስ አጥፊዎችን ለሕግ ማቅረብ ነበረበት። ለሀገሪቱ ሰላምና ደኅንነት አደገኛ የሆነውን የሃይማኖት ጦርነት ሊያሥነሳ የሚችልን አደገኛ ድርጊት በቸልታ ከመመልከት ይልቅ

መፍትሔ መስጠት ብልህነት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአደባባይ "ሀገር ናት" ያሏት ቤተ ክርስቲያን በተደጋጋሚ ስትጠቃ የመንግሥት ምላሽ ዝምታ መሆኑ የሚያስገርም ነው።

## 6.3 መጅሊስ

የእስልምና እምነት የበላይ ጠባቂ የሆነው መጂልስ እስካሁን ከተፈጸሙት ጥቃቶች 99 በመቶ የሚሆነው በእስምና እምነት ተከታዮች መሆኑን አውቆ አማኞቹን ከእኩይ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማድረግ ይኖርበታል። ጽንፈኞች ሃይማኖታዊ ተልእኮ ይዘው በአደባባይ "አላህ ወአከበር" እያሉ ጥቃት ሲፈጽሙ ታይቷል። ድርጊቱ ተቋሙን የማይወክል ከሆነም በግልጽ ማውገዝና ጥቃት ፈጻሚዎቹ በሕግ እንዲጠየቁ መተባበር ይኖርበታል። ድርጊቱ ተቋሙን የሚወክል ከሆነ ደግሞ ኃላፊነቱን መውሰድ ይኖርበታል።

## 6.4 የፖለቲካ ፓርቲዎች

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሸከሙት የሕዝብን አጀንዳ ይዘው በመሆኑ የሕዝብን ጉዳት፣ ሕማም፣ ጩኸት ማሰማት ይኖርባቸዋል። ችግሩ እንዲወገድ መፍትሔ ማፍለቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እስካሁን ኦርቶዶክሳውያንን በተመለከተ ኃላፊነቱን የተወጣ የፖለቲካ ፓረቲ ባይኖርም ይህን ማድረግ ግዴታው ነው።

## 6.5 ሚድያዎች

ሚዲያ አራተኛው መንግሥት ተብሎ የሚታወቅ በመሆኑ ለመንግሥት አፈ ቀላጤ ከመሆን ወጥቶ የሕዝብ ድምጽ መሆን ይገባዋል።

## 6.6 ወጣት ክርስቲያኖች

ዘመናዊውን ትምህርት የቀሰመው ወጣት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ መሥራት የሚገባው ብዙ ነገር አለ። ችግር ሲከሠት የመከላከልም ሆነ መጪውን ጊዜ አስተማማኝ ለማድረግ መሥራት ለነገ የማይባል ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው። ድካሙ ውጤታማ እንዲሆንም በተደራጀና በተናበበ መልኩ በጋራ መቆም ይገባል። ከተነጣጠልን ለአጥቂዎቻችን ምቹ እንደምንሆንላቸው ማወቅ አለብን። ትግላችን ጦር መዝዞ እንደ መውጣት የቀለለ ሳይሆን በተጠና፣ በተደራጀ እና አንድ ማዕከላዊ አመራር ያለው መሆን ገባዋል። በተናጠል የምናደርገው ጥረት የሚያስገኘው ውጤት አጥጋቢ ስለማይሆን መተባበራችን አማራጭ የሌለው ተግባር ነው።

ኦርቶዶክሳውያንን ለመታደግ የምናደርገው ጥረት ሃይማኖታችን እንዳይጠፉ አስተዋጽዖ እያደረግን መሆናችንን ማወቅ አለብን፡፡ በቆራጥነት ሥራ ስንጀምር የሚደርስለት አጥቶ ዝም ያለው፣ ተገዶ የሰለመው ሁሉ ይመለሳል። በየሀገረ ስብከቱና በየደብሩ ለተግባራዊነቱ እንዲነሳሱ መቀስቀስ፣ ወጣቶችና ሠራተኞች በየመሥሪያ ቤቶቻችን ፣ በማኅበራዊና በሚዲያ ሱታፌያችን የቤተ ክርስቲያንን ጩኸት ማስተጋባት ይኖርብናል። በዚህም"-

*ሀ.* ***የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ***፡- ማኅበር፣ እድር እና ሌሎች ኦርቶዶክሳውያን የሚሳተፉባቸው አረጃጀቶች ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል። ግንዛቤ ለመፍጠር ጸሐፊያን፣ ጋዜጠኞች፣ አርቲስቶች ሞያቸውን ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ እንዲያውሉት ማስገንዘብ ሌላው ተግባር ነው። በየደብሩ በሰበካ ጉባኤ የምናገለግልም ሆነ በገጠር የሚገኙ ክርስቲያኖች የአንድን ክርስቲያን መጎዳት እንደ ሁላችን ጥቃት በመቁጠር ለተጎጂዎች የገንዘብ ፣ የቁሳቁስ፣ የመጠለያና ሌላም ድጋፍ ማድረግ ይገባቸዋል።

ለ. **በየቦታውና በየጊዜ ሰላማዊ ሠልፎችን ማድረግ፡-** ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በኦርቶዶክሳውያን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ እንዲመለከት፣ አምላካችን እግዚአብሔርም ግፋችንን አይቶ ይቅር ከጥፋት እንዲታደገን በፍጹም መንፈሳዊነት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን በየቦታው በተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎችን ማድረግ ይኖርብናል። እንዲህ ማድረጋችን የመንግሥትን ቸልተኝነትና በሴራ የተተበተቡ አካላትን ድርጊት ማጋለጥ ለነገ የማኘለው ተግባርና ኃላፊነታችን ነው።